# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

ልደታ ፋና የ2017 ዓ.ም የመጀመሪያ 6 ወር ዕትም

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ይገዛል አረጋ
ጌትነት መላኩ

**ሪፖርተር፡-**
ጌትነት መላኩ
መሰረት አለማየሁ
ሄኖክ ከድር
ይገዛል አረጋ
አቡበከር አሰፋ
መክሊት ይልማ

**ኤዲተር፡-**
ይገዛል አረጋ
ጌትነት መላኩ
መሰረት አለማየሁ
ሄኖክ ከድር

**ፎቶግራፈር፡-**
ድረስ ወርቁ
ብሩክ ተክሉ

**አስተባባሪ**
ሲፈን ባዩ

**ፀሀፊ፡-**
ሰላማዊት ተመል

## ማውጫ


1. የአዘጋጁ መልዕክት ....02
2. የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ሃላፊ መልዕክት....03
3. የዋና ስራ አስፈፃሚ መልዕክት ....03
4. የብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ሃላፊ መልዕክት ....04
5. ክህሎት መር ስራ እድል ፈጠራ ለዜጎች ተጠቃሚነት....05
6. የህዝብ እንደራሴ ትጋት....07
7. ትምህርት ለትውልድ ግንባታ....08
8. እናቅዳለን፣ እንተገብራለን እንፈፅማለን....10
9. ዘመናዊ የንግድ ስርዓት ለተሻለ እድገት....11
10. የተሟላ ሪፎርም ለቀልጣፋ አገልግሎት....12
11. በጎነት እና የልማት አርበኝነት ....14
12. ቀልጣፋ አገልግሎት በዘመናዊ አሰራር....16
13. ውጤታማ የፋይናንስ አሰራር ትግበራ....17
14. ፅዱ አከባቢ ለዘመናዊ አኗኗር....18
15. የበለፀገች ኢትዮጵያ ተረካቢዎች....20
16. በስዕብና የተገነባ ትውልድ ለሀገር ዕድገት....21
17. የአረንጓዴ አሻራ ተምሳሌት ....23
18. መስሪያ ቦታዎች ለልማት....24
19. ኢንዱስትሪ ለሀገር እድገት....25
20. ምግቤን ከደጃፌ....26
21. የህዝብ እና የመንግስት ሀብት ጠበቃ....26
22. የሰላም ዋጋው ስንት ነው....27
23. ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶቻችን ለብልፅግናችን!....28
24. ፕላንና ልማት....29
25. አገልግሎትን ያሳለጡ ቴክኖሎጅዎች ....30
26. ህዝብን ማገልገል ክብር ነው!....30
27. ትውልድን በስነ-ምግባር በመገንባት ሙስናን እንከላከል....31
28. ብክለት ይብቃ ዉበት ይንቃ ....33
29. የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለመልካም አስተዳር ስኬታማነት....34
30. መረጃን የማዘመን ጉዞ....35
31. ለሀገር ዕድገት የወጣቶች ሚና....36
32. የህዳሴ ግድባችን የአብሮነታችን ማሳያ....37
33. ጤናማ ትውልድ ለሀገር ዕድገት....38
34. ለመሰረታዊ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጥ ተቋም ....41
35. የህዝብ ንብረት ከብክነት የማዳን ተልዕኮ....43
36. ደንብና ስርአት ማክበር ስልጡንነት ነው ....44
37. ግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት....45


Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office

## የተቋሙ
## ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች

### የተቋሙ ራዕይ/Vision

በ2022 ዓ.ምጠንካራየኮሙኒኬሽንስርዓት በመዘርጋት በቂና የተሟላ መረጃ ያለው፤ በከተማዋ ሁለንተናዊ እድገት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ ህብረተሰብ በመፍጠር ከተማችን አዲስ አበባየአፍሪካየብልጽግናተምሳሌት ሆና ማየት።

### የተቋሙ ተልዕኮ/Mission

የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አግባቦችን በመጠቀም ዘመናዊ፣ ግልጽ እና ፈጣን ምላሽ መስጠትን ባህሉ ያደረገ የኮሙኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋትና በዘርፉ መሪ ሚና በመጫወት ብሎም በመንግስትና በህዝብ መካከል ጥራት ያለው እና ለሁሉም ነዋሪ ተደራሽ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ፡-

- የህዝቡን ትክክለኛ የመረጃ ፍላጎት በማርካት ተሳትፎውንና ተጠቃሚነቱን በቀጣይነት ማሳደግ፤
- የሀገራችንና የከተማችን መልካም ገጽታ መገንባት፤
- በዋና ዋና ሀገራዊና ከተማ አቀፋዊ አጀንዳዎች ላይ የጋራ መግባበት መፍጠር፤

### የተቋሙ እሴቶች/Values

- ተጠያቂነት፤
- ብዝሃነት፤
- ግልፅነት፤
- ተዓማኒነት፤
- የጋራ መግባባት መፍጠር፤
- ለጊዜ የላቀ ዋጋ መስጠት፤
- ለገጽታ ግንባታ ስኬት ግንባር ቀደም ሚና መጫወት፤

## የአዘጋጁ መልዕክት

መንግስት የሀገራችንን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዕድገት አሳይቶ ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጥረቶች በማድረግ ላይ ይገኛል።በተለያዩ ዘርፎች እየተደረገ ያለው ለውጥ ዜጎችንም ሆነ ሀገራችንን ተጠቃሚ ማድረግ ጀምረዋል። የተጀመሩትን ሀገራዊ ፕሮጀክቶች በከተማችን ተግባራዊ በመደረጋቸው የከተማችንን ነዋሪዎች ተጠቃሚ እያደረጉት ይገኛሉ።

በመከናወን ላይ የሚገኙትን ፕሮጀክቶች ቀጣይ በማድረግም ሆነ የዜችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የመንግስት ፣ የዜጎች፣ የባለሃብቱና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ርብርብን የሚጠይቅ በመሆኑ ሁሉም ኃላፊነቱን በመወጣት የሀገራችን ዕድገት ማፋጠንና የዜጎችን ተጠቀሚነት ማረጋገጥ ይገባናል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎችም በከተማችን እየተካሄዱ የሚገኙ ዜጋ ተኮር የሆኑ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን ነዋሪዎችም ኃላፊነታችን በመወጣት እየተሰሩ ባሉ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚነታችውን ማረጋገጥ ይገባቸዋል በማለት የዝግጅት ክፍል መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።

ልደታ ፋና የ2017 ዓ.ም የመጀመሪያ 6 ወር ዕትም



## ወ/ሮ ሲፈን ባዩ
## የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ

### ውጤታማ ተግባቦት ለሁለንተናዊ ዕድገት

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ጠንካራ የኮሙኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋት በቂና የተሟላ መረጃ ያለው፤ በሁለንተናዊ እድገት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ ህብረተሰብ በመፍጠር ከተማችን አዲስ አበባ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት እንድትሆን ለማስቻል የበኩሉን ራዕይ ሰንቆ በመንቀሳቀስ ላይ ነው፡፡

ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 74/2014 ዓ/ም በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አግባቦችን በመጠቀም ዘመናዊ፣ ግልጽ እና ፈጣን ምላሽ መስጠትን ባህሉ ያደረገ የኮሙኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋት ላይ ይገኛል፡፡

የኮሙኒኬሽን ዘርፉን በማጠናከር በመንግስትና በህዝብ መካከል ጥራት ያለውና እና ለሁሉም ነዋሪ ተደራሽ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ የህዝቡን ትክክለኛ የመረጃ ፍላጎት በማርካት ተሳትፎና ተጠቃሚነቱን ማሳደግ፣ የሀገራችንና የከተማዋን መልካም ገጽታ መገንባት እንዲሁም በዋና ዋና ሀገራዊና ከተማ አቀፋዊ አጀንዳዎች ላይ የጋራ መግባበትን መፍጠር የሚያስችል ተልዕኮ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

ጽ/ቤቱ በ2017 በጀት ዓመት በህዝብና ሚዲያ ግንኙነት ተግባራት ተግባቦት በመፍጠር የመረጃ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ የዲጅታል ሚዲያ፣ ሞኒተሪንግ እና የከሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መረጃ አገልግሎት ስርዓትን ማሳደግ እና ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀምና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማሻሻል ማዕከል ያደረጉ ስትረቴጂክ ግቦች ቀርፆ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት በዕቅድ ያስቀመጣቸውን ተግባራት ለማከናወን ያለሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡በዕቅድ ይዞ ያከናወናቸውን ተግባራት አፈፃፀም በየጊዜው በመገምገም የታዩ ጥንካሬዎችን ማስቀጠልና ክፍተቶችን በማረም ውጤታማ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ተቋሙ በ2017 በጀት ዓመት ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ስትሰሩ ለነበራቹህ ሁሉ ምስጋናየ የላቀ ነው በቀጣይም ድጋፋቹህ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አደራ እላለሁ



## ወ/ሮ አበባ እሸቴ
## የልደታ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ

### የዋና ስራ አስፈፃሚ መልዕክት

የአፍሪካ መዲና የሃገራችን ዋና ከተማ የኢትዮጵያ የብልጽግናችን ተምሳሌት፣የህብረ ብሄራዊነታችን መገለጫ የሆነችው አዲስ አበባ እንደስሟ ውብ እንድትሆን በክፍለ ከተማችን ይህን ታሳቢ ያደረገ ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስኬትን ለማስመዝገብ በተደራጀ የህብረተሰብ ተሳትፎ በመሥራት ፣ማህበረሰቡን ማዕከል ያደረገ የድህነት ቅነሳ-ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎች ላይ ትኩረት በማድረግ፣ የፀረ- ድህነት ትግሉን ሊያሰናክሉ የሚችሉ ውስጣዊም ውጫዊም ችግሮችን በማረም እና ህዝባችን የሚጠይቀውን በአግባቡ መመለስ የሚስችል ተቋም በመገንባት እንደ ክፍለ ከተማችን በርካታ ውጤታማ ስራዎችን አከናውነናል፡፡

በተጨማሪም በክፍለ ከተማችን ህዝቡን ያማከለ እቅድ በማቀድ በርካታ ስራዎችን ማከናወን የቻልን ሲሆን ለአብነትም መኖሪያ ቤት ፤ጤና ጣቢያና ትምህርት ቤቶችን በአጭር ጊዜ አስገንብተን ለአገልግሎት ክፍት አድርገናል፡፡
ከፀጥታ አኳያም ህዝቡ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባ የዕለት ተዕለት ተግባሩን በአግባቡ እንዲያከናውን የራሱን ደህንነት ከፀጥታ አካሉ ጋር በቅንጅት በመሆን የአካባቢውን ሰላም በማስጠበቅ ላይ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በክ/ከተማችን ስራ አጥ ሆነው ስራ ፈላጊ ወጣቶች በመመዝገብ በማደራጀትና በማቋቋም የስራ ዕድል መፍጠርና የነዋሪውን የገቢ አቅም እንዲጨምር በማድረግ ድህነትን ለመቀነስ በሚደረገው እንቅስቃሴ የጎላ ሚና እንዲኖረው ማድረግ በሚያስችል መልኩ ተግባሮችን በትኩረትና በቅንጅት በማከናወን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል። የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ የተለያዩ አማካኝ ቦታዎችን በመለየት ለገበያ አመቺ የሆኑትን ቦታዎች በማዘጋጀት የክፍለ ከተማ ነዋሪዎች በየአቅራቢያቸው ሄደው እንዲሸምቱ የሚያስችል ስራዎችን ለማከናወን ተችሏል::

አገልግሎት አሰጣጣችን ፈጣንና ቀልጣፋ ተደራሽ ለማደረግ በቴክኖሎጅ የተደገፈ አገልግሎት ለመስጠት መልካም ጅምሮች አሉ፣ በሰው ተኮር ተግባራትም በርካታ ስኬታማ ተግባራት ተከናውነዋል፣ በቀጣይም ክፍለ ከተማችን ምቹ የመኖሪያና የመሥሪያ አካባቢ እንዲሁም "ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጥበት ማዕከል ለማድረግ ከህዝባችን ጋር በአንድነት እንሰራለን"

## የ5ቱ ዓመታት ስኬታማ የለውጥ ጉዞ

ብልጽግና ፓርቲ በሀገራችን ኢትዮጲያ ሁለንተናዊ ብልጽግና እንዲረጋገጥ ሀገራዊ መግባባት እንዲኖር እና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን አልሞ በትጋት እየሰራ ይገኛል። ፓርቲው በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ለውጥን ለማምጣት የተለያዩ ስትራቴጅዎችን ነድፎ ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ በመሆን ባለፉት አምስት ዓመታት በተለያዩ ዘርፎች ለውጦችን አሰመዝግቧል።

ባለፉት 5 ዓመታት ዓመታት የለውጡን ማዕከላዊ ነጥብ ሰው ተኮር በማድረግ የዜጎችን ፍትሀዊ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ስራ በመስራት ፓርቲው የአይቻልም አስተሳሰቦችን በመጋፈጥ የይቻላል መንፈስን የሚያጎለብቱ የተለያዩ ኢንሼቲቮችን በመቅረጽ የወጣቶችናሴቶች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ከተስፋ ብርሃን ወደ ሚጨበጥ ብርሃን ለመሸጋገር ውሳኝ ምዕራፍ ላይ ይገኛል፡ ፡ ሀገሪቷን እየመራ የሚገኘው የብልጽግና ፓርቲ የህዝብ አንገብጋቢና ወቅታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ባለፉት የለውጥ ዓመታ ውጤታማ ተግባራትን አከናውኗል።



**አቶ ሐፍቱ ብርሃኑ**
**የልደታ ክ/ከተማ ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ**

ፓርቲው የኑሮ ውድነት የህዝባችን አንገብጋቢ ጥያቄ ነው በማለት ችግሩን ለመፍታት በትኩረት ሲሰራ ቆይቷል። በመሆኑም የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ የለውጡ መንግስት በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል።በዚህም የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ስርጭትና ተደራሽነት አሳድጓል፣የሰንበት ገበያዎችን አስፍቷል፣የወላጆችን ጫና ለማቃለል በሁሉም የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምገባን ተግባራዊ አድርጓል፣ በቀን አንድ ጊዜ እንኳን መመገብ የማይችሉ ዜጎችን ለመመገብ የምገባ ማዕከላትን ከፍቷል፣የሸገር ዳቦ ማከፋፍያን በማስፋት ዜጎች በተመጣጣኝ ዋጋ ዳቦ እንዲሸምቱ የማድረግና ሌሎች ስራዎችም ተከናውነዋል።

የስራ እድል ፈጠራ አማራጮችን በመጠቀምና አዳዲስ እድሎችን በማመቻቸት ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን የስራ እድል ከተፈጠረላቸው ውስጥም የወጣቶችና የሴቶች ድርሻ ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛል። ወጣቱ ሰርቶ እራሱንም ሆነ ቤተሰቡን እንዲደጉም ለማስቻል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል።

ከለውጡ በፊት አገልግሎት አሰጣጡ የህዝብን ችግር ከመፍታት ይልቅ ምሬትን ሲያስከትል ነበረ። የለውጡ መንግስት ይህንን ችግር ለመፍታት በትኩረት ሲሰራ ቆይቷል። ምንም እንኳን ገና ብንሆንም አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጅ በማዘመን ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት በማቅረብ ብዙ የህዝብ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል።

ብልጽግና ፓርቲ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶችን በአጠረ ጊዜ በመገንባት ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ችሏል። ጀምሮ መጨረስን ባህል ያደረጉ የፕሮጄክቶች አፈጻጸማችን የስራ ባህላችንን የቀየሩ፤ ቃላችንን የምንጠብቅና ድንቅ የአመራር ሰጪነት ያሳየንበት ሌላኛው ተግባር ነው።

ፓርቲው ዜጎች በምግብ ዋስትና እራሳቸውን እንዲችሉ ለማስቻል ከቀረጻቸው ፓኬጆች አንዱ የከተማ ግብርና የሌማት ቱሩፋት ተግባር ነው። ዜጎች ባላቸው ክፍት ቦታ የጓሮ አትክልት በማልማትና የከብትና የዶሮ እርባታ በማካሄድ በምግብ እራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ስራ በከተማ ግብርና ልማት ፓኬጅ ተሰርቷል።በሌላ መልኩ ካስመዘገበባቸው ተግባራት አንዱ የአረንጓዴ አሻራ ሲሆን መላው የኢትዮጲያ ህዝብን በማነቃቃት ደማቅ ታሪክ የተጻፈበት ትውልድ እንዲቀጥል መንገድ የተተለመበት ነው።

## የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

ከተማ የትናት አሻራ፣ የዛሬ ስራ፣ የነገ ርዕይ ድምር የስራ ውጤት በመሆኑ ከተማችንን ጽዱ፣ውብ፣ ምቹና ለኑሮ ተስማሚ ከማድረግ አኳያ በ7/24 የስራ ባህል ሰርተን ለህዝባችን አገልግሎት ክፍት ያደረግናቸው ትናንት፣ዛሬንና ነገን ያስተሳሰሩ ፕሮጀክቶቻችን ሕያው ምስክሮቻችን ናቸው፡፡
በአጠቃላይ የብልጽግና ፓርቲ የማህበረሰቡን ስር የሰደዱ ችግሮች በመፍታት ረገድ ውጤታማ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ፓርቲው በቀጣይ የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሰው ተኮር እቅዶችን አቅዶ እየሰራ ሲሆን እነዚህ አቅዶች ስኬታማ እንዲሆኑም ማህበረሰቡ ከፓርቲው ጎን እንዲሆን ጥሪየን አቀርባለሁ፡፡

አመሰግናለሁ

## ክህሎት መር ስራ እድል ፈጠራ ለዜጎች ተጠቃሚነት

የዜጎችን የስራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ ብሎም በኢኮኖሚ እራሳቸዉን እንዲችሉ ለማስቻል መንግስት ከሚመለከተዉ ባለድርሻ አካል ጋር ተቀናጅቶ ዘርፈ ብዙ ስራዎች እየሰራ ይገኛል፡፡ በእዚህም መሰረታዊ ለዉጥ ማምጣት ችሏል፡፡ በእቅድ ደረጃም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ከሚታቀድ ተግባር መካከል ዋነኛዉ ይህ የስራ እድል ለዜጎች መፍጠር ሲሆን በሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች በጉዳዩ ዙሪያ በባለቤትነት የድርሻቸዉን ወስደዉ እያቀዱና እየሰሩበት መሆኑም ለጉዳዩ ምን ያክል ትኩረት እንደተሰጠዉና ዉጤታማ እንደሆነም ያሳያል፡፡ በእዚህ ተግባርም በየቀኑ እና በየአመቱ አዳዲስ ስራ እድሎች እየተፈጠሩ ዜጎች የስራ ባለቤት እንዲሆኑም ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ዜጎች ለስራ ያላቸዉ ፍቅርና ባህል በየጊዜዉ እየዳበረ እንዲሄድም ለሴቶች፣ለወጣቶች፣ለአረጋዉያንና ለአካል ጉዳተኞች እንደ የእድሜቸዉ ሁኔታ ታይቶ በመረጡት የስራ ዘርፍ ስልጠናና ክህሎት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በዛሬዉ የመጽሄት አምዳችንም ትኩረት ያደረግነዉ በእዚሁ ጉዳይ ላይ ሲሆን እንደ ልደታ ክፍለ ከተማ ስራና ክህሎት ጽ/ቤት ዜጎች በልዕልና እና በቴክኒክ ክህሎት አብቅቶ የተመቻቸ ወይም የተፈጠረ የስራ እድል አለ ወይ በሚል ዙሪያ ነዉ፡፡ እስኪ እንደመነሻ ልዕልና እና ቴክኒክ ክህሎት ምን ማለት ናቸዉ? ያላቸዉ ጠቀሜታስ ምንድነዉ? የሚለዉን እንመልከት፡፡

ልዕልና ከሁሉ በላይ መሆን ማደግ መበልጸግ፣ታላቅነት፣በስራም ሆነ በህይወት አመለካከታችን ከፍ ማለት ነዉ፡፡

ቴክኒክ ክህሎት ማለት ደግሞ የሰዉ ልጅ በዉስጡ ያለ እምቅ ሀብት ወይም ፍላጎት፣ዝንባሌ፣ተሰጥኦ፣ጥንካሬ ወደ ተግባር በመለወጥ እንዲሁም በህይወት ዘመን የሚገጥሙ የኑሮ ጥያቄዎችን / ገጠመኞችን/ዉጤታማ በሆነ መንገድ በመመለስ በማህበረሰቡ ዉስጥ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ለመኖር የሚያስችሉ የህይወት ስልቶች ማለት ነዉ፡፡ ታዲያ ቴክኒካል ክህሎት ስናዳብር፡- የሚጎዳና የሚጠቅመንን እንለያለን፣መነሻና መድረሻችንን እናዉቃለን፣በአላማ እንመራለን፣ገጠመኞቻችንን ሙሉ ወደ ጥቅም መለወጥ እንችላለን፡፡ በቴክኒካል በክህሎት እና በልዕልና ዙሪያ ያለን ግንዛቤ ግልጽ ከሆነ እንደልደታ ክፍለ ከተማ ስራና ክህሎት ጽ/ቤት በ2017 በጀት አመት የተከናወኑ ተግባራቶችና ተያያዥ ጥያቄዎችን ከክ/ከተማዉ ምክትል ስራ አስፈጻሚና ስራና ክህሎት ጽ/ቤት ሃላፊ ከሆኑት ከወ/ሮ ነጻነት ደረሰ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገን ነበር በንባብ ተከታተሉን መልካም ቆይታ!



**ወ/ሮ ነፃነት ደረሰ**
**የክ/ከተማው ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚና**
**የስራና ክህሎት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**የስራና ክህሎት ጽ/ቤት የ2017 በጀት አመት ከዝግጅት ምዕራፍ ጀምሮ እየሰራቸው ያሉ ስራዎች ዋና ዋናዎቹ ምንድናቸው?
**ወ/ሮ ነጻነት፡-** የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸምን በየደረጃው በመገምገምና ጥንካሬና ክፍተቶችን በመለየት ለ2017 በጀት አመት እቅድ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡ የ2016 ዓ.ም የእቅድ አፈጻጸም ምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ በአፈጻጸም የተሻሉ እና ወደፊት የመጡ ወረዳዎችና ባለድርሻ አካላት የዋንጫና ሰርተፍኬት በመስጠት የማበረታታት ስራ የተሰራ ሲሆን የተሻለ አፈጻጸም ላላቸው ከክ/ከተማ እስከ ወረዳ ለሚገኙ የስራ አስተባባሪዎች፤ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች የሰርተፍኬትና የቦንድ ሽልማት በመስጠት የማነቃቃት ስራ ተሰርቷዋል፡፡

ዘርፉ በርካታ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍና በቅንጅት የሚሰራ በመሆኑ የቅንጅት ስራን ከሚያከናውኑ እና አብረውን ከሚተገብሩ 21 ጽ/ቤቶች ጋር የጋራ እቅድ በማዘጋጀትና በእቅዱ ላይ በመግባባት የቅንጅታዊ አሰራር መተግበሪያ የአተገባበር ስምምነት ፊርማ በማኖር ወደተገባር እንዲገባ ተደርጓል፡፡

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት

## Lideta Sub-City Communication office

የ2017 በጀት አመት የእቅድ አፈጻጸም የተሻለ አተገባበር እንዲኖረው የሚረዱ የደጋፊ እቅዶችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ጽ/ቤቶች በደብዳቤ እንዲደርስ በማድረግ ወደ ተግባር ገብተናል፡፡ በየደረጃው የሚካሄዱ መደበኛ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚካሄዱ የስራ ግምገማዎች፣ ወቅቱን ጠብቀው ተደርገዋል፡፡ አንድ ደረጃ ዝቅ ብሎ የሚደረጉ ቼክሊስትን መሰረት ያደረጉ ድጋፍና ክትትሎች እየተደረጉ ሲሆን፣ የእቅድ አፈጻጸምና የሪፖርት ግብረ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ወጣቱን በልዕልና እና በቴክኒክ ክህሎት አሰልጥኖ እራሱን ወደ ስራ እንዲያስገባ የተደረገበት አግባብ ምን ይመስላል?

**ወ/ሮ ነጻነት፡-** በበጀት አመቱ ከዝግጅት ምዕራፍ ጀምሮ ዘርፈ ብዙ ክንዉኖችን መስራት ችለናል፡፡ ምክንያቱም ተቋሙ ሲቋቋም ዓላማ አድርጎ የተነሳዉ በወጣቶች ስራ እድል ፈጠራና ማህበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ነዉ፡፡ በእዚህ መሰረትም ከአመት አመት እየቀነሰ ሳይሆን ዉጤቱ እየጨመረ የመጣ የስራ እድል ለወጣቶች ወይም አጠቃላይ እንደክፍለ ከተማችን ለሚገኙ ዜጎች መፍጠርና ዓላማዉን ማሳካት ተችሏል፡፡ እንደምሳሌ ማንሳት ካስፈለገም 1ኛ ሩብ ዓመት በ10ሩም ወረዳዎች በ311 ብሎኮች ላይ 32292 ነዋሪዎችን እና ስራ ፈላጊዎችን የማወያየት ስራ ተሰርቷል፡ ፡በክ/ከተማ ደረጃ በተፈጠረ የግንዛቤ መድረክ ወጣቶችንና ሴቶችን ወጣቶችንና ሴቶችን በማወያየትና ግንዛቤዉን ካገኙ በኋላ ወደ ተግባር እንዲገቡ ክትትል እያደረግን እንገኛለን፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ስራ እድል ፈጣሪ የሆኑ የግል ድርጅቶችን ማወያየትና 5986 ወጣት ስራ ፈላጊዎችን ተመዝግበው በሰለጠኑት ቅጥር እንዲፈጸምላቸዉ የትስስር ስራ ሰርተናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ወጣቱን የስራ ፍላጎት ለማሻሻልና ባገኘው የስራ ዘርፍ መስራት እንዲችል ጽ/ቤታቹ ምን ተግባራትን እየሰራ ነው?

**ወ/ሮ ነጻነት፡-** ጽ/ቤታችን የሚከተለው የስራ እድል ፈጠራ መርህ ክህሎት መር የስራ እድል ፈጠራ በመሆኑ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ለህብረተሰቡ እና ስራ ፈላጊው የህብረተሰብ ክፍል ውይይት በሚደረግበት ጊዜ እና ራሱን የቻለ መድረክ በመፍጠር አንዱ ዋና አጀንዳ በማድረግ የስራ ማማረጥ ባህልን ለመቀየር የሚያስችል የአመለካከት ቀረጻ ስራ፣ የጸጋ ልየታ፣ የስራ ፈላጊ ምዝገባ፣ ለተመዘገቡ እና ዘርፍ ለመረጡ ስራ ፈላጊዎች የልዕልና ቴክኒካል ክህሎት ስልጠና ማመቻቸት፣ የመስሪያ ቦታ በሚፈልጉ ዘርፎች አደራጅቶ ወደ ስራ የማስገባት፣ የቅጥር እና የስራ ትስስር የማመቻቸት ስራዎች እና ሌሎች መንግስታዊ ድጋፎችን የማመቻቸት ስራ እየተሰሩ ነው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በበጀት አመቱ ምን ያክል ወጣት ሴትና አካል ጉዳተኛ በምን በምን ዘርፍ በማሰልጠን ወደ ስራ (ተግባር) ማስገባት ተቻለ?

**ወ/ሮ ነጻነት፡-** በ2017 በጀት አመት ከላይ ከተገለጹ የቅድመ ዝግጅትና የአመለካከት ቀረጻ ስራዎች ጎን ለጎን ለ2665 ወጣቶች እና ሴቶች የልዕል /የኢንተርፕረነርና የብቃት አሀድ የማይጠይቁ/ እና የቴክኒካል ክህሎት ሙያዊ የሆኑ እና የብቃት አሀድ የተዘጋጀላቸውና በምዘና ብቃታቸው በሚረጋገጥ ሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 768 አንቀሳቃሾች በ140 አንተርፕራይዞች ተደራጅተዋል፡፡ ለ1762 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ተፈጠሯል፡፡ ከተፈጠረው የስራ እድልም 1013 (57.5%) ሴቶች ሲሆኑ 1105 (62.7%) ደግሞ ወጣቶች ናቸው፡፡ ይህም ወጣቶችና ሴቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ያመላክታል፡፡ የተፈጠረውን የስራ እድል በዘርፍ ስንመለከት በከተማ ግብርና ዘርፍ 86 (4.9%)፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ማለትም በማኑፋክቸሪንግና ኮንስትራክሽን 471 (26.7%)፣ በንግድና አገልግሎት ዘርፍ 1205 (68.4%) ነው፡፡ በሩብ ዓመቱ በ81 ኢንተርፕራይዞች ለተደራጁ 189 አንቀሳቃሾች የመስሪያ ቦታ የተመቻቸ ሲሆን 735 ኢንተርፕራይዞችን በስራ ገበያ መረጃ ስርዓት መመዝገብ ተችሏል፡፡ በሩብ ዓመቱ ስራ መስራት ለሚችሉ 15 አካል ጉዳተኞችም የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በመንግስት የሚደረግላቸው ድጋፍና ክትትል ካለ?

**ወ/ሮ ነጻነት፡-**ዘርፉ ከስራ እድል ፈጠራ እና ድህነት ቅነሳ ባሻገር የሃብት ክፍፍልን ፍትሃዊ በማድረግና በስራ እድል ፈጠራው ሀብት እንዲያፈሩ፣ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከመደገፍ ባለፈ ለሌሎች የስራ እድል እንዲፈጥሩ፣ በሀገራዊ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የበኩላቸውን ተሳትፎ እንዲያበረክቱ እና የሀገራችንን ብልጽግና በማረጋገጥ ሂደት ሚናቸውን እንዲወጡ  የሚያስችሉ መንግስታዊ ድጋፎች እየተደረጉ ነው፡፡

የሚደረጉ ድጋፎችም ለስራ ለማዘጋጀት መረጃ መስጠትና የግንዛቤ ፈጠራ፣ የጸጋ ልየታ፣ የስራ ፈላጊ ምዝገባ፣ የስልጠና ማመቻቸት፣ የማደራጀት ሲሆኑ ወደ ተጠቃሚነት የሚወስዱ ደግሞ የስራ ትስስር የማድረግ፣ እንደየ ዘርፉ ባህሪ የመስሪያ ቦታ የማመቻቸት፣ ማስቆጠብ፣ ብድር ማመቻቸት፣ የገበያ ትስስር የመፍጠር፣ በስራ ቦታ ላይ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ መስጠት፣ የእድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት የመስጠት፣ ኢንተርፕራይዞችን በስራ ገበያ መረጃ ስርዓት የመመዝገብና የገበያ እና ሌሎች መረጃዎችን የሚያገኙበትን ስርዓት የማመቻቸት ስራዎች ከሚሰጡ ድጋፎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በቀጣይ የስራ አጥ ምጣኔን ለመቀነስ ምን እየተሰራ ይገኛል?

**ወ/ሮ ነጻነት፡-** በ2017 የበጀት አመት ክህሎት መር የስራ እድል ፈጠራ መርህን በመከተል የክ/ከተማችንን የስራ አጥነት ቁጥር ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ ለ24000 የክ/ከተማችን ነዋሪ ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ የያዝነውን እቅድ ለማሳካት እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን በመለየት በተለይም የስራ ማማረጥ ችግርን ሊቀርፍ የሚችል የአመለካከት ቀረጻ ስራ መስራት፣ ወላጆች፣ ህብረተሰቡ እና ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ በማስቻል፣ ጸጋዎችን አሟጦ በመለየት ስልጠናን መሰረት ያደረገ ቋሚ የስራ እድል በመፍጠር፣ መንግስታዊ ድጋፎችን ጥገኝነትን በማያበረታታ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በማቅረብ በአጠቃላይ የክ/ከተማችን ነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሁሉንም ፈጻሚ እና ባለድርሻ አካላት በማቀናጀትና የአቅማችንን ብቻ ሳይሆን ከአቅማችን በላይ አስፍቶ በመስራት በከተማ አስተዳደሩና በክፍለ ከተማችን የ10 አመትና የ5 አመት ሰው ተኮር እቅዳችን ለማሳካት ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

## የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

**ልደታ ፋና፡-** ለወጣቱና አጠቃላይ ለማህበረሰቡ የሚያስተላልፉት መልክት ካለ?

**ወ/ሮ ነጻነት፡-** ዘርፉ የስራ አጥነት ችግር የሚቀረፍበት፣ ድህነት የሚቀነስበት፣ የሃብት ክፍፍል ፍትሃዊነት፣የሚረጋገጥበት ዜጎች ከራስ ፍጆታ ባለፈ ወደ ባለሃብትነትና ስራ ፈጣሪነት የሚሸጋገሩበት እንዲሁም የሀገራችንን ብልጽግና ለማረጋገጥ መሰረት የሚጣልበት የመንግስት ቁልፍና ቁጥር አንድ አጀንዳ ነው። በመሆኑም ይህንን ግዙፍ ተግባር ለማስፈጸም በዋናነት መንግስት ከፌዴራል እስከ ወረዳ ተቋም ፈጥሮ እየሰራ ቢሆንም ተግባሩ በመንግስት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ የተለያዩ አካላትን ልዩ ርብርብ ይጠይቃል።

ከእዚህ አኳያ በተለይ ስራ ፈላጊ የሆነው ወጣት ስራን ባለማማረጥና ጉልበት ተኮር በሆኑ ዘርፎች ላይ ተሰማርቶ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ስራ ፈላጊው ወጣት በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ ከመሆኑ አንጻር የወጣቱን የስራ ማማረጥ እና ዝቅ ብሎ መስራት ያለመፈለግ ባህሪን ወላጅና ማህበረሰቡ ከመንግስት ጋር በመተባበር በአመለካከት ቀረጻ ስራው ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶች የወጣቶችን እና የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ስራዎች ላይ ሚናቸውን እንዲወጡ እያልኩ በጋራ፣ በቅንጅትና በትብብር ከሰራን የከተማችንና የሀገራችንን ልማት በማረጋገጥ የዜጎቻችንን ተጠቃሚነት ማጎልበትና ማሳደግ ስለሚቻል ለጋራ ብልጽግናችን አብረን እንስራ የሚል መልክቴን ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን የቃለ መጠይቅ ጊዜ በጣም አመሰግናለሁ
**ወ/ሮ ነጻነት፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ

### የህዝብ እንደራሴ ትጋት

የልደታ ክፍለ ከተማ ምክር ቤት አስፈጻሚ አካላት ለክፍለ ከተማው ህዝብ በአግባቡ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥና ክፍተት ካለ ለመደገፍ እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እና በሚያደርጋቸው ድንገተኛ ምልከታዎች መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም ሁንም ያለበቂ ምክንያት ቢሮ የማይገኙ አመራሮች እና ባለሙያዎች መኖራቸውን እያረጋገጥን ነው በማለት በተደጋጋሚ በጉባኤ ከአባላቱ ይነሳል። ምክር ቤቱ በጉባዔ የሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎችን ለአስፈጻሚ አካላት በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ከማድረግ ባሻግር አስፈጻሚ አካላት ጥያቄዎችን መፍታታቸውን በአካል ወርዶ በሱፐርቪዥን ያረጋግጣል። የተፈቱ፣ ያልተፈቱ እና በሂደት ላይ ያሉ ጥያቄዎችንም ለይቶ ያልተፈቱና በሂደት ላይ ያሉ ጥያቄዎች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ አስኪፈቱ ድረስ ይከታተላል። ምክር ቤቱ የአስፈፃሚውን ተግባራት ክትትልና ቁጥጥር ስራ በተመለከተ እና በአዋጅ የተሰጡትን ተግባራት አፈፃፀም ዙሪያ ከልደታ ክ/ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ዘሪሁን ሽፈርዳ ጋር የዝግጅት ክፍላችን ቆይታ አድርጋለች። መልካም ንባብ።



**አቶ ዘሪሁን ሽፈርዳ**
**የልደታ ክ/ከተማ ምክር ቤት አፈ- ጉባኤ**

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለቃለ-መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን።
**የተከበሩ አቶ ዘሪሁን፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ በፅ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** ከተሰጣችሁ ስልጣንና ሀላፊነት አንፃር በአስፈፃሚ አካላት ላይ የምታደርጉት የክትትል እና ቁጥጥር ስራ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
**የተከበሩ አቶ ዘሪሁን፡-** ምክር ቤቱ የሚከናወኑ ተግባራትን በድጋፍ፣ ክትትልና በመስክ ምልከታ የአስፈጻሚ አካላትን እቅድ ተፈጻሚነት ያረጋግጣል፤ ክፍተቶች ሲታዩ እንዲስተካከሉ ግብረ መልስ ይሰጣል፤ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ጥብቅ ክትትል ያደርጋል። በየደረጃው ያለን አመራርና ባለሙያ ብልሹ አሰራርን እና ሌብነትን በመጸየፍ ህዝብን በቅንነትና በፍትሀዊነት ማገልገል እንዲችል ክትትል ያደርጋል። የልደታ ክ/ከተማ ምክር ቤት በዘንድሮው ዓመት በመልካም አስተዳደር የተሰሩ ስራዎች የተሻለ አፈጻጸም የታየባቸው ናቸው።

ልደታ ፋና የ2017 ዓ.ም
የመጀመሪያ 6 ወር ዕትም

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት

Lideta Sub-City Communication office

**ልደታ ፋና፡-** ክትትል እና ቁጥጥር የምታደርጉበት አግባብ ምን ይመስላል?

**የተከበሩ አቶ ዘሪሁን፡-** የክፍለ ከተማው አስፈጻሚ አካላት በአገልግሎት ቀን በተለይ ረቡዕ እና ዓርብ ከስብሰባና ከሌሎች ተልእኮዎች ነጻ ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ድንገተኛ ምልከታ ያካሂዳል። የድንገተኛ ምልከታው ዋና አላማ አስፈጻሚ አካላት ለክፍለ ከተማው ህዝብ በአግባቡ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥና ክፍተት ካለ ለመደገፍ እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ነው። አገልግሎት ፈላጊ ደንበኞችንም መጠይቅ አዘጋጅተን እንዲሞሉ በማድረግ የአስፈጻሚ አካላት አገልግሎት አሰጣጥ ያለበትን ሁኔታ ለመዳሰስ ሞክረናል። በተደጋጋሚ ባደረግናቸው ድንገተኛ ምልከታዎች መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በምናደርገው ምልከታ ያለ በቂ ምክንያት ቢሮ የማይገኙ አመራሮች እና ባለሙያዎች መኖራቸውን አረጋግጠናል። ሁሉም አመራርና ባለሙያ አገልግሎት ፈላጊውን ህዝባችንን በቢሮ ተገኝቶ አገልግሎት እንዲሰጥ የተቀመጠውን አቅጣጫ አክብሮ ሊሰራ ይገባል። ነገር ግን ያለ በቂ ምክንያት በአገልግሎት ቀን በቢሮ ተገኝተው አገልግሎት የማይሰጡ አመራርና ባለሙያዎች ላይ በቀጣይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ም/ቤቱ ይሰራል።

**ልደታ ፋና፡-** ከማህበረሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎች፤ አቤቱታዎች እና ጥቆማዎች እንዲስተካከሉ ምን ተሰርቷል?

**የተከበሩ አቶ ዘሪሁን፡-** የኛ ውክልና የመረጠን ህዝብ ጥያቄዎች እንዲመለሱ አስፈጻሚ አካላትን መከታተል፣ መደገፍና መቆጣጠር ነው፡፡ አስፈጻሚ አካላትም በየጊዜው በምናደርገው ድጋፍና ክትትል በርካታ የህዝብ ጥያቄዎችን እየፈቱ በመሆኑ በምክር ቤቱ ስም እያመሰገንኩ ቀሪ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን በምናደርገው የጋራ ጥረት በፍጥነት እንዲመለሱ በማድረግ የህዝባችንን እርካታ ከፍ ለማድረግ መስራት ከሁላችንም የሚጠበቅ ሀላፊነት ነው። በዚህ አመት ባደረግነው ሱፐርቪዥን የተፈቱ፣ ያልተፈቱና በሂደት ላይ ያሉ ችግሮችን ለይተናል፡፡ በቀጣይ በሚኖረን መድረክ ከአስፈጻሚ አካላት ጋር በጋራ ገምግመን የነዋሪዎቻችን ጥያቄዎች እዲመለሱ እናደርጋለን። በተደጋጋሚ በምክር ቤት ጉባዔና በተለያዩ መድረኮች የምክር ቤት አባላት ያነሷቸው በርካታ ጥያቄዎች ቢመለሱም አሁንም ቀላል የማይባሉ ችግሮች አለመፈታታቸውን አረጋግጠናል። በቀጣይ ክትትላችንን በማጠናከር እንሰራለን።

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን።

**የተከበሩ አቶ ዘሪሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## ትምህርት ለትውልድ ግንባታ

ትምህርት በአንድ አገር ውስጥ የሚከናወኑ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ያለው ሚና ትልቅ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ለዚህም መንግስት የተለያዩ አማራጮችን በመንደፍ የትምህርት አሰጣጡ እና የተማሪዎች ውጤት እንዲሻሻል የተለያዩ አማራጮችን በመተግበር ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ ተገኝተው ማግኘት ያለባቸውን እውቀት መቅሰም እንዲችሉ የሚያደርጉ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።በእውቀት የታነፀ ዜጋ በበዛ ቁጥር ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው አስተዋፅኦ የጎላ በመሆኑ ሀገራት ለዘርፉ የሚሰጡት ትኩረት በየጊዜው እየጨመረ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ። በሀገራችን ኢትዮጵያም ለትምህርት የተሰጠው ትኩረት ለዚህ እንደዋቢ ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል።

በዕውቀት የታነፀ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት ባለፉት ዓመታት የትምህርት ሽፋን በሁሉም ደረጃዎች በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ በመንግስት የተደረገው ጥረት እጅግ ውጤታማ ከመሆኑም ባሻገር በትምህርት ጥራት ላይ እየተደረገ ያለው ርብርብና ጥረት አሁንም የመንግስትን ቁርጠኝነት የሚጠይቅበት ደረጃ ላይ እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በእውቀትና በክህሎት የታነፀ አስተማማኝ ዜጋ የማፍራት ስራው በትኩረት እየተሰራ ይገኛል:የልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤትም ይህን በመረዳት ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በ2017 በጀት ዓመት እያከናወነ የሚገኘውን ስራ የጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አሰፋ ግርማን ቃለ መጠይቅ በመስራት እንዲህ አቅርበነዋል።



**አቶ አሰፋ ግርማ**
**የትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግና ተማሪዎችን ወደትምርት ቤት ከማምጣት አንጻር የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ አሰፋ፡-**የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ የቤት ለቤት ቅስቀሳ፣ ከእድርእና ከልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲሁም በተለያዩ ህዝባዊ መድረኮች ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ሰፊ የቅስቀሳ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሰረት በመንግስት፣ በግልና በህዝብ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የተመዘገቡ ሲሆን ጥቅል ተሳትፏቸውን በቅድመ አንደኛ ደረጃ 14,609፤ በአንደኛ እና በመካከለኛ ደረጃ 31,129 እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ 13,664 ማድረስ ተችሏል። በአፋን ኦሮሞ ስርዓተ ትምህርት አተገባበር ላይ በየደረጃው ያሉ አመራሮችና አደረጃጀቶች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ ቅበላ እና አፈጻጸም ግምገማ ዙሪያ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ሰፊ ስራ ተሰርቷል። በኦንላይን(on-line) ምዝገባ በቅድመ አንደኛ ደረጃ 345 ተማሪዎች፣ በአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ 796 ተማሪዎች እንዲሁም በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደግሞ 431 ተማሪዎችን በመቀበል ማስተማር ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**የትምህርት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥና የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ለማሳተፍ እየተሰራ ያለው ስራ ቢገልፁልን?

**አቶ አሰፋ፡-**የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎችን በቁጥር ከቅድመ አንደኛ እስከ በሁለተኛ ደረጃ 945 ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በቤት ለቤት የተለዩ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተማሪዎች ወደ ት/ቤት እንዲመጡ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር 206 ተማሪዎች ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ መልኩ በመሰረታዊ የጎልማሶች ትምህርት 267 ጎልማሶችን እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማታው መርሀ ግብር በአጠቃላይ 2,167 ተማሪዎችን በመመዝገብ ማስተማር ተችሏል፡፡ በአፋን ኦሮሞ ስርዓት ትምህርት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎችን በቁጥር ከቅድመ አንደኛ እስከ በሁለተኛ ደረጃ 60 ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በቤት ለቤት የተለዩ የአፋን ኦሮሞ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተማሪዎች ወደ ት/ቤት እንዲመጡ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር 16 ተማሪዎች ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ መልኩ በመሰረታዊ የጎልማሶች ትምህርት 49 ጎልማሶችን እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በማታው መርሀ ግብር በአጠቃላይ 144 ተማሪዎችን በመመዝገብ ማስተማር ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የእንግሊዝኛና ሒሳብ ትምህርቶችን ለማሻሻል እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ አሰፋ፡-**በሁሉም የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ለ6ኛ፤ ለ8ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሁለቱም መረሃ ግብሮች በክ/ከተማ ደረጃ በእንግሊዘኛና በሒሳብ ትምህርቶች የPerformance Placement Test እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በፈተናው ውጤት መሰረት በሶስቱም የክፍል ደረጃዎች በእያንዳንዱ 49% እና በታች፤ ከ50%-74% እንዲሁም ከ75% ውጤት እንዲተነተን በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ ተደርጓል፡፡

ለአንደኛና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝኛ እና የሂሳብ መምህራን የስልጠና ማዕከላት በስትራቴጂው አተገባበር ዙሪያ ስልጠና በመስጠት መምህራን ብቁ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ትምህርቶችን የተሳኩ ለማድረግ የእንግሊዝኛና የሂሳብ ቤተ ሙከራ በግብዓት የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ለማዳበር እንዲቻል በሳምንት ሰኞ ሙሉ ቀን ተግባቦቱን በእንግሊዝኛ ማድረግ ተችሏል፡፡ተማሪዎች በሂሳብና በእንግሊዘኛ ትምህርቶች መሻሻል እንዲመጣ በትምህርት ተቋማትና በክላስተር ማዕከላት የተማሪዎች የጥያቄና መልስ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በስትራቴጂው የተቀመጡ ተግባራት በታሰበው መንገድ እየተከናወኑ መሆናቸውን፣ በሂደቱ ውስጥ ለውጥ ስለመኖሩና መሻሻል ያለባቸውን በታዎች ለመለየት ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ በእንግሊዘኛና በሒሳብ ትምህርቶች ላይ የትምህርት ባለሙያዎችና ሱፐርቫይዘሮች በልዩ ሁኔታ የክፍል ምልከታና ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ለእንግሊዝኛና ሒሳብ ትምህርቶችን ትኩረት የተሰጠበት ዓላማ ምንድን ነው?

**አቶ አሰፋ፡-**ከ1ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በእንግሊዘኛ እና ሒሳብ የትምህርት ዓይነቶች ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ከአማካይ በታች አፈጻጸም እያሳዩ ሲሆን ውጤቱም ከ50 በመቶ በታች ዝቅ ያለ በመሆኑ በሁለቱ የትምህርት ዓይነቶች ውጤት ከፍ ለማድረግ በማሰብ ስትራቴጅውን መተግበር ተጀምሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእንግሊዝኛና የሒሳብ ትምህርቶች የትምህርትና የስራ ስኬት ወሳኝ መሆናቸውን ከግምት በማስገባት በትምህርት ቤቶች ለሁለቱ ትምህርቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የእንግሊዝኛና ሒሳብ ስትራቴጂ በመተግበሩ የመጡ ለውጦች እንዴት ይገለጻሉ?

**አቶ አሰፋ፡-**በሂሳብና እንግሊዝኛ ትምህርቶች ውጤታማና አላማ ተኮር የማጠናከሪያ ትምህርት ወጥ በሆነ ፕሮግራም በየተቋማት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ተግባሩ ከተጀመረ በኋላ በተደረገው ክትትልና ድጋፍ መምህራን የእንግሊዝኛና የሒሳብ የማስተማር ችሎታን እና የይዘት እውቀትን በማሻሻል አጠቃላይ መማር ማስተማሩን መደገፍ ችለዋል፡፡ስለትምህርቶቹ ለወላጆች በተሰጠው ግንዛቤ መሰረት ለልጆቻቸው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ለልጆቻቸው ድጋፍ ማድረግ ችለዋል፡፡የሂሳብ እና እንግሊዝኛ መምህራን ተነሳሽነት መጨመሩ እና መምህራን በቀላሉ ሁሉንም ተማሪዎች መድረስና መደገፍ አስችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የተጀመረውን የእንግሊዝኛና የሂሳብ ትምህርቶችን ለማሻሻል እየተወሰደ ባለው እርምጃ ከባለድርሻ አካላት የሚጠበቁ ተግባራት ምን መን ናቸው?

**አቶ አሰፋ፡-** የትምህርት ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን በተለይም የእንግሊዝኛና ሒሳብ ትምህርቶችን ለማሻሻል የተጀመረው ስትራቴጂ ውጤታማ እንዲሆን ስራዎች በመንግስት ብቻ ሊከነወኑ ዐይገባም፡፡ ባለድርሻ አካላት የትምህርት ስራውን በገንዘብም ሆነ በጉልበት በመደገፍ ተመሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ከትምህርት ጽ/ቤት ጋር በመተበበር ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ወላጆች የልጆቻቸውን ውጤት በመከታተልና ከመምህራን ጋር በመነጋገር ውጤታቸው የተሻለ እንዲሆን መስራት ያስፈልጋል፡፡

ከስትራቴጂክ ዕቅድ ከማቀድ ጀምሮ በሁሉም የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ለ6ኛ፤ ለ8ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሁለቱም መረሃ ግብሮች በክ/ከተማ ደረጃ በእንግሊዝኛና በሒሳብ ትምህርቶች የPerformance Placement Test እንዲሰጥ በማድረግ ውጤት ተተንትኖ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ ተደርጓል፡፡ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ሊጠቀሙበት የሚችል የእንግሊዝኛ እና የሂሳብ ቤተ-ሙከራ በግብአት ማሟላት እና ማደራጀት ተችሏል፡፡ በሁሉም የትምህርተ ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ለማዳበር በሳምንት አንድ ቀን (ሰኞ) ሙሉ ቀን ተግባቦቱን በእንግሊዝኛ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሰኞ ዕለትም መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘት አንድ ክፍለ ጊዜ የሚያስተምሩበት የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በትምህርት ተቋማትና በክላስተር ማዕከላት በሂሳብና እንግሊዝኛ ትምህርቶች ላይ በተማሪዎች መካከል የጥያቄና መልስ ውድድር ማካሄድ ተችሏል፡፡

የእንግሊዝኛ እና የሂሳብ ትምህርት ማጠናከሪያ የሚሰጡ መምህራንን በሚወጡ መስፈርቶች በመመልመል የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሰረት በማድረግ በየምዕራፉ ይዘቶችን ልየታ በማድረግ የማጠናከሪያ ትምህርት በቋሚ ፕሮግራም እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በእንግሊዘኛ እና በሒሳብ ትምህርቶች በትምህርት ቤቶች መካከል የአተገባበር ሂደቱ ምርጥ ስራዎች እንዲስፋፉ በክ/ከተማ ደረጃ በመዝገበ ብርሃን አንደኛና መካከለኛ ደረጃ የልምድ ልውውጥ መድረክ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

የእንግሊዝኛና ሒሳብ ስትራቴጂ በመተግበሩ ከመጡ ለውጦች መካከል፤ የሂሳብ እና እንግሊዝኛ ስትራቴጂውን ለመምህራን፣ ለወላጅ እና ለተማሪዎች ግንዛቤ በመፍጠር ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ በእንግሊዘኛና በሒሳብ ትምህርቶች የPerformance Placement Test በመስጠት ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ መለየት ተችሏል፡፡ በሂሳብ እና እንግሊዝኛ ትምህርቶች ውጤታማ እና አላማ ተኮር የማጠናከሪያ ትምህርት ወጥ በሆነ ፕሮግራም በየተቋማት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት ከጊዜ ወደ ጊዜ በግብዓት እንዲሟሉ በማድረግ ለተማሪዎች በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት መቻሉ፡፡ በትምህርት ተቋማት ሰኞ ሰኞ ሙሉ ቀን ተግባቦቱን በእንግሊዝኛ ለማድረግ ጅምሮች መኖራቸው፡፡ ወላጆች ባገኙት ግንዛቤ መሰረት ለልጆቻቸው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል መደረጉ እና በገንዘብ ድጋፍ ማድረጋቸው፡፡ የሂሳብ እና እንግሊዝኛ መምህራን ተነሳሽነት መጨመሩ እና መምህራን በቀላሉ ሁሉንም ተማሪዎች መድረስ እና መደገፍ ማስቻሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ራሳቸውን ለማሻሻል የሚያግዛቸውን ግብአቶች እና ቤተ ሙከራዎች ማግኘታቸው ይጠቀሳሉ፡፡

ከባለድርሻ አካላት የሚጠበቁ ተግባራት፤ የእንግሊዝኛና ሒሳብ ስትራቴጂ በጥልቀት በመረዳት ለተቋማት ድጋፍ ማድረግ፤ የማጠናከሪያ ትምህርት በቅርበት መደገፍ፤ ወላጆችን በልጆቻቸው ትምህርት ማሳተፍ እና ጠንካራ የማህበረሰብ ተነሳሽነትን መፍጠር ትምህርት ቤቶች ብቻቸውን ሊሰጡ የማይችሉትን ተጨማሪ ግብዓቶችን እና ድጋፍ መስጠት፤ ባለድርሻ አካላት በጋራ በመስራት ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ወላጆች እና ማህበረሰቡ የላቀ እና ውጤታማ የሆነ የትምህርት ስርዓትን የሚያበረታታ የእርስ በእርስ ትስስር መፍጠር፡፡
ልደታ ፋና፡- ለሰጡን መረጃ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን፡፡
አቶ አሰፋ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የተለያዩ ሃብቶችን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ ወደ ሆኑ የፊዚካልና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶች እና የግንባታ ውጤቶች የሚለውጥና አቅም የሚፈጥር የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዲስትሪ በልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ልዩ ሚና ያለው ኢንዱስትሪ ከመሆኑ አንጻር ቀጥተኛ ያልሆነ ነገር ግን ከፍተኛ ተጽዕኖ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያሳድር ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ዘርፍ ተልዕኮ በመረዳት ለዘርፉ የሚመጥን አመራር መስጠት ወሳኝና ወደ ኃላ ሊባል የማይገባው ተግባር ነው፡፡ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት የኮንስትራክሽን ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ የሚያችሉ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ የልደታ ክ/ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት እየሰራ ያለውን ስራ በማስመልከት የጽ/ቤቱን ኃላፊ አቶ ናርዶስ መንክር ጠይቀን እንዲህ አቅርበነዋል፡፡



**አቶ ናርዶስ መንክር**
**የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**ጽ/ቤቱ እየሰራ ያለውን ስራ በአጭሩ ቢገልፁልን?
**አቶ ናርዶስ፡-**የልደታ ክ/ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት በከተማ አስተዳደሩ የተሰጠውን ተልዕኮ በማሳካት ረገድ ባለፉት ዓመታት በከተማዋ ስር ሰዶ የቆየውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በዘላቂነት በመቅረፍ ፈጣንና ፍትሃዊ ልማት ለማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ግንባታ ያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ጅምር ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ጽ/ቤታችሁ በ2016 በጀት ዓመት የማህበራዊ ተቋማትን፣ዕድሳትና ጥገና ስራዎችን ከመስራት አኳያ የነበረው አፈጻጸም እንዴት ይገልፁታል?
**አቶ ናርዶስ፡-**በ2016 በጀት ዓመት 5 ነባርና 12 አዲስ የማህበራዊ ተቋማት ግንባታ፣ ዕድሳትና ጥገና ስራዎችን በዕቅድ በመያዝ ወደተግባር በመግባት በቁርጠኝነት ለማስፈፀም የተንቀሳቀሰው የልደታ ክ/ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት በዕቅድ ከያዛቸው 5 ነባርና 7 አዲስ በድምሩ 12 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ መቻሉ ተቋሙ የለውጡን እንቅስቃሴ በመቀላቀል ለውጤት የበቃ እንደሆነ ምስክር አያሻውም፡፡ ጽ/ቤቱ ስራዎችን የተሳካ ለማድረግ ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ከማድረግ ጎን ለጎን የተለያዩ ባለሃብቶች እንዲሳተፉ ተ,ደርጓል፡፡




**ልደታ ፋና፡-**በተለያዩ ዘርፎች የነበራችሁን አፈጻጸም ቢገልጹልን
**አቶ ናርዶስ፡-** ጽ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ ከሚያከናውናቸው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት የግንባታና ዕድሳት ስራዎች መካከል ሃገር ተረካቢ ትውልድ ለሚቀረጽበት የትምህርት ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት 7 ያህል የግንባታና ዕድሳት ስራዎችን በማስጀመር በበጀት ዓመቱ 5 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ የቻለ ሲሆን የትምህርት ተቋማቶቻችን ለመማር ማስተማር ስራው ምቹና ማራኪ እንዲሁም በትምህርት ሴክተሩ የተቀመጠውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉ ከማድረግ አንጻር ፋና ወጊ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በጤናው ዘርፍ አንድ ፕሮጀክትን በማጠናቀቅ የጤናው ዘርፍ ለህብረተሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት የተሳካ እንዲሆን ጥረቶችን አድርገናል፡፡ ይህ ተግባር ሲከናወንም የጤና ተቋማትን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ያስቀመጠውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉ ተደርጎ ነው፡፡ በሌሎቹም ዘርፎች ማለትም በስራ ዕድል ፈጠራ ዘርፍ፣ በወጣቶችና ስፖርት መልካም ጅምሮች በቀጣይ ለምናከናውናቸው ተግባራት ስንቅ የሚሆኑ ናቸው፡፡

**ልደታ ፋና፡-**በቀጣይ ስራችሁን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ምን እየሰራችሁ ነው?
**አቶ ናርዶስ፡-**በባለፈው በጀት ዓመት ተጀምረው የተሻገሩ ፕሮጀክቶችንና በ2017 በጀት ዓመት የተቋማትን ፍላጎት መሰረት ተደርጎ በዕቅድ የተያዙ የተለያዩ በየዘርፉ የታቀዱ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው የግንባታ ጊዜ ጥራትና ወጪ በማጠናቀቅ ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ ጥቅም እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በመስተመጨረሻ የሚያተላልፉት መልዕክት ካለ
**አቶ ናርዶስ፡-**እንደልደታ ክፍለ ከተማም ሆነ እንደከተማ አስተዳደሩ በርካታ የኮንስትራክሽን ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡እነዚህን ስራዎች በማሳካት ህብረተሰቡ የሚፈልገውን አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል፡፡ መንግስት በጀት በመመደብና ስራዎችን ክትትል በማድረግ በወቅቱ እንዲጠናቀቁ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህን ስራ በተሻለ መልኩ ለማስቀጠል ባለሃብቶች፣ ማህበረሰቡና ባለድርሻ አካላት ከመንግስት ጋር በመተባበር ሊሰሩ ይገባል የሚል መልዕክት አለኝ፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ለቃለ መጠይቁ አመሰግናለሁ፡፡
**አቶ ናርዶስ፡-**እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## ዘመናዊ የንግድ ስርዓት ለተሻለ እድገት

የልደታ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽ/ቤት በከተማችን ለዘመናት ስር ሰዶ የቆየውን የተዛባ የንግድ ስርዓት፤ስርዓቱ ፍታዊነት እንዲኖረው፤የሸማቹን መብት ለማስጠበቅ፤ መንግስት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በአግባቡ መሰብሰብ እንዲችል በስሩ ያሉ 10 ወረዳዎች በማቀናጀትና በማስተባበር ዘመናዊ የንግድ ስርዓት ለማስፈን በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በንግድ ሰውርዓቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍና ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት በክፍለ ከተማችን ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች አሳታፊ ለማድረግ የተለያዩ መድረኮችንና ስልጠናዎችን መጠቀም የሚያስችል የአሰራር ስልት በዕቅድ በማስቀመጥ በትኩረት እየሰራን እንገኛለን፡፡

ባለፉት ወራች ግብራቸውን ያልከፈሉ ነጋዴዎችን በመከታተል የንግድ ፍቃድ እድሳት እንዲያጠናቅቁ በስፋት ተሰርቷል፡፡ የተረጋጋ የንግድ ስርዓትን ለማስፈን የክትትልና ድጋፍ ስራችን ላይ ከምንግዜውም በላይ ትኩረት በመስጠት አላግባብ ኢፍትሃዊ የዋጋ ጭማሪን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም የእሁድ ገበያ የተጠናከረ እንዲሆን ከመሰራቱም በላይ ምርት በተሻለ ሁኔታ እንዲቀርብ እርብርብ በመደረጉ የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር በሚደረገው ርብርብ አስተዋፅዎ አበርክተናል፡፡ በእነዚህ እና በሌሎች ለግባራት ዙሪያ ከንግድ ጽ/ቤት ሀላፊ ዶ/ር ጥበቡ ደጀኔ ጋር የመጽሔት ዘግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡ መልካም ንባብ



**ዶ/ር ጥበቡ ደጀኔ**
**የንግድ ጽ/ቤት ሃላፊ**

## የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office


**ልደታ ፋና፡-** የንግድ ስርዓቱን ለማዘመን እየተሰሩ ያሉ ተግባራትን ቢገልፁልን

**ዶ/ር ጥበቡ ፡-**በጽ/ቤታችን ከንግድ ስርዓት ጋር ተያይዞ የምርት አቅርቦትን መሰረት በማድረግ የቁጥጥርና ክትትል ስራ በመስራት ችግር ውስጥ የተገኙትን እርምጃ በመውሰድና ወደ ህጋዊነት እንዲመጡ ትኩረት በማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የተሻለ ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡

ተቋሙን ለማዘመን ከንግድ ፈቃድ ጋር ተያይዞ ያሉ አገልገሎቶችን ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ በማድረግ ያለምንም እጅ ንክኪ በኦንላይን እየተሰጠ ሲሆን ይህም በርካታ ጥቅሞች እያስገኘ ይገኛል፡፡ ይህም የነጋዴን ሰዓት መቆጠብ፣ ሌብነትና ብልሹ አሰራር ለመካለከልና የግብዓት ብክነትን መቀነስ አስችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የንግድ ፍቃድ ቁጥጥርና የዋጋ ግሽበቱን ለመቆጣጠር ምን እየተሰራ ነው

**ዶ/ር ጥበቡ፡-** የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን በማሻሻል የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸውን ነጋዴዎች ለመፍጠር በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት 270 ቅድመ የንግድ ስም (ድርጅት ስም) ምዝገባና ማጣሪያ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 39 የንግድ ስም (የድርጅት ስም) ማሻሻያ ማድረግ ተችሏል፡፡





**የእሁድ ገበያ**

የምርት አቅርቦትን በማሳደግ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነትን ማረጋጋት ስራን በትኩረት የተሰራ ሲሆን በዚህም የእሁድ ገበያዎችን ተደራሽነትን በማስፋትና ስታንዳርድ በማስጠበቅ በእሁድ ገበያዎች የምርት አቅርቦት መጠን የማሳደግ ስራ እየተሰራ ያለ ሲሆን በዚህም የተለያዩ ሰብል ምርቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬና ኢንዱስትሪ ምርቶችን በማቅረብ ለህብረተሰቡ በተመጣጠኝ ዋጋ እየቀረበ ገበያን ከማረጋጋጥ አንፃር ከፍተኛ ሚና እየተወጣ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል መንግስት ድጎማ የሚያደርባቸውን ምርቶች በፍትሃዊነት ማቅረብ ስራን በተመለከተ፣ ለህብረተሰቡ የሸማች ማህበራትንና ማኬባን በመጠቀም አቅርቦት መር ስራዎች እየተሰራ ሲሆን እስከአሁን ባለው ለክ/ከተማችን ህብረተሰብ ስኳር፣ ዘይት እና የዳቦ አቅርቦት ስራ ተሰርቷል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-**በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት ነገር ካለ

**ልደታ ፋና ፡-** የንግድ ስርዓቱ የተሻለና ቀልጣፋ እንዲሆን ከነጋዴ ማህበረሰቡና ከነዋሪው ጋር በቅንጅት በመስራት የንግድ ድርጅቶች የበርለበር ክትትልና ቁጥጥር ስራ ህጋዊ የንግድ ስርዓትን ለማረጋገጥ ተሰርቷል ይህን ህጋዊነቱን በማረጋገጥ ህገ-ወጥነትን ለመከላከል ቁጥጥር ማድረግ የተቻለ ሲሆን ችግር ያለባቸውንም እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡ በማለት አስተላልፈዋ፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን

**ዶ/ር ጥበቡ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

## የተሟላ ሪፎርም ለቀልጣፋ አገልግሎት!

በልደታ ክፍለ ከተማ የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ዘመናዊ ለማድረግና ለማሻሻል ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ የክ/ከተማው ፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ፅ/ቤት ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል የአገልግሎት አሰጣጡን የህብረተሰቡን ፍላጎት ያማከለ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ የለውጥ መሳሪያዎችን ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛል፡፡ የለውጥ ስራዎችን አፈፃፀምን ከማጎልበት አኳያ የክትትልና ድጋፍ በስፋት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ተቋማት ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ እና አገልግሎቶች በቅድመ ሁኔታን በማሳወቅ በስታንዳርድ መሰረት አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ሰፊ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በየደረጃው ለሚገኙ ባለሙያዎች እና ቡድን መሪዎችን በፍላጎት ዳሰሳ ጥናት መሰረት በማድረግ ስልጠና በመስጠት የመፈፀም እና የማስፈጸም አቅም ማጎልበት ተችሏል፡፡

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት

## Lideta Sub-City Communication office

ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት ግልጽነት ባለዉ መንገድ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ተቋማት የተሟላ ግብአት እንዲኖራቸውን በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን ምቹ ለማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡ በእነዚህ እና ሌሎች ፅ/ቤቱ በተከናወኑ ተግባራት ዙሪያ ከፅ/ቤቱ ሀላፊ አቶ ጢቂ ድሪባ ጋር የመፅሄት ዝግጅት ክፍላችን ቆይታ አድርጓል፡፡ መልካም ንባብ፡፡



**አቶ ጢቂ ድሪባ**
**የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ ጢቂ ድሪባ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የተቋማት የሪፎርም ስራዎች በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?

**አቶ ጢቂ፡-** የተቋማት የሪፎርም ስራዎች በየምዕራፉ የክትትልና ድጋፍ ቼክ ሊስት ላይ በማካተት ምቹ የተገልጋይ ማረፊያ እንዲዘጋጅ በተከታታይ በቃልና በጽሁፍ ግብረ መልስ መስጠት ተችሏል፡፡ አብዛኞቹ ተቋማት የተገልጋይ ማረፊያ የተዘጋጀላቸው ናቸው፡፡ ለዚህም በክፍለ ከተማ ደረጃ 198 በወረዳ ደረጃ 690 የተገልጋይ ማረፊያ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች እና የአገልግሎት ቅደም ሁኔታዎች በተለያዩ መንገዶች ለተገልጋይ ግልጽ ማድረግ ተችሏል፡፡ በጽ/ቤቱ ዌብ ሳይት፣ ፌስ ቡክ፣ ቴሌግራም፣ ኤልዲ፣ ስቲከር በመለጠፍ፣ በብሮሸር እንዲሁም በተለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ግልጽ ማድረግ ተችሏል፡፡ አገልግሎትን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ ተገልጋዩ ባለበት(ኦንላይን) ተደራሽ የተደረገ አገልግሎት እና የተገኘ ውጤት በዝርዝር ለማስቀመጥ ያህል እንደ ክፍለ ከተማችን አገልግሎት ተገልጋዮች በቀላሉ ባለበት ቦታ አገልግሎት እንዲያገኝ አስችሏል፡፡ በዚህም ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ተችሏል፡፡ የአገልጋዩ ማንነት መለያዎች አቅጣጫ ጠቋሚዎች በአጠቃላይ የ'ሀሁ' ስራዎች አፈጻጸም ያለበት ደረጃ እና ውጤት በተመለከተ በተለይም በባለጉዳይ ቀን ምልከታ በማድረግ የ'ሀሁ' ስራዎች እዲተገበሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለዚህም አብዛኞቹ ነባርና አዳዲስ አመራሮችም ሆኑ ፈጻሚዎች የደረት ባጅ፣ የጠረጴዛ ባጅ እንዲጠቀሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ በክፍለ ከተማ ደረጃ 40 አመራርና 1295 ፈጻሚ በወረዳ ደረጃ 230 አመራርና 3809 ፈፃሚ መጠቀም ችለዋል፡፡ እንዲሁም የጠረጴዛ ባጅ በክፍለ ከተማ ደረጃ 40 አመራርና 1202 ፈጻሚ፤ እና በወረዳ 230 አመራርና 3205 ፈጻሚዎች እንዲኖር ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በክፍለ ከተማ ደረጃ 34 አቅጣጫ ጠቋሚ በወረዳ ደረጃ 230 አቅጣጫ ጠቋሚ ተዘጋጅቷል፡፡

እንዲሁም የስም ስያሜና ቁጥር በክፍለ ከተማ ደረጃ 33 በወረዳ ደረጃ 230 እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተገልጋዮች የአገልግሎት ተደራሽነት ለማረጋገጥ በአማራጭነት ተግባራዊ ተደረገበት ሁኔታ በተመለከተ በክፍለ ከተማ ደረጃ ህንጻው ሊፍት በመጠቀም አገልገሎት እንዲያገኙ ማድረግ እና በወረዳ ደረጃ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አካላት በየወረዳው እንዳይቸገሩ ፎቅ ላይ ያሉ ጽ/ቤቶች ምድር ላይ እንዲሆኑ በማድረግ አመራሩም ሆነ ፈጻሚዎች አገልግሎት መስጠት መቻላቸውን በክትትልና ድጋፍ ወቅት ማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለ1,300 ሰራተኞች በሪፎርም እና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተደጋጋሚ ስልጠና መስጠት ችለናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የሚሰጡ አገልግሎቶች እና የተገልጋዩ የእርካታ መጠን ሚዛን በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

**አቶ ጢቂ፡-** በባለጉዳይ ቀን ረቡዕ እና ዓርብ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን በተለየ መልኩ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ ይገኛል በዚህም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለዉጥ እየመጣ ይገኛል፡፡ በክ/ከተማ እንዲሁም በ10ሩም ወረዳ ኮሙኒኬሽን እና ፐብሊክ ሰርቪስ ፅ/ቤት በጋራ በመሆን ተገልጋይ የሚበዛባቸው ተቋማት ላይ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በመምረጥ 'የእንጠያየቅ' መድረክ በማዘጋጀት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የአገልገሎት አሰጣጥ ችግሮችን የማዳመጥና በመንግስት የተሰሩ ስራዎችን ሪፖርት በማቅረብ ለቀጣይ አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት ግብዓት ማግኘት ተችሏል፡፡ የተገልጋይ ህብረተሰብ እርካታ ሊለካ የሚያስችል የተሰራ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በሁሉም ወረዳዎችና ክ/ከተማ አገልግሎት በሚበዛባቸው ጽ/ቤቶች 553 ተገልጋይ መረጃ በመሰብሰብ የተገልጋይ እርካታ ጥናት የተሰራ ሲሆን የአገልግሎት እርካታ ውጤት 70% መሆኑን ያሳያል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለአስተዳደሩ ሰራተኞች ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር የተሰሩ ስራዎች ካሉ ቢገለፅ?

**አቶ ጢቂ፡-** ለአስተዳደሩ ሰራተኞች ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር በክፍለ ከተማ ደረጃ 1 የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣1 የህጻናት ማቆያ 60 ህጻናት የሚጠቀሙበት፣1 የሽማቾች ሱቅ 1,298 ሰራተኞች የሚጠቀሙበት፣ እንዲሁም የምድረ ግቢውን ውበት እንዲኖረው እና ፅዳቱን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በወረዳ ደረጃ 9 የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣ 10 የህጻናት ማቆያ 57 ህጻናት የሚጠቀሙበት፣ 10 የሸማቾች ሱቅ 3,809 ሰራተኞች የሚጠቀሙበት ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም በክ/ከተማ ደረጃ የስፖርት ጂም፣ በክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት በልዩ ሁኔታ ባለሙያ በመመደብና ቦታ በማዘጋጀት ለሰራተኞች የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ክፍል አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ሌብነት፤ ብልሹ አሰራር እና የስነ-ምግባር ችግሮች ከማረምና እርምጃ ከመውሰድ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ቢገልፁልን?
**አቶ ጢቂ፡-** የሌብነትና ብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመፍታት ምንጮችን በመለየት የማክሰሚያ እቅድ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ የሌብነትና ብልሹ አሰራር ለመቀነስ እና ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ የስራ ክፍሎች ላይ የአሰራር ስርዓት ለማሻሻል ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከሌብነት እና ብልሹ አሰራር ጋር ተያይዞ ተጠያቂነት ከማስፈን አንፃር የተለያዩ ጥቆማዎች የሚቀርብበት ስርዓት ተዘርግቶ ጅምር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህም በመነሳት በክፍለ ከተማችን በየደረጃው በመመሪያ መሰረት ሃላፊነታቸው በአግባቡ መወጣት ያልቻሉ 20 የክፍለ ከተማ ፈጻሚዎች እንዲሁም በወረዳ ደረጃ 7 አመራር እና 191 ፈጻሚዎች በድምሩ በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ 218 አመራርና ፈፃሚ ተጠያቂ በማድረግ በየደረጃው እርምጃ የመውሰድ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የሚሰጡ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ምን ተሰርቷል?
**አቶ ጢቂ፡-** አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ለህብረተሰቡ የተሻሻለ እና የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ነባር የለሙና አዲስ የለሙ ቴክኖሎጂዎች በባለሙያ ደሰሳ ጥናት በመስራት ያለባቸውን ችግር መፍታት ተችሏል፡፡ አገልግሎት አሰጣጡ ለተጠቃሚው ስራን ያፋጥናሉ ተብለው የለሙ ቴክኖሎጂዎች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ እና ምን ውጤት እንዳመጡ 'ምን ይቀራል?' የሚለውን ዳሰሳ በማድረግ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብና ለአገልግሎት ምቹ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ተሰርተል፡፡ ሁሉም ተቋማት ከየራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው የለሙ እና መልማት ያለባቸውን ቴክኖሎጂዎች ለይተው መስራት፤ በተቋሙ ያሉ ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ በስራ ላይ እየዋሉ ስለመሆኑ እና ሌሎች ለተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ ተለይተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ፣ በሁሉም ደረጃ ዳሰሳ ጥናት ተሰርቷል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ከመፅሔት ዝግጅት ክፍላችን ጋር ለነበርዎት ቆይታ እናመሰግናለን፡፡
**አቶ ጢቂ ድሪባ:-** እኔም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## በጎነት እና የልማት አርበኝነት

በልደታ ክ/ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በከተማ አስተዳደሩ የተሰጠውን ተልዕኮ በማሰካት ረገድ ባለፉት ዓመታት በከተማዋ ስር ሰዶ የቆየውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በዘላቂነት በመቅረፍ ፈጣንና ፍትሃዊ ልማት ለማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል አደረጃጀታዊ መዋቅር በአዲስ መልክ ተቋቁሞ ወደ ስራ ተገብቷል፡ ፡ ስለሆነም ዘርፉ የተቋቋመበትን ዓላማና የተሰጠውን ተልዕኮ እውን ለማድረግ፤ በየጊዜው የአሰራር ዘዴውን እየፈተሸ ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል አደረጃጀት፣አሰራር እንዲሁም በከተማዉ የሚሰጠውን አግልግሎት በግልጽነት፣በተጠያቂነት እና በፍትሃዊነት መርህ መሠረት እንዲያገኝ ማድረግ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ በመሆኑ፤ህብረተሰቡ በሚኖርበት ብሎክ ያሉትን ችግሮች እንዲለዩ በማድረግና በመፍታት የመንግስት መዋቅሩን በመደገፍ እንዲሁም ችግሮችን በጋራ እንዲፈታ ነጻና ግልጽ በሆነ መልኩ ማሳተፍ ለሁለተናዊ ለውጥ ወሳኝ በመሆኑ መንግስት ሕዝቡን በየደረጃው በማሳተፍ፤ የህዝቡንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ እንዳለበት በመደንገጉና ይህን ተግባራዊ የማድረግ ሕገ-መንግስታዊ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ነዋሪዎች ስለከተማዉ የሚወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት፣ሀሳብና ጥያቄ የማቅረብ መብታቸዉን እንዲጠቀሙ የብሎክ መዋቅሩን ከማደራጀትና የተሰሩ የሰላምና ፀጥታ ፣የበጎ ፍቃድ ፣ የልማት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች ላይ ያለዉን የተግባር እንቅስቃሴ የሚያሳይ አጭር ቃለ ምልልስ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ እንግዳው ጓዴ ጋር ቆይታ አድርገናል መልካም ንባብ

**ልደታ ፋና፡-** አቶ እንግዳው ጓዴ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ጽ/ቤት ኃላፊ ለቃለ መጠይቅ ስለተባበሩን በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን
**አቶ እንግዳው:-** እኔም መረጃ እንዳካፍል ስለጋበዛቹህኝ አመሰግናለሁ

**ልደታ ፋና፡-** የተቋሙ ዋና ምሰሶ ምንድን ነው?
**አቶ እንግዳው፡-**በከተማው አስተዳደሩ ብሎክን ማዕከል ያደረገ የአግልግሎት አሰጣጥ፣ የመሠረተ ልማት፣ የፀጥታ ችግሮችን እና የበጎ ፈቃድ ተግባራት ፍላጎትን በመለየት የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት ችግሮችን ከምንጫቸው እንዲፈቱ በማድረግ የህብረተሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡



**አቶ እንግዳው ጓዴ**
**የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ**

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
## Lideta Sub-City Communication office

**ልደታ ፋና፡-** የህብረተሰቡን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ባህል ለማጎልበት ምን ተሰራ?

**አቶ እንግዳው፡-** በበጎ ፈቃድ ፅንሰ ሃሳብ እና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራ አመራር ዙሪያ ለበጎ ፈቃደኞች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር መፍጠር ተችሏል።

**ልደታ ፋና ፡-**በበጎ ፍቃድ ስራዎች የማህበረሰቡ ተሳትፎ ምን ይመስላል?

**አቶ እንግዳው፡-**አሳታፊ የበጎ ፈቃድ መርሀ-ግብሮችን በመቅረፅ ማህበረሰቡ በበጎ ፍቃድ ተግባራት ተሳትፎ እንዲያደርግ አስችለናል፡ ፡ በዚህም በአረንጓዴ ልማት፣በደም ልገሳ፣ በማጠናከሪያ ትምህርት እና የአጫጭር የክህሎት ስልጠና መርሃ-ግብር፣አካባቢን በማጽዳትና የጎርፍ ስጋትን በመከላከል፣በማዕድ ማጋራና በመንገድ ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።















Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
## Lideta Sub-City Communication office







**ልደታ ፋና፡-** ያላቸውን ሙያ ተጠቅመው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታዎች የተፈጠረላቸው በጎ ፍቃደኞች አሉ ወይ ?

**አቶ እንግዳው፡-** «ሙያዬን ለሀገሬ» የሙያ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ፕሮግራም ተቀርጾ  በጎ ፍቃደኛ የሆኑ የህክምና ባለሙያዎች፣ ኢንጅነሮች፣ አርቲስቶች፣ የህግ ባለሙያዎች፣ መምህራን፤ የመከላከያ አባላት፣ የሀይማኖት መሪዎችና የማህበረሰብ አንቂዎች በሙያቸው አገልግሎት እንዲሰጡ  ማድረግ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በጎ ፍቃደኞች የተሳተፉባቸው ሌሎች ዘርፎች ካሉ ቢያብራሩልን?

**አቶ እንግዳው፡-** በክፍለ ከተማው በጎ ፍቃደኞች በሰፊው የተሳተፉበት ስራ ማዕድ ማጋራት ሲሆን በዚህም በቀን አንዴ እንኳን በልተው ማደር የማይችሉ ዜጎችን መመገብና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን ፡፡
**አቶ እንግዳው፡-**  እኔም አመሰግናለው፡፡

### ቀልጣፋ አገልግሎት በዘመናዊ አሰራር

የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ቤት ነው፡፡የልደታ ክ/ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነት መነሻ በማድረግ የቤቶችን መረጃ በዘመናዊ መልኩ በማደራጀት ፍትሃዊና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃዎችን በማደራጀት ፈጣንና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በመስራት የነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት ርብርብ አድርጓል፡፡በመሆኑም ቤቶችን በአሰራሩና በመመሪያው በማስተዳደር የነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለመመለስ የተከናወኑ ስራዎች በምን አግባብ እየተከናወኑ እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን ከቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ ደምስ በየነ ጋር ቆይታ አድርጓል መልካም ንባብ፡፡



**አቶ ደምስ በየነ**
**የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ**

## የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

ልደታ ፋና የ2017 ዓ.ም የመጀመሪያ 6 ወር ዕትም

**ልደታ ፋና ፡-** ቤቶችን በፍትሃዊነት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ከማስተላለፍ አንፃር የተከናወነ ተግባር ካለ ቢብራራ ?

**አቶ ደምስ በየነ ፡-** ቤቶችን በፍትሃዊ መንገድ ከማስተላለፍ አንፃር እንደሚታወቀው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 140/2015 ላይ በዝርዝር ባስቀመጠው መሰረት የመንግስት ቤት እንዴት እንደሚተላለፍ ተቀምጧል። በመመሪያው 9/3 ላይ የድሃ ድሃ (ዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ) ላይ ላሉ አካላት ቤት ይተላለፋል ይላል ይህም 10 ላይ ባስቀመጠው መሰረት በቀጠና ደረጃ ባመቻቸው የድሃ ድሃ ልየታ ኮሚቴ መሰረት ከታች ከብሎክ ተለይቶ በወረዳ ካቢኔ ተተችቶና ፀድቆ የሚመጣውን የክ/ከተማው ካቢኔ ሲያፀድቅ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ (የደሀ ደሀ) ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ቤቶች ይተላለፋሉ፡፡በዚህ መሰረት 59 ቤቶች ለልማት ተነሺዎችና 36 ቤቶች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የክ/ከተማችን ነዋሪዎች የቤት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና ፡-** በህገ ወጥ መንገድ የተያዙ ቤቶችን ከማስለቀቅ አንፃር የተከናወኑ ተግባራት ቢገለፅ ?

**አቶ ደምስ በየነ፡-** በህገወጥ መንገድ የተያዙ ቤቶችን ከማስለቀቅ አንፃር በክ/ከተማችን በ3ኛ ወገን በህገወጥ መንገድ የተያዙ ቤቶችን በተደራጀው የቤቶች ግብረ ሀይል 228 ቤቶችን ለማስለቀቅ ታቅዶ 228 ቤቶችን የማስለቀቅ ስራ ተሰርቷል አፈፃፀሙ 100% ነው። ይህን ተግባር ይበልጥ አጠናክረን እንቀጥላለን።

**ልደታ ፋና ፡-** የመንግስት ቤቶችን በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ከማስተዳደር አንፃር ምን እየተሰራ ነው ?

**አቶ ደምስ በየነ፡-** የልደታ ክ/ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት በአዋጅ 74/2014 ከተቋቋመ ጀምሮ የተለያዩ ተግባራት እየሰራ የሚገኝ ጽ/ቤት ነው። በመሆኑም መረጃ በዘመናዊ መልኩ በማደራጀት ፍትሃዊና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ በከተማ አስተዳደሩ በለማው ሶፍትዌር ላይ መረጃ የማስገባት ስራ የተጀመረ ሲሆን በክ/ከተማአችን ከምናስተዳድረው የመንግስት 21,613 ቤቶች 100% ወደ መረጃ ቋት የገባ ሲሆን የእነዚህ ቤቶች ተጨማሪ መረጃ ስካን በማድረግ 18738 ቤቶች መረጃ የማያያዝ ስራ የተሰራ ሲሆን በቅርቡ ሶፍትዌሩ ላይ ሁሉም የቤቶች መረጃ በማያያዝ የኦንላየን አገልግሎት የምንጀምር ይሆናል።

**ልደታ ፋና ፡-** የቤቶች ኪራይ ገቢ አሰባሰብ በምን አግባብ እየተከናወነ ነው ?

**አቶ ደምስ በየነ፡-** ከመንግስት የቀበሌ መኖሪያ ቤቶች የኪራይ ገቢ መሰብሰብን በተመለከተ በዚህ በጀት አመት 6,250.000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 16,507,108 ብር መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 264.11% ነው። ከመንግስት የቀበሌ ንግድ ቤቶች ኪራይ ገቢ 30,325,000 ብር ለመሰብሰብ በእቅድ ተይዞ 41,664,730 ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ 137.39% ነው። በአጠቃላይ በዚህ በጀት አመት 36,575.000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 58,171,838 ብር መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 159% ነው። ከመንግስት መኖሪያና ንግድ ቤቶች ዕድሳት ጋር በተያያዘ 18,226 መኖሪያ ቤቶችን የኪራይ ውል ለማደስ ታቅዶ 15,328 ቤቶች የኪራይ ውል ማደስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 84.9% ነው።1,875 የመንግስት ንግድ ቤቶች የኪራይ ውል ለማደስ ታቅዶ 1,555 የንግድ ቤቶችን የኪራይ ውል ማደስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 82.93% ነው።

**ልደታ ፋና ፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**አቶ ደምስ በየነ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

### ውጤታማ የፋይናንስ አሰራር ትግበራ!

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት የህዝብና የመንግስት ሃብት እንዳይባክን፣የሀብት ክፍፍሉ ፍትሃዊ እንዲሆን እና ከብልሹ አሰራር የፀዳ የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖር ለማስቻል በትኩረት እየሰራ ይገኛል። ጽ/ቤቱ የህዝብና የመንግስት ሀብት ለታለመለት ዓላማ ብቻና ብቻ እንዲውል ለማስቻል የተለያዩ አሰራሮችን ቀይሶ እየሰራ ውጤት እያስመዘገበ ነው። እኛም በዚህ ጽሁፍ የክፍለ ከተማችንን የፋይናንስ አሰራርን በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጡን ከፋይናንስ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሓዱሽ ሓጎስ ጋር ቆይታ አድርገናልና ተከታተሉን መልካም ቆይታ ።

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመሪያ አቶ ሓዱሽ ለቃለ-ምልልስ ፈቃደኛ ስለሆኑልን እናመሰግናለን።

**አቶ ሓዱሽ፡-** እኔም ማብራሪያ እንድሰጥ ስለጋበዛቹህኝ በጣም አመሰግናለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** የመንግስትና የህዝብ ሃብት እንዳይባክን ለማስቻል የተሰራ የግንዘቤ ማስጨበጥ ስራ ካለ ቢያብራሩልን?

**አቶ ሓዱሽ፡-**የፋይናስ አሰራርን እንዲሁም የመንግስትና የህዝብ ሀብት ፍትሀዊ አጠቃቀምን አስመልክቶ ለአመራሮች፣ለባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት በተለያዩ የፋይናንስ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ዙሪያ ተከታታይነት ያላቸው የግንዘቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እና የአመለካከት ቀረጻ ስራ ተሰርቷ።

**ልደታ ፋና፡-** ፍትሃዊ የፋይናንስ ስርዓትን ከመዘርጋት አንፃር የተሰራ ስራ ካለ ቢያብራሩልን ?

**አቶ ሓዱሽ፡-** ተቋማት የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን በእቅዳቸው መሰረት ስለመጠቀማቸው ለማረጋገጥ በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል ክፍተቶች ካሉም በፍጥነት የማረም ስራ ይከናወናል። የተቋማት የፋይናስ አሰራር ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ስርዓትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን በትኩረት ተሰርቷል በዚህም ውስንየሆነው የህዝብና የመንግስት ሀብት ከብክነት የጸዳ እንዲሆን ተደርጓል



Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

## ፅዱ አከባቢ ለዘመናዊ አኗኗር

የልደታ ክ/ከተማ ፅዳት አስተዳደር ፅ/ቤት በ2016 ዓ/ም ከ11ዱ ክ/ከተሞች የላቀ አፈፃፀም ውጤት በማምጣቱ እውቅናና ሽልማት አግኝቷል። የከተማው ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በክ/ከተማችን የተሻለ ውጤት ለነበረውና 1ኛ ደረጃ ይዞ ላጠናቀቀው ወረዳ 2 ልዩ ልዩ ግብዓቶች በሽልማት ተበርክቶለታል። ክ/ከተማው ደግሞ በ2ኛ ደረጃ በማጠናቀቁ የላቀ አፈፃፀም ሽልማት፤ ሙሉ ዴስክቶፕ ከነአክሰሰሪው ተሸላሚ አድርጎታል። ይህንንም መነሻ በማድረግ በ2017 ዓ/ም ከክ/ከተማ እስከ ከወረዳ በየደረጃው ያለውን ባለድርሻ አካላት በማስተባበር እና በመነቃቃት ለላቀ ስራ ወደ ተግባር አስገብቷል። ፅ/ቤቱ የንቅናቄ ስራዎችን በተለያዩ ጊዜ የሚተገብር ከመሆኑ አንፃር የጳጉሜ 5 ቀናትን፤ የአዲስ አመት መለወጫ ቀን፤ የመስቀል ደመራን፤ የመዉሊድን እና የእሬቻ በዓልን መነሻ በማድረግ ሰፋፊ ንቅናቄዎችን አካሂዷል። እንዲሁም የብልፅግና ፓርቲ የተመሠረተበትን 5ኛ ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ የ7 ቀናት ደማቅ የፅዳት ሳምንት በ10ሩም ወረዳዎች በተሻለ ደረጃ በንቅናቄ ማስፈፀም ተችሏል። እነዚህን ተግባራት እና ያስመዘገበውን የላቀ አፈፃፀም በተመለከተ ከፅ/ቤቱ ሀላፊ አቶ በፍቃዱ ሀይሌ ጋር የመፅሄት ክፍላችን ቆይታ አድርጋለች፡ ፡ መልካም ንባብ።



**አቶ ሓዱሽ ሓጎስ**
**የፋይናንስ ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የውስጥ ገቢ አሰባስብ ላይ የተሰራ ስራ ካለ ቢጠቅሱልን?
**አቶ ሓዱሽ፡-** ውጤታማና በወቅቱ ገቢ የመሰብሰብ ስራ ከማከናወን ተግባር ጋር በተያያዘ በዚህ በጀት ዓመት በከፍተኛ ደረጃ እቅዳችንን አስፍተን ያቀድን ሲሆን ያለፉት ወራት የገቢ አሰባሰብ ተግባራችን ውጤታማ ነበረ ለዚህም የባለድርሻ አካላት ሚና ከፍተኛ ነው። በዚህ አጋጣሚ ክፍለ ከተማችን በገቢ አሰባሰብ ባለፉት ዓመታት ከፍተኛና ከሁሉም ክፍለ ከተሞች ቀዳሚ ነበረ ይህንን ውጤት አጠናክረን ለመሄድ እየሰራን እንገኛለን።

**ልደታ ፋና፡-** የግዥ ስርአቱ ከብልሹ አሰራር የጸዳ እንዲሆን ምን ተሰራ?
**አቶ ሓዱሽ፡-**አብዛኛው የግዥ ስርዓታችን ግልፅ ጨረታን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ተሰርቷል። የጨረታና የጥራት ኮሚቲዎች ተከታታይ የሆነ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። ጥራቱን የጠበቀና ወቅቱን የጠበቀ የግዥ ስርአት እንዲኖርም ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** የኦዲት ግኝትን ለማስመለስ የተሰሩ ስራዎች ካሉ ቢያብርሩልን?
**አቶ ሓዱሽ፡-** ቀዳሚ ስራችን የኦዲት ክፍተቶች እንዳይኖሩ በትኩረት መስራት ነው አጋጣሚ ሆኖ የኢዲት ክፍተቶች ከተከሰቱ ክፍተቱን በአሰራር የማረጋገጥ ስራ ከሰራን በኃላ ክፍተቱን ለማረም በቅንጅት እንሰራለን እስከሁንም ለውጥ አምጥተናል ሊባክን የነበረ የህዝምና የመንግስት ንብረትን አስመልሰናል በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል።
**ልደታ ፋና፡-**ለነበርን ቆይታ በድጋሚ በዝግጅት ክፍላችን ስም አመሰግናለሁ።
**አቶ ሓዱሽ፡-** እኔም ለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለው።




**አቶ በፍቃዱ ሀይሌ**
**የፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** ለቃለ-መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ በቅድሚያ እናመሰግናለን።
**አቶ በፍቃዱ ሀይሌ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ በፅ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** ፅዳትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ለመፍጠር የተሰሩ ስራዎች ምንድናቸው?
**አቶ በፍቃዱ-** በየወረዳዎች ብሎኮች ከ184 በላይ ባሉ በግንዛቤ ባለሙያዎች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያና በሳምንታዊ ጽዳት ዘመቻ ዙሪያ የበር ለበር ግንዛቤ ስራ በየቀኑ ነዋሪዎችን ተደራሽ የማድረግ ስራ ይሰራል። ልዩ ልዩ በራሪ ጹሁፎችን በማዘጋጀት በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ስራ ተሰርቷል። በየሳምንቱ አርብ በት/ት ቤቶች፣ በተቋማቶች እና ቅዳሜ በየወረዳ የመኖሪያ ብሎኮች እንዲሁም በዋና አንድ ማዕከሎች ሰፊ የጽዳት ዘመቻ ንቅናቄ በማድረግ ማህበረሰብ መር ጽዳትና ጽዳት ባህሉ የሆነ ህብረተሰብ ለመፍጠር በስፋት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት

## Lideta Sub-City Communication office

**ልደታ ፋና፡-** ምን ያህል ሞዴል መንደሮች አሉ? ሞዴል ያሰኛቸው ተግባር ምንድነው?

**አቶ በፍቃዱ፡-** በ2016 ዓ.ም ሰፊ በከተማ ደረጃ ግንባር ቀደም ለከተማው ሞዴል የሚባሉ የሞዴል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በመሆኑም በ2017 ዓ.ም 45 ሞዴል ብሎኮችን፤ 20 ሞዴል ት/ት ቤቶችን፤ 3 ስማርት /ምርጥ/ ወረዳ፤ 3 ሞዴል የወረዳ አስተዳደሮችን፤ 3 ሞዴል የሀይማኖት ተቋማቶችን የመፍጠር /የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡ 2000-3000 የሚደርሱ ሞዴል ቤተሰብ በክፍለ ከተማ ደረጃ የማብቃት/የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡ በአጠቃላይ የባለፈውን ዓመት በከተማ ደረጃ የተገኘውን ውጤት በማስቀጠል እነዚህን የሞዴል ስራዎች በመስራት ላይ እንገኛለን፡፡ የሞዴል ስራዎች መመዘኛ መስፈርት በተመለከተ በከተማ ደረጃ ራሱን የቻለ 11 ክፍለ ከተሞችን የሚያወዳድር መመዘኛ መስፈርት ከተማው አዘጋጅቷል፡፡










**ልደታ ፋና፡-** ቆሻሻን ከምንጩ መለየትና ማስወገድ ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል ?

**አቶ በፍቃዱ፡-** በልደታ ክፍለ ከተማ በ10ሩም ወረዳዎች 324 ብሎኮች ደረቅ ቆሻሻን በአይነት (የሚበሰብስና የማይበሰብስ) በመለየት በተዘጋጁ እቃዎች ተለይተው እንዲቀመጡና ለሽርክና ማህበራትና ለግል ድርጅቶች የማስረከብ ስራዉን በትኩረት ተፈጻሚ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመቀነስ ተግባርን ግንዛቤ በመስጠት የሚበሰብሱ ደረቅ ቆሻሻዎችን ቤት ለቤት ቀልዝ ስራ በማዋል ወደ ረጲ የሚጓጓዥ ደረቅ ቆሻሻን መጠን መቀነስ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ነዋሪ ማህበረሰብ እና ተከራይ ማህበረሰቡን ደረቅ ቆሻሻ በአይነት የመለየት እና ከምንጩ የመቀነስ ዓላማን በማስገንዘብ በሩብ ዓመቱ ካሉን 40,000 እማ ወራ አባ ወራ መካከል ከ34,649 እማ ወራ አባ ወራ 92% ነዋሪዎች ደረቅ ቆሻሻን በአይነት የመለየት ደረጃ ተደርሷል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ላይ የተሰሩ ስራዎች ካሉ ቢያብራሩልን?

**አቶ በፍቃዱ፡-** በክፍለ ከተማችን ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 1,643.22% ቶን ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ማዋል ተችሏል፡፡ ይህም 28,987,724.3 ብር ማህበራት ማግኘት አስችዋል፡፡ በ3 ወራት 724 ቶን የፕላስቲክ ጠርሙስ እና ፌስታል በተገቢው መንገድ ተለይቶ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውል ተደርገዋል፡፡ 326.26 ቶን ማይካ፤ ጀሪካን፤ ባልዲ፤ ማዳበሪያ፤ የሻምፖ ደረቅ ቆሻሻዎችን በተገቢው መንገድ ተለይቶ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውል ተደርገዋል፡፡



Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office

193.09 ቶን ወረቀትና ካርቶን በተገቢው መንገድ ተለይቶ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውል ተደርገዋል። በሁሉም የጽዳት ሽርክና ማህበራት እና የመልሶ መጠቀም ማህበራት ወቅቱን የዋጀ አስተማማኝ የገበያ ትስስር በመፍጠር 28,987,724.3 ብር ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ ተችለዋል። በተጨማሪም ከተማችን ልታጣ የነበረውን 241,997.90 የአሜሪካን ዶላር ማትረፍ ተችለዋል።

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን።

**አቶ በፍቃዱ ሀይሌ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## የበለፀገች ኢትዮጵያ ተረካቢዎች

ሁሉም ህጻናት በህይወት የመኖር፣ወላጆቻቸዉን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸዉን ሰዎች የማወቅና የእነርሱንም እንክብካቤ የማግኘት መብቶች አሏቸዉ። ጉልበታቸዉን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣በትምህርት፣በጤናቸዉና በደህንነታቸዉ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ስራዎች እንዲሰሩ ያለመገደድ ወይም ከመስራት የመጠበቅ እና በትምህርት ቤቶች ወይም በህጻናት ማሳደጊያ ተቋሞች ዉስጥ በአካላቸዉ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነጻ የመሆን መብቶች አሏቸዉ።

ነገር ግን ከጊዜ ጊዜ እየባሰ የመጣዉና የህጻናት ስነ-ልቦና ላይ ትልቅ ተጽእኖ እየፈጠረ የመጣዉ የህጻናት የጉልበት ብዝበዛ መበራከት ነዉ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በየጊዜዉ አዳዲስ ደንቦች፣ ጥናቶችና የእርምት እርምጃ እየወሰዱ ቢገኙም አሁንም ችግሩ እንዳለ ነዉ።

በህጻናት ላይ የሚደርሱ የጉልበት ብዝበዛዎች የምንላቸዉ የህጻናት ንግድ እና ህገ ወጥ ዝዉዉር፣ህጻናትን በእዳ እና በግዴታ አገልጋይነት መያዝ፣እንዲሁም ህጻናትን በኃይል በማስገደድ ወይም ግዴታን ለማሟላት የጉልበት ስራ ማሰራት እና ለጦርነት ዓላማ መመልመልና ባርነት ላይ ማዋል ሲሆኑ እነዚህን አስከፊ የሆኑ የህጻናት ጉልበት ስራን በተመለከተ በዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት የወጣ ስምምነት ቁጥር 182/1999፣አንቀጽ 3 ላይ በዝርዝር አስቀምጦታል። እንደ ሀገራችንም የህጻናት መብት እንዲከበርና ከጥቃት ነጻ ሆነዉ በእድሜያቸዉ ልክ ማድረግ ያለባቸዉን ተግባር እንዲያከናዉኑም በባለቤትነት ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ዋነኛ ተጠቃሽ የሆነዉ የሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ሲሆን ተግባሩን ከፋፍሎ ከከተማ እስከ ወረዳ ተቋም በማቋቋም በትኩረት እየሰራ ይገኛል።

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

በዛሬዉ የልደታ ፋና የመጽሄት አምድም በህጻናት ጉልበት ብዝበዛ እንዲሁም ህጻናት መብታቸዉና ደህንነታቸዉ እንዲጠበቅ ከማን ምን ይጠበቃል በሚለዉ ዙሪያ ከልደታ ክፍለ ከተማ ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ ከሆኑት ከወ/ሮ ሄለን መሀመድ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገናል እንድትከታተሉን ጋበዝናችሁ መልካም ንባብ!



**ወ/ሮ ሄለን መሀመድ**
**የሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ በህጻናት መብትና ጥበቃ ዙሪያ ምን እየሰራ ይገኛል?

**ወ/ሮ ሄለን፡-** የልደታ ክፍለ ከተማ ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ጽ/ቤት የሴቶችን፣የህጻናት መብትና ጥበቃ፣ የአካል ጉዳተኛ እና የአረጋዊያንን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በባለቤትነት ይዞ እየሰራ ያለ ተቋም መሆኑ ይታወቃል። ከተጠቀሱት መካከልም በጥያቄሽ ያነሳሽዉን የህጻናት መብትና ጥበቃ እንዲሁም ጉልበት ብዝበዛ በተመከለተ ሲሆን የህጻናትን ጉዳይ በተመለከተ ሃገራችን በዓለም ዓቀፍ ስምምነትና በአፍርካ ቻርተር ፈርማ የተቀበለችዉን ኃላፊነትና ግዴታን እንዲሁም በሀገራችን ህገ-መንግስት አንቀጽ 36 ላይ የህጻናትን መብት አስመልክቶ የሰፈረዉን ህገ-መንግስታዊ ሃላፊነትን ለመተግበር እየሰራች ያለች መሆኗ ይታወቃል።

የህጻናት ጉዳይ የሁሉም አካላት ጉዳይ ስለሆነም የሚመለከተዉን አካል ሁሉ በማሳተፍ የሚሰራ ስራ ነዉ።ከዚህ አንጻር የህጻናትን መብት ከማስጠበቅ ጋር ተያይዞ እንደ ክፍለ ከተማዉ ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ጽ/ቤት ተጨባጭ ዉጤት የተመዘገበባቸዉን ስራዎች መስራት ችለናል። ከሰራናቸዉ ስራዎች መካከልም፡-

ህጻናት ላይ ጉዳት ሳይደርስ አስቀድመን የህጻናትን መብት በማስመልከት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ከሚመለከተዉ የማህበረሰብ ክፍል ጋር የሰራን ሲሆን ለአብነት ያህልም ከሃይማኖት መሪዎች ጋር፣ ከሲአርሲ ኮሚቴ ጋር እንዲሁም ከእድር ምክርቤት ጋር በመተባበር በአካባቢያቸዉ ለሚያገኟቸዉ ማህበረሰቦች የህጻናትን ጥቃት ለመከላከል እና ጥቃት ሲፈጸምባቸዉ ካዩም ጥቆማ እንዲሰጡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ሰርተናል ተግባሩ አሁንም እንደቀጠለ ነዉ።

ሌላዉ በየትምህርት ቤቱ ጥቃት እንዳይፈጸም ከእያንዳንዱ ተግባር ጋር በማያያዝ የህጻናት መብት መርሆዎችን ትኩረት በማድረግ ግንዛቤ እናስጨብጣለን። በጎጂ ልምዳዊ ድርጊት ዙሪያ ለት/ቤት ማህበረሰብ፣ ለተማሪዎች ግንዛቤ የማስጨበጥና በተጨማሪም ጥቃት ሲፈጸም ለማን ማመልከት እንደሚገባቸዉ እንዲሁም ወደሚመለከተዉ የህግ እና የስነ- ልቦና አማካሪ ተቋማት ስልክ እንዲደዉሉም ስልክ ቁጥር እያሳወቅናቸዉ እንገኛለን ።

የህጻናት ፓርላማም በየት/ቤቱ ህጻናት ላይ በሚደርሰዉ ጥቃት ዙሪያ እንዲሰሩና መብታቸዉ እንዲከበር በማድረጉ ረገድም ዉጤታማ ስራ እየሰራን እንገኛለን ።

**ልደታ ፋና፡-** እንደ ክፍለ ከተማችን ያሉ ህፃናት የጉልበት ብዝበዛ እንዳይፈፀምባቸው ከማድረግ አንጻር ምን ተሰርቷል?

**ወ/ሮ ሄለን፡-** የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ አንዱ የመብት ጥሰት እንደመሆኑ መጠን አላግባብ በጉልበት ብዝበዛ የሚጠቃ ህጻን ካለ እና ለኢኮኖሚ ችግር የተጋለጡ ህጻናት በእኛም ተቋም ሆነ በሌላ መንገድ ካሉ መጀመሪያ ህጻናቱን የማዳን፣በስነ-ልቦና የማጠንከር ስራ እየሰራን ሲሆን ችግሩን በሚፈጥሩ አካላት ላይም ከግንዛቤ በተጨማሪ ከተግባሩ ሳይታረሙ ሲቀሩ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ከህግ አካላት ጋር ተቀናጅተን እየሰራን ነዉ። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን የመስራት አቅም ካላቸዉ እድሜያቸዉ ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ በተወሱ ስራዎች ላይ ተሳትፈዉ ራሳቸዉን የማስተዳደር መብት እንዳላቸዉ በአዋጅ 11/56/2015 መጠቀሱን ግን መዘንጋት የለብንም።

**ልደታ ፋና፡-** ህፃናቱ ላልተገባ የጉልበት ብዝበዛ የሚገቡት በምን ምክንያት ነዉ?

**ወ/ሮ ሄለን፡-**ህጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ የሚያጋልጣቸዉ ዋነኛዉና የሁሉም ዜጋ ችግር የሆነዉ የኢኮኖሚ ችግር፣ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪ መኖር፣ግንዛቤና እዉቀት ትምህርት አለመማር፣ የህግ ከለላ ማጣት እንዲሁም የስረዓተ ጾታ አመለካካት መዛባት ፣ማህበራዊና ባህላዊ ደንቦች እና የመሳሰሉት ናቸዉ።

**ልደታ ፋና:-** ድርጊቱ ከተፈጸመ ወይም ሲፈጸም ከተስተዋለስ ቅድሚያ የሚወሰደዉ እርምጃ ምንድነዉ?

**ወ/ሮ ሄለን፡-** ለእዚህ ድርጊት ተጋልጠዉ ከተገኙ በመጀመሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል። ለዚህ ያጋለጣቸዉን ምክንያት በመለየት በማህበረሰቡ እንዲቀረፍላቸዉ የማድረግ ስራ እየሰራን እንገኛለን፡፡ በተጨማሪም አሰሪዉን አካል ከግንዛቤ በተጨማሪ በህግ ተጠያቂ እንዲሆን የማድረግ ስራ እንሰራለን።

**ልደታ ፋና፡-** ህፃናቱን ከጉልበት ብዝበዛ በማዉጣትና በእድሜያቸዉ ወደ ት/ቤት እንዲገቡ እንዲሁም በኢኮኖሚ እንዲደገፉ ለማስቻል የተሰራ ስራ አለ?

**ወ/ሮ ሄለን፡-** አንድ ህጻን ተወልዶ እድሜዉ ለት/ት እንደደረሰ ወደ ት/ቤት የመሄድና የመማር መብት እንዳለዉ ይታወቃል ።ይህንን ደግሞ በግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለማህበረሰቡ የማሳወቅ ስራ እንሰራለን፡፡ ለምሳሌ፡-አንድ ህጻን ተወልዶ በ90 ቀን ዉስጥ ተመዝግቦ የልደት ሰርቴፊከት ማግኘት እንዳለበት ሁሉ እድሜዉ ለት/ት እንደደረሰ ት/ት የመማር እና የመሳሳሉትን መብቶች እንዳሉት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንሰራለን። በተጨማሪም በባለቤትነት ተቆጥሮ ከተሰጠዉ አካል ጋር በትስስር እንሰራለን ።

**ልደታ ፋና፡-** ህፃናት መብታቸዉ ተጠብቆ በስነ--ልቦና፣ በአካልና፣ በሞራል እንዲጠበቁ ከባለድርሻ አካላት ምን ይጠበቃል?

**ወ/ሮ ሄለን፡-** ከባለድርሻ አካላት ጋር ትስስር ፈጥረን የህጻናትን ደህንነት እንዲጠበቅና የኢኮኖሚ ችግሮቻቸዉን ለመቅረፍ ከመንግስት ሰራተኞች ከደመወዛቸዉ 1% ተቆራጭ በማድረግ እንዲደገፉና እንዲያስተምሩ፣በዓላት ምክንያት በማድረግ ለበዓል መዋያ ግብአት እና የት/ት ቁሳቁስ እንዲደግፉአቸው ብሎም 42 ህጻናት በየወሩ ከተለያዩ የክፍለ ከተማዉ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፣ አሁንም ግን ይሄ በቂ ነዉ ተብሎ ስለማይታመን ከተቋማችን ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት የተለመደና ጠንካራ ትብብራቸዉን ቢያስቀጥሉ አመራሩም ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት እንዲያስተባብር እና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ርብርብ በማድረግ የነገ ሀገር ተረካቢዎችን ማሳደግና ማብቃት እንዲሁም ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በአብሮነት መስራት ይጠበቅባቸዋል።

**ልደታ ፋና፡-** አጠቃላይ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጠዎት

**ወ/ሮ ሄለን፡-**እንደሚታዉቅ ጽ/ቤታችን ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚፈታ ተቋም ነዉ። ታዲያ እነዚህን ጉዳዮች ሲፈታ ብቻዉን እንዳልሆነ ይታወቃል። የብዙ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ቅንጅትና ትብብር ኖሮበት ነዉ የሚሰራዉ ስለዚህ እንደ ክፍለ ከተማችን በሴቶችም ሆነ በህጻናት እንዲሁም በአረጋዉያንና በአካል ጉዳተኞች የሚገጥሙንን ማንኛዉም ተግዳሮቶች ለመፍታት አሁንም ኑ አብረን እንስራ ህፃናትንም ከሚደርስባቸዉ ማንኛዉም ጥቃት እንታደጋቸዉ የሚል መልዕክት አስተላልፋለሁ።

**ልደታ ፋና ፡-** ለነበርን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን ።

**ወ/ሮ ሄለን ፡-** እኔም አመሰግናለሁ ።

## በስዕብና የተገነባ ትውልድ ለሀገር ዕድገት

የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ለወጣቶች በፈጠራቸው የሥራ ዕድሎች በድጋፍ ማእቀፍ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት በተለይም በእግር ኳስ አሰልጣኝነት፤ተጫዋችነት፤በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ጥበቃና ጽዳት እንዲሁም በስፖርት ነክ ንግድ ቤቶች ዘርፎች ግንባር ቀደም ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑና የወጣቶች የስነ-ተዋልዶና የኤች አይ ቪ ኤድስ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት ፤ወጣቶችን በተለያዩ ወቅታዊና ወጣት ተኮር በሆነ ርዕስ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና በበጎ ፈቃድ ሥራዎች በንቃት እንዲሳተፉ ተደርጓል።

በመሆኑም በጽ/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራትን ለእናንተ ለአንባብያን ለማቅረብ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ ክብራለም ደምሴ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡

**የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት**
Lideta Sub-City Communication office



**አቶ ክብረዓለም ደምሴ**
**የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የወጣቶችን ኢኮኖሚያው ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተሰሩ ስራዎችን ይግለጹልን?

**አቶ ክብረዓለም፡-** በጽ/ቤታችን የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በርካታ ስራዎችን ያከናወኝን ሲሆን በየደረጃው ባሉ የወጣት ማህበራት ተሳታፊ በማድረግና ወጣቶች ሁለንተናዊ ስብእናቸው እንዲጎለብት በክፍለ ከተማው ዘርፍም ማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ፕሮግራምን በመተግበር፣ በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በባለሃብቱ ሁለት የተግባረ-ዕድ እና አትሌት ሴንተር በደረጃው በመገንባትና በማስፋፋት፤የስፖርት ማህበራትን በማደራጀት ኅብረተሰቡን በተለይም ወጣቱን በስልጠና በስፖርት አበረታች ቅመሞች ስልጠና ስፖርተኞችና ለታዳጊዎችና አሰልጣኞች ስልጠና በስፖርት የህክምና ሙያ ማሻሻያ ስልጠና ባለሙያዎች ሰጥተናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ስልጠናዎችን በእቅድ በመመራት ምን ያህል ወጣቶችን አሳትፋችኋል?

**አቶ ክብረዓለም፡-** አቅደን ወደ ስራ የገባን ሲሆን በክረምት መርሃ ግብር በመንግስት ድጋፍ የታዳጊ ስፖርት ስልጠና ፕሮጀክት ፕሮግራም ስልጠና እቅድ ለ5,835 ታዳጊ በ69 ጣቢያዎች በታዳጊ ስፖርት ስልጠና ፕሮጀክት ፕሮግራም በክረምት በመንግስት ፤በግለሰብና በክለብ ድጋፍ የሰሩ የብቃት ምዘና ለ456 ታዳጊዎች አሰልጥነናል፡፡ እንዲሁም ኤሊት ስፖርተኞች ማፍራት እቅድ 16 ክንውን 28 አፈፃፀም በፌዴራል ማረሚያ ቦክስ ክለብ፣በአካዳሚና በኤሌክትሪክ ቢ ቡድን በእግርኳስ ስፖርት አስመርጠናል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** በጽ/ቤቱ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ያለው ቁርጠኝነት እንዴት ይገለጻል?

**አቶ ክብረዓለም፡-** መንግስት የወጣቶችን እና የስፖርትን ጉዳይ እንደ ዋና የልማት አጀንዳ በመያዝ የህብረተሰቡን ሁለንተናዊ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በክፍለ ከተማው ብሎም በወረዳዎች በተደረገው ሁሉን አቀፍ ጥረት ወጣቶችን ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር የተመዘገበው ውጤት የፈጠራቸው አዳዲስ ፍላጎቶች የወጣቶችን ዘርፈ ብዙና አንገብጋቢ ችግሮች በሚፈለገው ደረጃ መፍታት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ወጣቶች በአደረጃጀቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ የተሰሩ ስራዎችን ይግለጹልን?

**አቶ ክብረዓለም፡-** የአካባቢው ህብረተሰብና ወጣቱ በሀገር ገጽታ ግንባታ፣ በስፖርት ተሳትፎና መዝናኛ በስልጠና ህብረተሰቡን በጤና ስፖርት ውድድር፤የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ውድድር በአካል ጉዳተኞችና መስማት የተሳናቸው ስፖርት ውድድር በማሳተፍ እንዲሁም በሁለንተናዊ ልማት በሚፈለገው ደረጃ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም የስፖርት ኮሚቴዎችንና ባለድርሻ አካላትን በአግባቡ መምራት፣ መከታተል እና በመደገፍ ክፍለ ከተማችንን በአሁኑ ሰዓት እየተገበረችው ያለውን የለውጥ ጉዞ ከማሳካት አንፃር ወጣቱ እያበረከተ ያለውን ጉልህ አስተዋጽኦ የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል፣ የህብረተሰቡ በስፖርት እና በመዝናኛ ፕሮግራሞች የመሳተፍና የማዘውተር ፍላጎቱ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ይህን ፍላጎት በየደረጃ ለማርካት የሚያስችል ደንበኛ ተኮር አደረጃጀት በመፍጠር አሁን የተጀመረውን እንቅስቃሴ ከክፍለ ከተማ አልፎ በከተማው አቀፍ፣ ደረጃ እውቅና እንዲኖረው ማደረግ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ህብረተሰቡን ለማነቃቃትና ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ ለመፍጠር የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ ክብረዓለም፡-** ማህበረሰቡ በስፖርት ጤናውን እንዲጠብቅ ማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ከማስፋፋት ህብረተሰቡን በሚኖሩበት በሚሰሩበት እና በሚማሩበት ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡የስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራዎችን ተደራሽ ከማድረግ፣ ከታችኛው ዕድሜ እርከን ጀምሮ ዘመናዊ ስልጠናን ከመስጠት፣ የስፖርት ማህበራት በገቢ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ከማድረግ እና ባለሀብቱ በስፖርት መሰረተ ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ አሰራሮች በመዘርጋት በሚፈለገው መልኩ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልክት ካለ

**አቶ ክብረዓለም፡-** በዚህም በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዙሪያ በተከናወኑ ተግባራት በርካታ ውጤቶችና በቀጣይ ለሚከናወኑ ተግባራት አጋዥ የሚሆኑ መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋፋት፣ የታዩ የአደረጃጀትና የአሰራር ማነቆዎችን በመለየት፣ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት እንዲያስችል የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ከወትሮ በበለጠ አበክሮ በመስራት ላይ ይገኛል ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ ክብረዓለም፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

## የአረንጓዴ አሻራ ተምሳሌት

ከተማችን አዲስ አበባ የኢንባሲዎች መቀመጫ ከመሆኗም በላይ በርካታ ዲፕሎማቶች የሚኖሩባት ትልቅ ከተማ ነች።የዲፕሎማቶች መኖሪያ እንደመሆኗ መጠን በከተማዋ ያሉ ቦታዎች ሳቢና ማራኪ ንጽህናቸው የተጠበቁ ሊሆኑ ይገባል።ይህን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ከተማ አስተዳደሩ የከተማውን ነዋሪዎች በማስተባበር በኮሪደር ልማት የከተማዋን ገጽታ ውብ ዕይታን ለማላበስ እየሰራ ይገኛል።

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደርም የከተማ አስተዳደሩ የያዘውን ከተማውን የማስዋብ ሂደት ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። የክፍለ ከተማውን ውበት በመጠበቅ ሳቢና ማራኪ እንዲሆን ለማድረግ የክፍለ ከተማውን ነዋሪዎችና ባለድርሻ አካላት እያሳተፈ ይገኛል።

ጽ/ቤቱ የመንገድ አካፋዮች፣አደባባዮች፣ ፓርኮች እንዲሁም የወንዝ ዳርቻዎች ላይ የአረንጓዴ ልማት ውጤታማ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በስራውም የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች፣መስሪያ ቤቶችና ባለሃብቶች ተሳታፊ ሆነዋል።

በመሆኑም በከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት የተከናወኑ ስራዎች የጽ/ቤቱን ኃላፊ ወ/ሮ ሄለን ጥበቡ ጠይቀን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።



**ወ/ሮ ሄለን ጥበቡ**
**የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**ጽ/ቤታችሁ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል?
**ወ/ሮ ሄለን፡-** ጽ/ቤታችን የከተማ ውበትና አረንጋዴ ልማት እንደመሆኑ መጠን ክፍለ ከተማችንን ሳቢና ማራኪ የሚያደርጉ ስራዎችን በመስራት ለመኖሪያ ምቹ አካባቢ እንዲፈጠር የመንገድ አካፋዮች፣ አደባባዮች፣የወንዝ ዳርቻ ቦታችን የማልማት የማፅዳትና የመንከባከብ፣ በክረምት የተተከሉ ችግኞችን የመንከባከብና የማስዋብ ተግባራትን የማከናወን ስራ ሰርተናል።

**ልደታ ፋና፡-**ክ/ከተማውን ውብና ፅዱ ለማድረግ አደባባዮችና የመንገድ ዳርቻዎች ላይ የተሰሩ ስራዎች ምን ምን ናቸው?
**ወ/ሮ ሄለን ፡-**በክፍለ ከተማችን የሚገኙ አደባባዮችና የመንገድ ዳርቻዎች በኮሪደር ልማቱን መሰረት ሳቢ እንዲሆኑ ለማድረግ በጽ/ቤታችንና በሌሎች ተቋማት ትብብር የአረንጓዴ ልማት ስራዎች ተሰርተዋል።የአረንጓዴ ልማት ስራዎች ባለሃብቶች፣ የተደራጁ ማህበራትና የክ/ከተማውን ነዋሪዎች በማስተባበር አዲስ እይታ እንዲኖረው የማድረግ ስራ ሰርተናል።





**ልደታ ፋና፡-**ፓርኮችን ከማስዋብ አንጻር የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?
**ወ/ሮ ሄለን፡-**በክፍለ ከተማችን የአረንጓዴ ልማት ከተከናወኑባቸው ቦታዎች ውስጥ ፓርኮችን የማስዋብ ስራ ይገኝበታል። በፓርኮች ውስጥ ማህበራት ገብተው እንዲሰሩ በማድረግ አትክልት የማልማትና የመንከባከብና ከማሳመር በተጨማሪ ለወጣቶች የስራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ዕድል ፈጥሯል።

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
## Lideta Sub-City Communication office

**ልደታ ፋና፡-** አረንጓዴ አሻራ ችግኝ ከመትከልና ከመንከባከብ ጋር በተያያዘ የሰራችሁት ተግባር እንዴት ይገለጻል?

**ወ/ሮ ሄለን፡-** መንግስት በሀገራችን ያለውን የአየር ንብረት መዛባት ለመከላከል ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ዘርፎች መካከል ችግኞችን መትከልና መንከባከብ ነው።ጽ/ቤታችንም ይህን ኃላፊነት በመውሰድ ችግኞችን የመትከልና የመንከባከብ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል።በጽ/ቤታችን አስተባባሪነት 849,811 ችግኞችን የክ/ከተማችንን ነዋሪዎችና ባለድርሻ አካላት በማስተባበር የመትከልና የመንከባከብ ስራዎችን ሰርተናል። ከህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት በተጨማሪ የአረንጓዴ ልማት ቦታዎችን በተደራጁ ማህበራት ዘላቂነት ባለው መልኩ የእንክብካቤ ስራዎችን እንዲሰሩ ተደርጓል።





**ልደታ ፋና፡-**በቀጣይ ከምሰሩት ስራዎች ጋር ያለዎት መልዕክት

**ወ/ሮ ሄለን፡-** ጽ/ቤታችን ክፍለ ከተማችንን ውብና ማራኪ ሆና ለነዋሪዎች ለመኖሪያ ምቾ እንድትሆን የሚያደርጉ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ እንሰራለን።የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎችም በከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስራዎች ላይ በመሳተፍ የመኖሪያ አካባቢያቸው ሳቢና ማራኪ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል።በአጠቃላይ የአካባቢያችንን ውበት በመጠበቅ በኩል የሁሉንም የክፍለ ከተማችንን ነዋሪዎች ተሳትፎ የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑ ሁሉም የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች በሚችሉት መልኩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪየን አቀርባለሁ።

**ልደታ ፋና፡-**ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ሄለን፡-**እኔም አመሰግናለሁ።

## መስሪያ ቦታዎች ለልማት



**ወ/ሮ ሸጉ ተሰማ**
**የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ**

በክ/ከተማችን የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግና ለማረጋገጥ ከጥቃቅን ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ኢንደስትሪዎችን በመደገፍ ዘርፉ ስራ ለሌላቸው ወጣቶችና ሴቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የስራ ስምሪት እንዲሳለጥና የኢንዱስትሪ ሰላም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መንግስታዊ ድጋፍችን ማለትም የመስሪያ ቦታዎች ገንብቶ በማስተላለፍ በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካትና ወደ ውጪም ምርቶቻቸውን በመላክ ለኢኮኖሚው እድገት አስተዋፅኦ ከማበርከታቸውም በላይ ገበያውን የማረጋጋትና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ሂደት ውስጥ አይነተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።

የመስሪያ ቦታዎችን በማልማት እና በማስተላለፍ በክፍለ ከተማው በሚገኙ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪዎች በመስሪያ ቦታ ዙሪያ የሚታየው የመስሪያ ቦታ ችግር መቅረፍ ለከተማዋ ልማት፣እድገትና ብልጽግና ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡ ፡ በመሆኑም እስከ አሁን በተለይ በአዲሱ ሪፎርም መሠረት በአዲስ መልክ የተዋቀረው የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጄንሲ በ2016 በጀት የነበረው አፈፃፀም መነሻ በማድረግ በ2017 ሊከናወኑ በሚችሉ 4 ግቦች እና 27 ዓላማዎች ጽ/ቤት አሁን ባለው የሰው ኃይል ዓቅምን መሠረት ያደረገ የጽ/ቤት መገልገያዎች እና ግብዓት በመጠቀም ዕቅዱ እንዲሳካ በማድረግ በዘርፉ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተደራጁ የህብረተሰባችን ክፍሎች ከመጥቀሙም ባሻገር በከተማዋ ለተጀመረው የልማት ስራ፣ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት የበኩሉን ሚና ይጫወታል።

በአጠቃላይ በ2017 በጀት ዓመት ከላይ የተጠቀሱት ግቦች፣ዓላማዎች እና ተግባራት በዕቅዱ በተቀመጠው መሠረት በወቅቱ እንዲከናወኑ በማድረግ ኢንተርፕራይዞች እና አምራች ኢንዱስትሪዎች በሃገራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ ሚናቸውን በላቀ ደረጃ የሚጫወቱበት ሁኔታ እንዲኖር በማድረግ የከተማውን ነዋሪ የኑሮ ውድነት ማቃለል ሚናቸውን እንዲያሳድጉ ይደረጋል። ለዕቅዱ መሳካትም በአዲሱ አደረጃጀት ቀደም ሲል የነበሩትን የአሰራር ማነቆዎች በመፍታት እና የመልካም አስተዳደር ስራዎችን በማረጋገጥ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት የምንሰጥበት ሆኖ ለዚሁም የዘመናዊ ቴክኖሎጅ አጠቃቀምን በማሳደግ የአመራር እና የሰራተኛን የመፈፀም አቅም በማጎልበት በፈፃሚው እና በአመራሩ የተሻለ ተነሳሽነት በመፍጠር፣በቡድን የመስራት ባህል በማጎልበት እና ውጤታማነት የሚረጋገጥበት የተደራጀ አመራር የሚሰጥበት ይሆናል።

### የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት የሚገባው ቅድመ ሁኔታ

•የታደሰ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪነት መታወቂያ ፤የስራ ፈላጊ መታወቂያ፤በስልጠና ያለፋበት ሰርተፍኬት ፤የሙያ ምዘና ሰርተፍኬት፤የወረዳ ኘሮሰስ ካውንስል ቃለ ጉባኤ ፤የአዋጭነት ጥናት ፤የመንደር እና የቀጠና ኮሜቴ ቃለ ጉባኤ፤ለተከታታ 30 ቀናት ስራ አጥ ስለመሆኑ ማስታወቂያ የተለጠፈ መሆኑን የሚያሳይ ደብዳቤ

የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ከተቋቋመበት አላማ አንዱ የሆነው ተግባሩ ለተጠቃሚ ዜጐች የመስሪያ ቦታ ማስተላለፍ ሲሆን በ2017 በጀት አመት ለአዲስ ኢንተርኘራይዞች የተላለፈ የመስሪያ ቦታ በኢንተርኘራይዝ 75 ፤በአንቀሳቃሽ 175፤በካሬ ሜትር 1238.5 ሲሆን ተደራጅተው መስፈርቱን አሟልተው ለመጡ ኢንተርኘራይዞች የሚተላለፍ ክፍት ቦታ በካሬ ሜትር

1/ ህንፃ G+4 ማምረቻ **3206.07** ካ/ሜ
2/ ሼድ **1685** ካ/ሜ
3/ ወርክሸኘ **235** ካ/ሜ
4/ ሱቅ/ኮንቴነር **324.5** ካ/ሜ

### ኢንዱስትሪ ለሀገር እድገት

መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ እንደጀመረ ይታወቃል። በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪ ልማቱን በማፋጠን ለአገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ለስራ ዕድል ፈጠራና ለኤክስፖርት ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋፆኦ በመረዳት የዘርፉን ልማት ለማፋጠን ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡ ፡ከተማ የሚታየውን ድህነትና ስራ አጥነት ለመቀነስ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የተደራጁ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ የኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ሽግግር ማረጋገጥ፣ ገቢ ምርቶችን በሀገር ምርት በመተካትና ኤክስፖርት የማድርግ አቅም በማሳደግ ሀገራችን ኢትዮጵያ የበለፀገችና ለዜጎች የምትመቸ ሀገር እንድትሆን የተጠናከረ ስራ እየተሰራ ይገኛል። በመሆኑም የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የተከናወኑ ስራዎች በምን አግባብ እየተከናወኑ እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን የልደታ ክ/ከተማ ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ አበበ ዱላ ጋር ቆይታ አድርጓል መልካም ቆይታ።



**አቶ አበበ ዱላ**
**የኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**ጽ/ቤታችሁ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል?
**አቶ አበበ፡-** በጽ/ቤታችን የሚከናወኑ ተግባራት አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመሳሪያ ሊዝ አቅርቦት ተጠቃሚ ማድረግ፣ኢንዱስትሪ አክስቴንሽን ድጋፍ መስጠት፣ /BDS/ ድጋፍ ማድረግ፣ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የማሸጋገር ስራ መስራት፣ተኪ ምርቶችን እንዲያመርቱ ማድረግ፤ምርታቸውን ወደ ውጪ እንዲልኩ ማድረግ፣ብድር የማመቻቸትና ማስመለስና ቁጠባ፣ የደረጃ ዕድገት ዕድሳት፣የሒሳብ አያያዝ ድጋፍ፣ የካይዘን ፍልስፍና ስልጠናና የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው የማድረግ ስራዎችን ሰርተናል።

**ልደታ ፋና፡-** የአረንጓዴ ኢንዱስትሪ ልማትና ኢነርጂ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ቢገልፁልኝ?
**አቶ አበበ፡-** አካባቢ ጥበቃና ኢነርጂ አጠቃቀም ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠኛ ተሰጥቷል።የዘመናዊና ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡ ፡ በጥናት የተለየ የገበያ ትስስር ፍላጎት በማድረግ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች 6,314,593 ብር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል። አምራች ኢንዱስትሪዎች ኤክስፖርት ያደረጉና ተኪ ምርት እንዲያመርቱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። ለአምራች ኢንዱስትሪዎች 4,300,000 ብር ብድር ማመቻቸትና ለ25 ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ዕድገት ዕድሳት የሰጠ ሲሆን በቀጣይም አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

**ልደታ ፋና፡-** ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ
**አቶ አበበ፡-** በመጨረሻም አምራች ኢንዱስትሪዎች ያለባቸው መሰረት ልማት ፤የገበያ ትስስርና የግብዓት አቅርቦት ችግር በመፍታት ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን፡፡
**አቶ አበበ፡-**እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## ምግቤን ከደጃፌ

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት እንደ ጽ/ቤት ከተቋቋመ በኋላ የከተማው አስተዳደር ለአርሶ አደርና ለከተማ ግብርና ልዩ ትኩረት በመስጠቱ ተጠቃሚዎች ከቤተሰብ ፍጆታ ማምርት አልፎ ተርፎም ለገብያ ማዋል እንደሚቻል በሌማት ቱሩፋት መርሃ-ግብር በ2017 ዓ.ም ነዋሪዎች በእጽዋትና እንስሳት እርባታ ዘርፍ ወደ ስራ ለማስገባት በዕቅድ ተይዞ በርካታ የክፍለ ከተማችን ኑዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ማህረሰባችን ቀደም ሲል የነበረው አመለካከት ተቀይሮ ክፍት የሆነ ቦታ እየጠቆሙ ጭምር ቢሰራበት የሚል ጥያቄ እያቀረበ ይገኛል፡፡ ከሁሉም በላይ “የይቻላል” መንፈስ መፍጠር ተችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት እንደ ልደታ ክፍለ ከተማ በሁሉም ወረዳዎቻችን በጓሮ አትክልት፤ በእንስሳት ዘርፍ፤ በወተት ላም እርባታ እና በእንቁላል ጣይ ዶሮ ሞዴል የሆኑ ሲሆኑ ከራሳቸው አልፈው ለገብያ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ የመፅሔት ዝግጅት ክፍላችን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ከፅ/ቤቱ ሀላፊ ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡ መልካም ንባብ፡፡



**ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው**
**የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** ለቃለ-መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡
**ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የሌማት ትሩፋት ስራዎች አሁን ላይ ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል? ውጤቱን እንዴት ይገልፁታል?
**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** እንደ ልደታ ክ/ከተማ በከተማ ግብርና እና በሌማት ትሩፋት ስራ አዲስ ተሳታፊዎችን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር በቤተሰብ ፍጆታ 2,210 ዜጎቻችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በሆልቲካልቸር ልማት ዘርፍ ነባር ተጠቃሚና ተሳታፊ የሆኑትን 33,874 ተጠቃሚዎችን ማስቀጠል ተችሏል፡፡ በዚህም በስራ እድል ፈጠራ 25 ተጠቃሚዎችን የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ተጠናክሮ በቀጠለው የሌማት ትሩፋት ስራችን በአመቱ አጋማሽ 603 ቶን ምርት ማግኘት ተችሏል፡፡ በከተማ ግብርና ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍላችን የአትክልት ዘር አቅርቦት 37 ኪግ፤ የአትክልት ችግኝ አቅርቦት ደግሞ 18,662 ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የግብርና ምርቶችን ከግል ፍጆታ ባለፈ ለገበያ እንዲቀርብ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች ካሉ ቢገልፁልን?
**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ስራችን በተጨባጭ ገብያ በማረጋጋት ውስጥ ጉልህ ሚና አለው፡፡ በአሁኑ ሰዓት የእንቁላል ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡ በክ/ከተማችን ያሉ የከተማ ግብርና ተጠቃሚዎች ከቤተሰብ ፍጆታ አለፈው ገብያውን የማረጋጋት ስራ በደንብ እየተወጡ ይገኛል፡፡ ይህ ተግባር እንዲቀጥል የሁላችንም ርብርብ ክትትል መጠናከር አለበት፡፡ የከተማ ግብርና ስራችን ውጤታማ እንዲሆን እና እንዲቀጥል በየወረዳው ከቤተሰብ ፍጆታ ያለፈ ምርት የሚያመርቱ አካላትን የገብያ ችግር እንዳይገጥማቸው በወረዳው የሰንደይ ማርኬት(የእሁድ ገብያ) እንዲሳተፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በከተማ ግብርና ተሰማርተው ለሚገኙ ግለሰቦች እና ማህበራት የድጋፍ አግባባችሁ ምን ይመስላል?
**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** በከተማ ግብርና ተሰማርተው ለሚገኙ ግለሰቦችና እና ማህበራት የድጋፍና ክትትል አግባባችን በተመለከተ የክትትልና ድጋፍ ኮሚቴ በማዋቀር ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ለአስሩም ወረዳዎች ባለሙያዎችን በመደብ በሳምንት ሁለት ግዜ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በየወሩ በክትትልና ድጋፍ የተገኙ ውጤቶችን በመገምገም እስካሁን እየተሰራ ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን፡፡
**ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## የህዝብ እና የመንግስት ሀብት ጠበቃ

የልደታ ክ/ከተማ ፍትህ ፅ/ቤት ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል የክ/ከተማው ማህበረሰብ እንዲሁም የአስተዳደሩ ፅ/ቤቶች በህግ ንቃተ ህሊና ዙሪያ፤ የህግ ምክር ድጋፍ እና በፍትህ ብሄር ክርክር የህዝብና መንግስት ሀብት ጥቅም ማስጠበቅ ሲሆን ህግን ጠንቅቆ አለማወቅ ሊያስከትል ከሚችል ጉዳት ማህበረሰቡን እና አስተዳደሩን ለመጠበቅ በህግ አግባብ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም በርካታ ሀብትና ንብረት አለአግባብ እንዳይባክን ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህን አስመልክቶ ከፅ/ቤት ሀላፊው አቶ ጋሻዬነህ ታፈሰ ጋር የመፅሔት ዝግጅት ክፍላችን ቆይታ አድርጋለች፡፡ መልካም ንባብ፡፡

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

ልደታ ፋና የ2017 ዓ.ም የመጀመሪያ 6 ወር ዕትም



## አቶ ጋሻየነህ ታፈሰ
## የፍትህ ጽ/ቤት ሀላፊ

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለቃለ-መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ ጋሻዬነህ ታፈሰ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ በፅ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የህዝብና የመንግስት ጥቅሞችን ከማስከበር አኳያ የተሰሩ ስራዎች ቢገልፁልን?

**አቶ ጋሻዬነህ፡-** የህዝብና የመንግስት ጥቅምን ከማስከበር አንፃር 133 መዝገቦች ከባለፈው በጀት አመት የዞሩ እንዲሁም 32 መዝገቦች አዲስ የመጡ ሲሆኑ በአጠቃላይ 165 መዝገቦች በተለያዩ ፍ/ቤቶች ክርክር ስናደርግባቸው የቆየን ሲሆን ከእነዚህ መዝገቦች ውስጥ 29 መዝገቦች ላይ ውሣኔ ያረፈ ሲሆን 28 ለመንግስት ተወስኗል:: 1 መዝገብ ደግሞ በመንግስት ላይ ተወስኗል፡፡ በመንግስት ላይ የተወሠነው መዝገብ በቀጣይነት ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ብናቀርበው የሚያዋጣ ባለመሆኑ በፓናል ተወያይተን እንዲዘጋ ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ ለመንግስት እንዲወሰን የማድረግ ንፅፅሩ 97.6%ነው፡፡ በአጠቃላይ ቀሪ 136 መዝገቦች ደግሞ በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በችሎት ክርክር ላይ ተገኝቶ በቂ ማስረጃ አቅርቦ ከመከራከር አንፃር የሚስተዋለው ክፍተቶችን ለማረም ምን ተሰርቷል?

**አቶ ጋሻዬነህ፡-** በፍትሐ-ብሄር ጉዳዮች ላይ ክርክር እንድናደርግባቸው በሚል ወደ ጽ/ቤታችን የሚልኩ ባለድርሻ አካላት ሲከሰሱ ሆነ ሲከሡ ተገቢ መልስ ለመስጠት እንድንችልና የመንግስት ጥቅም በተገቢው ለማስከበር ወሳኝ ማስረጃዎችን እንዲልኩልን በተዘጋጁት የጋራ መድረኮች ላይ የመወያየት ስራ ተሠርቷል፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ሠፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሠርተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ባለድርሻ አካላት ከበፊቱ በተሻለ ጥራቱን የጠበቀ እና ጊዜው ከግምት ውስጥ ያስገባ ማስረጃ እየላኩልን ይገኛሉ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በህግ ንቃተ-ህሊና ዙሪያ ግንዛቤ ከማስረፅ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ቢያብራሩልን?

**አቶ ጋሻዬነህ፡-** የማህበረሰቡን እንዲሁም በተለያዩ መስክ የተሰማሩትን ባለሞያዎች በሚሰሩት ስራዎች እንዲሁም የህግ ንቃተ ህሊናቸውን ለማዳበር የተለያዩ የህግ ግንዛቤ ማስጨበጫ በዋነኛነት የተለያዩ የንቃተ ህግ ግንዛቤ መፍጠሪያ የሚሆኑ ርዕሶችን በመለየት የግንዛቤ ስራ ተሰርቷል፡፡ ወቅቱን ያማከለ የህግ ግንዛቤ መሰረት በማድረግ በብሮሸር፤ በሰሌዳ መፅሄት፡ በራዲዮ እንዲሁም በቴሌቪዥን እና በአዲስ ልሳን ጋዜጣ የህግ አምድ በማውጣት ለክ/ከተማው እና ለከተማ አስተዳደሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ሲሆን በተጨማሪም የህግ ንቃተ ህሊናን በማሳደግ ደረጃ በተለያየ ጊዜ መጠይቆችን በመበተን እና ማህበረሰቡ ሊያውቀው ይገባል ተብሎ የሚታሰበውን የህግ ጉዳዮች የማስጨበጥ ስራ ሰርተናል፡፡ በመንግስት ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 56/2010 ላይ፤ የቤት አከራይ ተከራይ አዋጅ 1320/2016 አዋጅን እና ሌሎችም ተጨባጭ ብዙ የሚባሉ የህግ ግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በማዘጋጀት በተለይ የህግ ንቃተ ህሊና የማሳደግ ስራ ሰርተናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የህግ ምክር ድጋፍ ስራ ያለበት ደረጃ ቢገልፁልን?

**አቶ ጋሻዬነህ፡-** በጽ/ቤታችን ከህግ ማስረፅ ስራ በተጨማሪም በማንኛውም ጊዜ የህግ ምክር ድጋፍ ፈልገው የሚመጡ ሰዎችን በማስተናገድ እና ነፃ የህግ ምክር ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን የህግ ምክር ድጋፍ የሚሰጠው በሁለት አይነት መንገዶች ሲሆን ይህንንም በቃል እና በፅሁፍ የህግ ምክር አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ በቃል የሚሰጠው የህግ ምክር አገልግሎት በጽ/ቤታችን የሚመጡትን ተገልጋዮች የሚጠይቋጠን የህግ ምክር በመለየትና እና ምን ማድረግ እንዳለባቸው የህግ ምክር እንሰጣለን፡፡ በፅሁፍ የህግ ምክር አገልግሎት እንዲሁም የተለያዩ የክስ፡ የይግባኝ እንዲሁም የማመልከቻ አይነቶችን በመፃፍ እና የተፃፈውን በመገምገም እና ተያይዞ የቀረበውን ሰነድ በመመልከት የህግ ምክር የምንሰጥበት መንገድ ነው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን፡፡

**አቶ ጋሻዬነህ ታፈሰ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

### የሰላም ዋጋው ስንት ነው!

የልደታ ክፍለከተማ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ፅ/ቤት የተሰጠዉ ተለልዕኮ "የተቀናጀ የፀጥታ ጉዳዮች አስተዳደር ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ በወንጀል፣ በትራፊክ አደጋ እና በደንብ መተላለፍ ላይ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ በሀይማኖትና እምነት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበርን እንዲሰፍን ለማድረግ የህገ-መንግስቱ መርሆዎች መሰረት ባደረገው መልኩ ከሀይማኖት ተቋማትና ተከታዮቻቸው ጋር በጋራ በመስራት፤ የመረጃ ስርዐታችንን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ነዋሪውን ማህብረሰብና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ሰላሟ ፤ፀጥታና ደህንነቷ የተጠበቀ፣ ህግና ስርዓት የተከበረባት ከተማ ማድረግ ነው"፡፡በተሰጠን ተለዕኮ መሰረት ህዝቡን በፀጥታ ጉዳይ በማሳተፍና ባለቤት በማድረግ ክፍለከተማችን ያለምንም የፀጥታ ችግር የወንጀል ድርጊቶችን ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ ባይቻልም ከነበረበት እንዲቀንስ በማድረግ ህዝባችን በሰላም ወጥቶ እንዲገባ ማድረግ ነዉ፡፡

Lideta sub-city communication office

Lideta sub-city communication office

Lideta sub-city communication office

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
## Lideta Sub-City Communication office

### ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶቻችን ለብልፅግናችን!

ኢትዮጵያ በርካታ ብሄርና ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚኖሩባት ሀገር ነች፡ ፡በርካታ ብሄሮችና ብሄረሰቦች እንዲሁም ህቦች መኖሪያ ከመሆኗ ጋር ጋር ተያይዞ የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች፣ ቋንቋዎችና የታሪክ ባለቤት እንድትሆን አድርጓታል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ሀገራችን በአለም አቀፍ ደረጃ እንድትታወቅና የጎብኝዎች መዳረሻ እንድትሆን አድርጓታል። በኢትዮጵያ የሚገኙ ቅርሶችና ባህሎች በዓለምአቀፍ ደረጃ እንዲታወቁ በማድረጉ በኩል መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራቱ ውጤቶች እንደተገኘ ቢታወቅም ቅርሶችን የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት መሆናችን ይታወቃል።

ያሉንን ቅርሶቻችንን በአግባቡ በመጠቀም ሀገራችን በኢኮኖሚው ዘርፍ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ማሳካት እንድትችል የልደታ ክፍለ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት እያከናወነ የሚገኘውን ተግባር የጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ ግዛው አለሙን ጠይቀን ለመፅሔት ዝግጅታችን እንዲመች እንዲህ አቅርበነዋል።



**አቶ ፈይሳ ብርሃኑ**
**የሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ**

ፅ/ቤቱ በያዝነዉ 2017 ዓ.ም ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር በርካታ ሰራዎችን ሲያከናዉን የቆየ ሲሆን፡ ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ እና በመስቀል ደመራ እና የኢሬቻ በአላት የፀጥታ ርዕሶች ላይ በድግግሞሽ በክ/ከተማ እና በወረዳ ደረጃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ አደረጃጀቶች እና ማህበራት በመስጠት የአደባባይ በዓላት ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲያልፉ ማድረግ ተችሏል።

በአካባቢ ሰላም፣ አብሮነትና ትብብር፣ የህግ የበላይነትና መልካም አስተዳደር፣ ወቅታዊ ችግሮችና የተፈቱበት መንገድ፣ ሰላምን የሚያደፈርሱ በየአካባቢው ያሉ ድርጊቶች ዙርያ በድግግሞሽ እስከ ብሎክና በቡና ጠጡ መድረኮች ጭምር የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሳተፉበት የምክክር መድረኮችን ማድረግ ተችሏል።

ወንጀልና ህገ-ወጥ ድርጊቶችን በመከላከል፣ በመቆጣጠር እና እርምጃ በመውሰድና በማስወሰድ የወንጀል ድርጊቶችን በ2016 በተመሳሳይ ግዜ ከነበረው 212 ወደ 142 በማድረስ የወንጀል ምጣኔ መቀነስ ችሏል።

ከማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር ተያይዞ ዶላር ጭማሪ ያሳየ መሆኑን ከግምት በማስገባት ያልተፈለገ የዋጋ ጭማሪ የማድረግ ሁኔታዎች በንግድ ቤቶችና በችርቻሮ ሱቆች ጭምር የተስተዋለ መሆኑን ከግምት በማስገባት የሰላምና ፀጥታ ከፀጥታ አካላት ከደንብ ማስከበር እና ከንግድ ጽ/ቤት ጋር በመሆን የበርለበር ክትትሎች በማከናወን የተለያዩ ንግድ ቤቶች ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ ችሏል።



**አቶ ግዛው አለሙ**
**የባህል ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊ**

የባህል፣ኪነጥበብና ቱሪዝም ዘርፍን በማላቅ ከቀዳሚ የክ/ከተማችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና መሠረቶች አንዱ በማድረግ፤የክፍለ ከተማችንን ሕዝብ ባህላዊ፣ኪነ ጥበባዊ፣ታሪካዊ እና ተፈጥሮአዊ መስህቦችን በማጥናት፣ በመጠበቅ፣ በማልማት፣ በማስተዋወቅና ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግና የከተማችንን መልካም ገጽታ በመገንባት ዘላቂ የሆነ፣ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ እንዲቻል በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ እንገኛለን። ጽ/ቤታችን የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶችም በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባራትን እንዲያከናውን፣ የባህል፣ የኪነጥበብ፣ የሥነ ጥበብና የፈጠራ ችሎታ በከተማው ውስጥ እንዲያዳብርና እንዲያሰፋ የማድረግ ተግባራትን ማከናወን በአዋጅ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ነው።

እንደ ልደታ ክ/ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ጽ/ቤት በጽ/ቤታችን 21 አገልግሎቶች የሚሰጡ ሲሆን ከነዚህም መካከል የእደ ጥበብ ማህበራት እንዲደራጁ የተለያዩ ሙያዊ ድጋፎችን መስጠት፤እደ ጥበብ ዘርፍ ሥልጠና መስጠት፤የባህል/በዕደ ጥበብ ምርቶች አውደ ርዕይ የማዘጋጀት አገልግሎት በዚህም ውስጥ በእደጥበብ የተሰማሩ በክፍለ ከተማችን የሚገኙ አምራቾችን ባህል ከማስተዋወቅ ባለፈ የገበያ ትስስር መፍጠር ተችሏል።

የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት በባህልና ኪነጥበብ ዘርፎች የሚሰጥ ሲሆን የሆቴልና ቱሪዝም ብቃት ማረጋገጫ መስጠት ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሙያ ፍቃድ መስጠት፤ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃዎችን መወሰንና መቆጣጠር፤በጠቃሚ የባህል እሴቶችን በማህበረሰቡ ዘንድ የማስረፅ፤የአሉታዊ መጤ ባህሎችና መከላከል ፣በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ ዕድገትን የሚያዳትቱ አመለካከቶችን ግንዛቤ መፍጠር፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ተግባሮችን ያከናውናል፤ የባህል ዘርፍ ልማታዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያድርጋል፡፡

ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ሥነ ጥበብ እና የፈጠራ ችሎታ በክፍለ ከተማው ውስጥ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ግብረ-ገባዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን የሚያራምዱና የሚያስፋፉ እንቅስቃሴዎችን በመመከታተል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤ህዝባዊና መንግስታዊ ከተማ አቀፍ የባህል ቀናት እና ሁነቶች ያከብራል፡፡ ለምሳሌ የብሄር ብሄረሰቦች ቀን እና የመሳሰሉት ክብረ በዓላት በተጨማሪ ቅርሶችን የመመዝገብ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን በመለየት ጥናትና እንክብካቤ እንዲሁም ጥበቃ ማድረግ፤በቤተ መፅሀፍት የንባብ አገልግሎት እና የውሰት አገልግሎት፤ የኪነ-ጥበብ የዕይታዊ ጥበባት ኤግዝቢሽን ማዘጋጀት አገልግሎት፤የስነጹሁፍ ምሽት አገልግሎት፤በኪነ-ጥበብ ዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ሙያዊ ሥልጠና መስጠት፥የቱሪዝም መረጃ አገልግሎት መስጠት፤ የሃገርን እወቅ ክበባትን ማቋቋምና መደገፍ እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን በማከናወን የባህልና ኪነ ጥበብ ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡

በመሆኑም እንደ ልደታ ክ/ከተማ የባህል፣ኪነ-ጥበብ ቱሪዝም ጽ/ቤት ተፈጥሮአዊ፤ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም ሀብቶቻችንን በማልማትና በማስተዋወቅ ከዘርፉ የሚገኘዉን ጠቀሜታ ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ ለአገራችን ብልፅግና ግብዓት እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

**“ተፈጥሮአዊ፤ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም ሀብቶቻችን ለብልፅግናችን!!”**

## ፕላንና ልማት

ለተቋሙ በአዋጅ ከተሰጡት ተልዕኮች የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ማከናወን፣ ከተቋማት የሚቀርቡ የፕላን አስተያቶች ምላሽ መስጠት፣ የስፓሻል/ገጸ-ምድር ፕላን መረጃዎች ከተቋማት በመሰብሰብ የአፈጻጸም ክትትል ማድረግና የማስተካከያ ግብረ-መልስ መስጠት፣ የፕላን አፈፃጸም ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ የክፍለ ከተማ አስተዳደሩን የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የማህበራዊ ኢኮኖሚ ልማት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት እንዲሁም የክትትል፣ ግምገማና ምዘና ስራ ማከናወን እና የፕላን መረጃ ማዘጋጀትና የማሰራጨት ስራዎች ናቸዉ፡፡

ለተቋሙ የተሰጡ ተልዕኮዎችን ከማሳካት አንፃር ከመሬት ተቋማት እና ግንባታ ፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ጽ/ቤት ለቀረቡ የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ጥናቶች፣ የፕላን ማብራሪያና አስተያየት ጥያቄዎች ከመዋቅራዊ ፕላን አንፃር በማየት ለሁሉም የፕላን ማብራሪያ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ተችሏል፡፡ የግንባታ ፈቃድ መረጃዎች በመሰብሰብ ከፕላን አንጻር ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ በቤዝማፕ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል ፡፡ የክፍለ ከተማ አስተዳደሩን የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት እቅድ እና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የማዘጋጀት እንዲሁም ለሴክተሮች የክትትልና ድጋፍ ስራ እየተሰራ ይገኛል ፡፡

የሴክተሮች የ5 አመት (2013-2017) ስትራቴጂክ እቅድ አንፃር ከ2013 -2016 ያለዉን የ4 አመት አፈፃፀምን ከእቅዳቸዉ ጋር የማናበብ ስራ እየተሰራ ሲሆን ከሴክተሮች ጋር ዉይይት በማድረግ ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ ይሰራል ፡፡



**አቶ ክብረት አሳምነው**
**የፕላንና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ**

ከፕላን ቢሮዉ ፀድቀዉ የተላኩ የፕላን መረጃዎችን ለሚመለከታቸዉ የመሬት ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ የማድረግ ስራ የተሰራ ሲሆን ከተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መረጃ ፈልገው የመጡ ተማሪች የጥናት ማሟያ መረጃዎች እንዲያገኙ ተደርጓል ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ቢሮ ፀድቀዉ የመጡ መመሪያዎች የማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፕላን ዝግጅት አፈፃፀም፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ምዘና መመሪያ ቁጥር 4/2016፣ የገፀ ምድራዊ ፕላን አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ ቁጥር 3/2016 በተመለከተ ለሚመለከታቸዉ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በ2016 በጀት አመት በክፍለ ከተማችን ተጀምሮ የነበረዉ የኮርደር ልማት ስራ በያዝንዉ በጀት አመትም ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ከሳርቤት-ካርል አደባባይ-ብስራተገብረኤል-አቦማዞሪያ-አረቄ ፋብሪካ እንዲሁም ከሳርቤት ቫቲካን-አቦ ማዞሪ 6.5 ኪ.ሜ ርዝመት እና 168 ሄ/ር የሚሸፍን የእግረኛ መንገድ፣ አረንጓዴ ልማት እና ሳይክል ያካተተ እንዲሁም የግሪን ፕላዛ እና የትራንስፖርት ፓርኪንግ ልማት ስታንዳርዱን የጠበቀ ልማት በከተማ አስተዳደሩ ድጋፍ በከፍተኛ ፍጥነትና ጥረት እየተሰራ ይገኛል ፡፡

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት

## Lideta Sub-City Communication office



**አቶ ገመቹ ጌታቸው**
**የኢኖቪሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ**

### አገልግሎትን ያሳለጡ ቴክኖሎጅዎች

የልደታ ክፍለ ከተማ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ጽ/ቤት በጥናትና ምርምር የተደገፈ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን በማልማትና ደህንነቱ የተጠበቀ ሲስተሞችን በማበልጸግ እና ዲጂታል አገልግሎት በማስፋፋት የልደታ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች እና የነገብኚዎቿን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በትኩረት እየሰራ ይገኛል። ጽ/ቤቱ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተግባራዊ በማድረግ በዘርፉ ወሳኝ የሚባሉ ለውጦችን አስመዝግቧል። በዚህ ጽሁፍ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ ገመቹ ጌታቸው ጋር ቆይታ ያደረግን ሲሆን በቆይታችንም ተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሳለጥ ያለማቸውን የቴክኖሎጂ አይነቶች እናስቃኛችኃለን መልካም ንባብ።

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቅ ስለተባበሩን እናመሰግናለን ?

**አቶ ገመቹ፡-** እኔም ስለጋበዛቹህኝ አመሰግናለው።

**ልደታ ፋና፡-**የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ኢኖቪሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ጽ/ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል እና ማዘመንን በተመለከተ ምን ስራዎችን ሰራ?

**አቶ ገመቹ፡-** በክፍለ ከተማችን ያለውን አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን እና አገልግሎት በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ለማስቻል በርካታ ስራዎችን ሰርተናል።

**ልደታ ፋና፡-** በክፍለ ከተማው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ቴክኖሎጂዎች አሉ ካሉ በዘርዝር ቢነግሩን?

**አቶ ገመቹ፡-** በክፍለ ከተማችን የወሳኝ ኩነት(Versis and web system)፣ ንግድ ጽ/ቤት (Online registering)፣ ትምህርት ጽ/ቤት (Educational management system)፣ ጤና ጽ/ቤት (health registration)ና ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት (ICMIS) ናቸው።

**ልደታ ፋና፡-**ቴክኖሎጂዎች አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ምን ለውጥ አመጡ?

**አቶ ገመቹ፡-** ቴክኖሎጂዎች አገልግሎት አሰጣጡን እንዲዘምን ሌብነት እንዲቀንስና ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እንዲኖር አድርገዋል።

**ልደታ ፋና፡-** የሰው ሀብትና የንብረት አስተዳደሩን ለማዘመን የተሰራ ስራ አለ?

**አቶ ገመቹ፡-**የሰው ሀብትና የንብረት አስተዳደሩን ለማዘመን በአራቱም ፑል የሰው ሃይል ፋይናስ ጽ/ቤት(IBX)፤ ቤቶች ጽ/ቤት(Housing pro, mudc.gov.et፣ የስዓት መቆጣጠሪያ አሻራ፣ ግንባታ ፍቃድ ጽ/ቤት (e-service)፣ዌብ ሳይት( web site)፤ የንብረት አስተዳደር ሲስተምና የመሬት አስተዳደር ሲስተም ተዘርግቷል።

**ልደታ ፋና፡-** አዲስ እየለሙ ያሉ ቴክኖሎጂዎች አሉ ካሉ ቢዘረዝሩልን?

**አቶ ገመቹ፡-** እያለማናቸው ያሉ ቴክኖሎጅዎች ITMS ሲስተም 365 office

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን

**አቶ ገመቹ፡-** እኔም እድሉን ስለሰጣቹህን በጣም አመሰግናለው።

### ህዝብን ማገልገል ክብር ነው!

መንግስት የህብረተሰቡን የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቆዎችን ለመመለስ የተለያዩ ዘዴዎችን በመከተል ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡ :የሚሰሩ የልማት ስራዎች በአጭር ጊዜና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ በማጠናቀቅ ህብረተሰቡ ከመንግስት ጎን ተሰልፎ ኃላፊነቱን እንዲወጣ እየረዱት ይገኛል።መንግስት ያቀዳቸውን የልማት ስራዎች እውን እንዲሆኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ድርሻ የጎላ ነው።

በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳዳደርም የተያዙት የመልካም አስተዳደር ጥያቆዎችና የልማት ስራዎች በአስተዳደሩ ውስጥ ያሉት ሴክተር መስሪያ ቤቶች የህብረተሰቡ የልማት ጥያቄ የተሳካ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ውስጥ የዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤትን በመውሰድ በ2017 በጀት ዓመት ያከናወንቸውን ተግባራት ምን እንደሚመስል የጽ/ቤቱን ኃላፊ ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩን አነጋግረን ለመጽሄት በሚመች መልኩ አቅርበነዋል።

## የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office

ልደታ ፋና የ2017 ዓ.ም የመጀመሪያ 6 ወር ዕትም



**ወ/ሮ ብርቱካ ባህሩ**
**የዋና ስራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**በ2017 በጀት እያከናወናችሁ ያላችሁት ስራ ምን ይመስላል?

**ወ/ሮ ብርቱካን፡-**ጽ/ቤታችን በበጀት ዓመቱ በርካታ ተግባራትን ለማከናወን አቅዶ ስራዎችን በእቅዳቸው መሰረት እያከናወንን እንገኛለን፡፡ዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት በስሩ በርካታ ተቋማት ያቀፈና የተለያዩ አገልግሎቶች የሚገኙበት እንደመሆኑ መጠን ሰፊ ተልዕኮ ይዘን የክፍለ ከተማውን ነዋሪዎች ማዕከል ያደረገ አገልግሎት እንዲሰጥ ጥረቶችን በማድረግ ውጤታማ ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን፡፡ በዚህም የህብረተሰቡን የአገልግሎት ፍላጎት ከግምት በማስገባት የነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና በጸጥታና በመልካም አስተዳደር ዘርፍ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን፡፡ይህን አገልግሎት በመስጠታችንም የህብረተሰቡ የአገልግሎት ፍላጎት እየተሸሻለ በመምጣት ህብረተሰቡና አስተዳደሩ ይበልጥ በመቀራረብ አስተዳደሩ የህብረተሰቡን ፍላጎት ምን እንደሆነና የትኛውን ተግባር ማስቀደም እንዳለበት ግንዛቤ እንዲኖረው እያደረገ ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**በ2017 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዛችሁትን አገልግሎት ከማሳካት አኳያ ስራችሁን እንዴት ገመገማችሁት?

**ወ/ሮ ብርቱካን፡-**በበጀት ዓመቱ ለመስጠት ካቀድነው አገልግሎት አንዱ የመልካም አስተዳደር ችግርን መለየትና ችግሮቹ እንዲፈቱ ማድረግ ሲሆን ለዚህም ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የተያዙት እቅዶች የተሳኩ እንዲሆን የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡የህብረተሰቡን የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት የተለያዩ አማራጮችን የምንጠቀም ሲሆን አሁንም ተግባራዊ እየሆነና የሆነው ፕሮግራማችን የአንድ ማእከል አገልግሎት ሲሆን ፕሮግራሙን ረቡዕ እና አርብ በማከናወን የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች የሚፈልጉትን ጥያቄ ለሚፈልጉት መስሪያ ቤት በቀጥታ ጥያቄያቸውን ማቅረብ እንዲችሉ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪምበአንድ ማዕከል የቀረቡ ጥያቄዎችን በማድመጥና ችግሮችን ለመረዳት የነዋሪዎች ቤት ድረስ በመውረድ በህብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች በፍጥነት መልስ እንዲያገኙ ትረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ሴክተር መስሪያ ቤቶችን በበጀትና በሰው ሀይል አደራጅቶ ከመምራት አንጻር ምን ምን ተግባራትን እያከናወናችሁ ትገኛላችሁ?

**ወ/ሮ ብርቱካን፡-**ተቋማችን በርካታ ሴክተሮችን በስሩ በሰው ሃይልና በበጀት በማደራጀት በበላይነት የሚመራ ሲሆን በካሽ ፍሎው መሰረት በጀታቸውን እንዲጠቀሙ እያደረግን እንገኛለን፡፡በስሩ ያሉ ተቋማት በካሽ ፍሎው መሰረት ስራቸውን ሲያከናውን የፋይናንስ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ለህብረተሰቡና ለተቋማት የምንሰጣቸውን አገልግሎት ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆን አድርጓል፡፡ተቋማት ለሚፈልጓቸው ግዥዎችና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያዎችን በመቅቱ በማከናወንና የተገዙ ዕቃዎች ለተጠቃሚው በወቅቱ እንዲደርሱ በማድረግ ስራዎቻችን በቅልጥፍና እንዲከናወኑ አስችሎናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ከክፍለ ከተማው የካቢኔ ስራዎች ውስጥ የእናንተ የስራ ድርሻ እንዴት ይገልጹታል?

**ወ/ሮ ብርቱካን፡-**እንደተቋም ሌላው ተግባራችን የካቢኔ ጉዳዮች ሲሆኑ በበጀት ዓመቱ የሴክተሮችን የበጀት እንዲሁም የግብዓት ችግርና የክፍለ ከተማው መደበኛና ወቅታዊ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በካቢኔ አጀንዳ በማስያዝ የበጀት ድጋፍ እንዲደረግ በትኩረት እየሰራን እንገኛለን፡፡በቤቶች፣በኮሪደር ልማትና በሌሎች \የልማት ስራዎች ጋር በተያያዘ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ውሳኔዎች አጀንዳ በመቅረፅ እንዲወሰኑና አሰራር እንዲጠበቅ የማድረግ ስራዎችን ሰርተናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን

**ወ/ሮ ብርቱካን፡-** እኔም አመሰግናለሁ

### ትውልድን በስነ-ምግባር በመገንባት ሙስናን እንከላከል

የልደታ ክ/ከተማ ስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ክፍል ካሉት ዓላማዎች አንዱ የትውልድ ሥነ-ምግባር እና የሞራል እሴቶችን መገንባት ነው፡፡

የሞራል እና ስነ-ምግባርና ግንባታ ዋነኛ ማዕከል የግልና የመንግስት ት/ቤቶች ናቸው፡፡

የትምህርት ማህበረሰቡ በትምህርት ተቋማት ላይ ሊጎለብቱ በሚገቡ የስነ-ምግባር ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፣በትምህርት ተቋማት የሚቋቋሙ የስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ክበባት ማንዋል ላይ የጋራ ግንዛቤ መያዝ

ዜጎች በአስተሳሰብና ባህሪ የተሻለ ሀገር ተረካቢ ሆነው ከሚወጡባቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው፣ዜጎች ተሰጥኦአቸውን የሚያገኙበት የተሰጥኦ መግለጫና ማጎልበቻ ማዕከል ነው፣ትምህርት ዜጎች የነገ ማንነታቸውን የሚያሳልጡበትና እራሳቸውን በእውቀት ፣ክህሎትና አመለካከት የሚያሳድጉበት ዘርፍ ነው፣ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችል መልኩ እውቀት የሚገበይበት የእውቀት መድረክ ነው፣ዕውቀትን ለማስረጽ፣ ክህሎት ለማጎልበትና ተሞክሮን ለማጋራት የተነደፉ የትምህርት ፖሊሲዎች፣ ሥርዓተ ትምህርቶችና ስትራቴጂዎች የሚተገበሩበት ነው፡፡



Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት

## Lideta Sub-City Communication office



**ወ/ሮ እማዋይ አበባው**
**የስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪ**

### ከትምህርት ተቋማት የሚጠበቅ ሚና

በትምህርት ቤት ውስጥ ግብረገባዊ እሴቶች እንዱጎለብቱ ተማሪዎች በግብረገብ የሚታነጹበትን መድረክ ማመቻቸት፤የግብረገብ ባህርያት እንዲሰርጹ ሃላፊነት የተሰጣቸውን የስነምግባር ክበባትን ማገዝ፤የሥነምግባር ክበባት ከት/ቤቱ መምህራን፤ ሰራተኞችና ተማሪዎች ሊወገደ የሚገቡ እኩይ ጠባዮችና ተግባሮችን ነቅሶ በመለየት እንዱወገደ ጥረት ማዴረግ፤ መልካም ግብረገባዊ ድርጊቶችና ጠባዮች እንዲስፋፉና እንዱጎለብቱ ጥረት ማድረግ። ክትትል ድጋፍ ግምገማና ግብረመልስ ማድረግና ይህም ትኩረት የሚያደርገው የክበቡ አደረጃጀትና አሰራር ፤ ከተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ ማምጣት፤ ከተማሪዎች ውጤት መሻሻል ጋር ማጣጣም ያስፈልጋል።

### ግብረ ገብን በማጎልበት የአስተዲደር ሰራተኞች ሚና

• በት/ቤቶች መልካም ስነምግባር እንዲጎለብት በየደረጃው ያለ የአስተዲደር ሰራተኞች በመልካም ሥነምግባራቸው ዓርአያ መሆን ፤ የትምህርት ቤት አመራሮች መሪዎች የተናገሩትን ሆነው በመገኘት አርአያ ሆነው መገኘት። በትምህርት ቤት ውስጥ መልካም ስነምግባርን ማጎልበት የስነምግባር ግንባታ ስልጠና መስጠት፤ መልካም ሥነምግባር የሚያሳዩትን ማበረታታት፤በስነ-ምግባራቸው የተመረጡ የቀደሙ የስራ ሃላፊዎች በተለየ ሁኔታ ሮል ሞዴል እንዲሆኑ ማድረግ፤ የህብረተሰቡን ፍላጎት አክብሮ የመስራት ባህል በት/ቤቱ ውስጥ የዘወትር ልማድ እንዲሆን የአስተዲደር ሰራተኞች ሚናቸውን በመወጣት የመምህራን ሚና፣ መምህራን በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን በእውቀት፣በክህሎት እና በአመለካከት (መልካም ስነምግባር) የማጎልበት ቁልፍ ሚና መወጣት አለባቸው፣ መምህራን በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎቻቸው ከሚሰጡት እውቀት ባሻገር በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸው የሥራ ባህል እንዱሁም ልማድ የተማሪዎቻቸውን የወደፊት ስብእና በመቅረጽ ረገድ የሚያሳድረው ተጽእኖ ከስርአተ ትምህርቱ ያልተናነሰ ነው።

### የአስቸካይ የሙስና መከላከል አስፈላጊነት

• ሙስና ለመፈፅም የታቀደውን ድርጊት በማምከን የሙስና መከላከል ሥራን ውጤታማ ማድረግ ስለሚያስፈልግ፣በእውቀት እና በልምድ ማነስ ወደ ስህተት የሚገቡ አመራሮችንና ሠራተኞችን እንዲሁም የመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸውን አካላት ስህተት ከመፈፃማቸው በፊት ጉዳዩን በማምከን አስፈላጊውን ማስተካካያ እንዲያደርጉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤ሆነ ብለው ሙስና የመፈፀም ሃሳብ ያላቸው አካሎች ድርጊቱን ከመፈፀማቸው እና የህዝብ ሃብት ከመዝረፋቸው በፊት ማስቀረት ስለሚገባ፤ ለምርመራና ክስ የሚባክነው ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ጉልበት ለማስቀረት፤በተቋም ውስጥ የግልፅነትና የተጠያቂነት አሠራር ለማስፈን፤የሙስና ወንጀል ተከስቶ ወይም ተስፋፍቶ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ከባቢያዊና ፖለቲካዊ ኪሳራን ለማስቀረት አስቀድሞ መከላከል ተገቢ በመሆኑ፤ሙስና ለመሥራት የተመቻቹ ሁኔታዎችን በማምከን በአገሪቱ ውስጥ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመሥጠት ስለሚያግዝ፤

### የአስቸኳይ የሙስና መከላከል አሠራር ሥርዓት መዘርጋት

• በተቋም የሥራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለሙስና ያላቸው ተጋላጭነት ባላቸው አሠራሮች ላይ ቋሚ የአስቸካይ መከላከል ሥራ ለመሥራት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ዋና የሥራ አካል ማድረግ፣በተቋም የአሰራር እንቅስቃሴ ሙስና እንዳይፈጸም በንቃት መከታተል

• በተቋሙ ሙስና ለመፈጸም እንቅስቃሴ እየተደረገ ያለውን ሙስና ለመገመት ወይም ለመጠርጠር፣በመደበኛና ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚሰጡ አስተያየቶችን በልዩ ትኩረት መከታተል፣ ሙስና ይፈፀማል በተባሉ ጉዳዮች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት በመከታተል መረጃ መያዝ፣ በመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች የሚወሩ ሃሜቶችን እና ሹክሹክታዎችን ሁሉ ሳያቃልሉ ትኩረት በመስጠትና በመቃኘት መከታተል፣

### የአስቸኳይ ሙስና መከላከል እንዴት ይከናወናል?

• የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ከጠቋሚዎች ወይም ከሌላ አካል የተገኘው መረጃ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ ሊሰራበት እና በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ መሆኑን ሲያምንበት አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ በመስራት ሂደቱን ማስተካከል እንዲሚችል የስነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል አሰራር ደንብ ቁጥር 11/2015 አንቀጽ 22 መሰረት ተደንግጓል። በዚህ መሠረት ተገቢውን የሰነድ እና የሰው ማስረጃ በማደራጀት ከተቋሙ የበላይ ሀላፊ ጋር ስለ ጉዳዩ በቅድሚያ ያሳውቃል።

### ከተቋም የበላይ አመራር የሚጠበቅ ቁርጠኝነት፣ ክትትልና ድጋፍ የተቋማት የበላይ አመራሮች

• የተቋም የበላይ አመራር ሙስና መከላከል የሥራቸዉ ዋነኛ አካል የማድረግ፣ ለሚከናወኑ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ አስፈላጊዉን ድጋፍ የመስጠት፣ለሚቀርቡ የአስቸካይ ሙስና

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
## Lideta Sub-City Communication office

መከላከል ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ድርጊቱ እንዲመክን አፈጣኝ ውሳኔ የመስጠት፣የሥራ ክፍሎች የተለያዩ ማስረጃዎች ሲጠየቁ እንዲሰጡ መመሪያ የመስጠት፣የተጠቆሙ የመፍትሄ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግ፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጉዳይ ላይ የተቋሙ የበላይ አመራር በሚሰጠው ማብራሪያ ላይ ሁለቱም (የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉና የበላይ አመራሩ በመረጃ በተደገፋ ማብራሪያ) ከተስማሙበት የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራውን ማቋረጥና ስለአፈፃፀሙ ለኮሚሽን ሪፖርት ማቅረብ፣የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና መከታተያ ክፍል በተቋሙ የበላይ አመራር የተሰጠው ማብራሪያ ላይ ከስምምነት ካልደረሰና የያዘቸው መረጃዎች አስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ መሥራትን የሚጠይቅ መሆኑ በቂ ማሳያዎች ካሉት ጉዳዩን ለሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቅረብ፣ ከኮሚሽኑ የመጨረሻ ውሳኔ ማግኘት፣በኮሚሽኑ ውሳኔ የአስቸካይ ሙስና መከላከል ስራ ጥናት ከተካሄደ በኋላ የውሳኔ ሀሳብ ይቀርባል፤የተሰጠው ምክረ ሀሳብ በተቋም የበላይ አመራር ተቀባይነት አግኝቶ እርምጃ ካልተወሰደበት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ያደርጋል ፤ ኮሚሽኑም ጉዳዮን የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያሳውቃል።

### የአስቸኳይ ሙስና ጠቀሜታው

• ሊባክን የሚችልን ሃብት መታደግ ያስችላል፤ዉስን የሆነዉን ሃብት ለታለመለት አላማ ለማዋል ያስችላል፣ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፤ችግሩ ከተከሰተ በኋለ የችግሩን ፈጣሪና የባከነውን ሃብት ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ የሃብት ብክነት ያስቀራል፣ለሃገር ጠቃሚ በሆነ ተግባር ላይ ሊሰማሩ የሚችሉ ዜጎችን በችግሩ ውስጥ ተዘፍቀው እንዲባክኑ ከማድረግ ያድናል፣በችግሩ ምክንያት በወንጀለኞች በቤተሰቦች ሊደርስ የሚችለውን ማህበራዊ ቀውስ ይቀርፋል፣ወንጀለኞችን ለማስተዳደር የሚወጣ ወጪን ይቀንሳል፣

### ብክለት ይብቃ ዉበት ይንቃ!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም እንደገና በወጣው አዋጁ ቁጥር 84/2016 መሰረት አደረጃጀቱ በከተማና በክፍለ ከተማ ብቻ እንዲሆን ተደርጎ ተደራጅቷል። በዚህም መሰረት በተሰጠዉ ስልጣንና ኃላፊነት የአካባቢ ብክለት ክትትልና ቁጥጥር ላይ በርካታ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። ሆኖም ህብረተሰቡ የሚያነሳቸዉን የአካባቢ ብክለት ይወገድልኝ ጥያቄዎችን በሚፈለገዉ ልክ ምላሽ እንዳልተሰጠ እና የአካባቢ ብክለት ጉዳይ ትኩረት ሳይሰጠው በተጨባጭ ወደ ተግባር ሳይቀየር ቆይተዋል። ሆኖም አሁን በመሪዎች ደረጃ ልዩ ትኩረት በመስጠት የአካባቢ ብክለት አሳሳቢነት ሁሉም ተረድቶ መከላከል እና እያንዳንዱ ዜጋ የራሱን ኃላፊነት መወጣት እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጧል።

ስለሆነም የልደታ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በወረደለት አቅጣጫ መሰረት የክፍለ ከተማውን ነዋሪዎች በማስተባበር የተለያዩ የንቅናቄ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። የተሰሩ ስራዎችን ለእናንተ አንባቢያን ለማድረስ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ አንተነህ በፍቃዱ ጋር ቆይታ አድርገናል።



**አቶ አንተነህ በፍቃዱ**
**የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** በጽ/ቤቱ እየተከናወኑ ካሉ ተግባራት መካከል ውጤት አምጪ ስራ የሰራችሁበትን ስራ ይገልጹልን

**አቶ አንተነህ ፡-** እንደሚታወቀው የአካባቢ ብክለትን ለመቅጣተርና ለመከላከል በትኩረት የሰራን ሲሆን በተጨማሪ ደግሞ ሰፊ የንቅናቄ ስራዎችንም ሰርተናል ለመጥቀስም ያህል "ብክለት ይብቃ ዉበት ይንቃ "በሚል መሪ ቃል ከሚያዝያ1/2016ዓ.ም እሰከ መስከረም30/2017ዓ.ም ለስድስት ወራት ሲካሄድ የቆየዉ የአካባቢ ብክለት መከላከል ንቅናቄ ተሰርቷል። ስራው ሲጀመር በእያንዳንዱ ወር የሚከበርበት መሪ ቃል ተሰይሟል።

ስያሜያቸውም ሚያዝያ የፕላስቲክ ብክለት ወር፤ግንቦት የአየር ብክለት ወር፤ሰኔ የዉሃ ብክለት ወር፤ሀምሌ የአፈር ብክለት ወር፤ነሀሴ የድምፅ ብክለት ወር እና መስከረም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ተግበራ ወር ተብሎ በመሰየም በርካታ ስራዎችን ስንሰራ ቆይተናል።

ወርሃ-ሚያዝያ - የፕላስቲክ ብክለት "የፕላስቲክ ልማዶችን እናስወግድ" በሚል መሪ ቃል ተከናዉኗል።ወርሃ-ግንቦት - የአየር ብክለት"ንፁህ አየር ለጤናማ አካባቢ" በሚል መሪ ቃል ተከናዉኗል።ወርሃ ሰኔ- የውሃ ብክለት"ውሃችንን እንጠብቅ፡ እያንዳንዱ ጠብታ ዋጋ አለው" በሚል መሪ ቃል ተከናዉኗል።ወርሃ ሃምሌ- የአፈር/መሬት/ ብክለት"አፈርን መጠበቅ፣ ብልጽግናን ማረጋገጥ " በሚል መሪ ቃል ተከናዉኗል።ወርሃ ነሃሴ- የድምጽ ብክለት "የተደበቀው ስጋት፡ የድምፅ ብክለትን መረዳት እና መከላከል" በሚል መሪ ቃል ተከናዉኗል።ወርሃ መስከረም/2017ዓ.ም- የአካባቢተፅዕኖ ግምገማ ትግበራ "በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መወሰን፡ አካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ግምት ውስጥ እናስገባ" በሚል መሪ ቃል ተከናዉኗል።

**ልደታ ፋና ፡-** ስራዎች ከመከናወናቸው በፊት የተሰሩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ምን ይመስላል

**አቶ አንተነህ፡-** "ብክለት ይብቃ ዉበት ይንቃ "በሚል መሪ ቃል ንቅናቄዉ እንደ አገር እና በከተማ አስተዳደር ሲጀመር እንደ ክ/ከተማችን እንዴት ማስጀመር እና ማስቀጠል እንደለብን እንዲረዳን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተከናዉነዋል፡ የተከናወኑት ቅድመ ዝግጅት ስራዎች የአካባቢ ብክለት ንቅናቄ እቅድ በማዘጋጀት በእቅዱ ላይ ያጋራ መግባባት መፍጠር፣ በቅድሚያ እንደ ፅ/ቤት ለሁሉም ባለሙያዎች ንቅናቄዉን በተመለከተ ግንዛቤ መስጠት ፣የስራ ክፍፍል በማድረግ እና ማን ምን እሰራል የሚለዉን በግልፅ በማስቀመጥ በዚህ የ6 ወር በብክለት ንቅናቄ የሚሰሩት ስራዎች ከማዕከል በወረደዉ መሰረት ከኮሚቴዎች ጋር የጋራ ዉይይት ተደርጓል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ባለፉት 6 ወራት በንቅናቄው ስራ ዙሪያ ግንዛቤ ከመፍጠር አንጻር የተሰሩ ስራዎችን ይግለጹልን

**አቶ አንተነህ፡-** በንቅናቄ ለሚሰሩ ስራዎችበርካታ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን ሰርተናል፡፡ለክ/ከተማ እስከ ወረዳ ነዋሪዎች፣ለሁሉም ብሎኮች ለአንደኛ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፣ ለኮምኒኬሽን ባለሙያዎች ፣ ህብረተሰብ አንቂዎች እና ታዋቂ ግለሰቦች ፣ ከክ/ከተማ ለተውጣጡ ሴቶች ፣ ከክ/ከተማ ለተወጣጡ የብሎክ ተወካዮች ለወረዳ እና ለክ/ከተማ የምክር ቤት ቋሚ ኮምቴዎች ፣ ለሁሉም የሀይማኖት ተቋማት ተወካዮች ፣ ከክ/ከተማ ለተወጣጡ ወጣቶች ፣ ለመንግስት ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰጥተናል፡፡ አጠቃላይ በዚህ የብክለት መከላከል ንቅናቄ ከ120 ሺህ በላይ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና የህ/ሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ችለናል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** በንቅናቄ በመሰራቱ የተገኙ ውጤትስ እንዴት ይገልጹታል

**አቶ አንተነህ ፡-** በንቅናቄ ስራዎች በመሰራታቸው የመጡ ውጤቶች ለመጥቀስ ህ/ሰቡ የአካባቢ ብክለት ይወገድልኝ ጥያቄዎችን በስፋት አቅርቧል፣ የአካባቢ ጉዳይ የሁሉም አካላት ጉዳይ መሆኑ ተቋማት የአካባቢ ብክለት ለመከላከል የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ በማዘጋጀት የአካባቢ ህግና ደረጃዎችን ለማክበር ሰፊ እንቅስቃሴዎችን እድርገናል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ

**አቶ አንተነህ፡-** ህብረተሰቡ በአካባቢ ብክለት ዙሪያ የወጡ ህጎች እና አዋጆችን በመገንዘብ ለአካባቢው የተቆርቋሪነት ባህል በማሳደግ ማንኛውንም ብክለት የመከላከል ስራ በመስራት ለኑሮ ምቹ አካባቢን የመፍጠር ስራ እንዲሰራ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ

**አቶ አንተነህ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለመልካም አስተዳር ስኬታማነት

በልደታ ክፍለ ከተማ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና ለሚያጋጥም ቅሬታና አቤቱታ አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት፣ ስህተቶችን ለማረምና አገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ ለማድረግ፤በየደረጃው ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊ እና ሠራተኛ ለህብረተሰቡ በሚሰጡት አገልግሎት አስተዳደራዊ ጥፋትና በደል እንዳይፈፀሙ መከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ ተጠያቂ ለማድረግ እና በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ የመስሪያ ቤት ኃላፊና ሠራተኛ በማፍራት ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ለማስቻል በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ እኛም በክፍለ ከተማው ህዝብ የሚያነሳቸውን ቅሬታና አቤቱታዎች ለመፍታት እየተሰራ ያለውን ስራ አስመልክቶ ከክፍለ ከተማው ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አቤል ኤርሚያስ ጋር ቆይታ አድርገናልና አብራቹህን ቆዩ መልካም ንባብ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በቅደሚያ ለቃለ መጠይቅ ስለተባበሩን በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን

**አቶ አቤል፡-** እኔም ለማህበረሰቡ መረጃ እንዳካፍል ስለጋበዛቹህኝ አመሰግናለሁ

**ልደታ ፋና፡-** እንደ ልደታ ክ/ከተማ መልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ምን ምን ስራዎች ተከናውነዋል?

**አቶ አቤል፡-** ጽ/ቤቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከብሎክ ጀምሮ እስከ ክ/ከተማ ሴክተር ተቋማት በመለየት ችግሮችን ለመፍታት እየሰራ ነው፡፡ ቅሬታና አቤቱታን በተመለከተ የቀረበ ቅሬታን ለመፍታት በቅንጅት እየሰራ ሲሆን በዚህም ለተለያዩ ቅሬታዎች ውሳኔ እንዲያገኙ ማደረግ ችሏል፡፡



**አቶ አቤል ኤርሚያስ**
**የመልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የአንድ ማዕከል አገልግሎት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ረገድ ምን ለውጥ አመጣ?

**አቶ አቤል፡-** ማህበረሰቡ በአንድ ማዕከል በሚሰጥ አገልግሎት ቀርቦ ችግሩን በማስረዳት ፈጣን የሆነ ምላሽ እንዲያገኝ ማደረግ ተችሏል፡፡ ለበርካታ ዓመታት ሳይፈጡ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ምላሽ ማግኘት የጀመሩት በአንድ ማዕከል አገልግሎት ነው፡፡





**ልደታ ፋና፡-** ከተቋማት ጋር በትስስር በመሰራቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ረገድ ምን ለውጥ መጣ?
**አቶ አቤል፡-**በቅንጅታዊ አስራር 30 ጽ/ቤቶች ትስስር የፈጠሩ ሲሆን በወረዳ ደረጃ 10 ቅንጅታዊ አስራር ትስስር በመፍጠር ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በክ/ከተማ ደረጃ ዕቅድና ሪፖርት ተቀብለን እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት ተችሏል፡፡
በአጠቃላይ 546 ሰው በጀመርነው አመት የመልካም አስተዳደር ችግሮች ዙሪያና በቅንጅታዊ አሰራር በዘላቂነት ለመቅረፍ ከዕቅድ ኦርንቴሽን ጀምሮ የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠዎችን ለባለድርሻ አካላት ፣ለአመራር ፣ለብሎክ አደረጃጀት፣ለሲቪክ ማህበራትና ለባለሞያዎች መድረክ ተፈጥሯል ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን
**አቶ አቤል፡-** እኔም አመሰግናለው

## መረጃን የማዘመን ጉዞ

በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት የአሰራር ስርአት ማሻሻል ጽ/ቤቱ ከያዛቸው የተቋማዊ ሪፎርም ስራ አንዱ ሲሆን እነዚህ ችግሮች ለመፍታት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ህትመት እና የአሰራር ብልሽት መሰረት በማድረግ በተቋሙ መዋቅር ስራ ላይ የነበሩ ህትመቶችን በሙሉ ወደ ማዕከል እንዲሰበሰብ ተደርጎ የማስወገድ ስራ በመስራት በምትኩ ተጨማሪ አዳዲስ ሚስጥራዊ ይዘት ያላቸው ህትመቶች ወደ አገልግሎት ማስገባት ያስቻለ ሲሆን አዲሱ ህትመት ለብልሹ አሰራር እንዳይጋለጥ የሚያደርግ አሰራር ስርዓት በመዝርጋት ቀድሞ ከነበረው ብልሹ አሰራር መሻሻል አሳይቷል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በተቋማዊ ሪፎርም ለማሳካት የታቀደው ከምዝገባ የተገኙ መረጃዎች ደህንነት ለመጠበቅ፣ ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል፣ የአገልግሎትን ቅልጥፍና እና ተደራሽነት የሚያረጋግጥ ቴክኖሎጂ መተግበር ነው፡፡ በተቋሙ እየተከናወነ ያለው የሪፎርም ስራ እና አጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጡ ያለበትን ደረጃ እንዲያብራሩልን የመፅሔት ዝግጅት ክፍላችን ከፅ/ቤቱ ሀላፊ ወ/ሮ መቅደስ ያደታ ጋር ቆይታ አድርጋለች፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለቃለ-መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡
**ወ/ሮ መቅደስ ያደታ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ የሚሰጣቸዉን አገልግሎቶች ለማዘመን የሰራቸዉን ስራዎች ቢገልጹልን?
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** የጽ/ቤቱ መዋቅር ለተገልጋይም ሆነ አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ምቹ ያልነበረ ሲሆን በተለይም በወረዳ ደረጃ ችግሩ የከፋ ነበር፡፡ በወረዳ ደረጃ በጣም ጠባብ ቢሮ ከመሆኑ የተነሳ ተገልጋዩ እና ባለሙያ መለየት የሚያስቸግርበት፣ ደላሎች በመሃል ተቀላቅለው ህገወጥ ስራ ለመስራት ምቹሁ ሁኔታ የሚፈጥር ሁኔታ የነበረበት፣ ተገልጋዮች ለወረፋ ብር የሚከፍሉበት፣ የህትመቶች አቀማመጥ ለብልሹ አሰራር፣ ለሌብነት እና ለብልሽት የተጋለጡ በአጠቃላይ ቢሮው ገፅታው የተበላሸ ነበር፡፡ አሁን ላይ በክፍለ ከተማችን የሚገኙ 8 የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤቶች ለተገልጋይ ምቹ የማድረግ የማዘመን ስራ ተሰርቷል፡፡ ህትመት እና የአሰራር ብልሽት መሰረት በማድረግ በተቋሙ መዋቅር ስራ ላይ የነበሩ ህትመቶችን በሙሉ ወደ ማእከል እንዲሰበሰብ ተደርጎ የማስወገድ ስራ በመስራት በምትኩ ተጨማሪ አዳዲስ ሚስጥራዊ ይዘት ያላቸው ህትመቶች ወደ አገልግሎት ማስገባት ተችላል፣ አዲሱ ህትመት ለብልሹ አሰራር እንዳይጋለጥ የሚያደርግ አሰራር ስርዓት በመዝርጋት ቀድሞ ከነበረው ብልሹ አሰራር መሻሻል ታይቷል፡፡ በተቋማዊ ሪፎርም ለማሳካት የታቀደው ከምዝገባ የተገኙ መረጃዎች ደህንነት ለመጠበቅ፣ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል፣ የአገልግሎትን ቅልጥፍና እና ተደራሽነት የሚያረጋግጥ ቴክኖሎጂ መተግበር ነው፡፡



**ወ/ሮ መቅደስ ያደታ**
**የሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የተገልጋይን እንግልትና ቅሬታ አሁን ላይ በምን ደረጃ ይገለጻል? የምታስተናግዱበት አግባብ ምን ይመስላል?

**ወ/ሮ መቅደስ፡-** የተገልጋይን እንግልትና ቅሬታ የቀነሰ እንዲሁም ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እየተሰጠ በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጥና በተገልጋይ መካከል የሚገባ ደላላ ለማጥፋት የወረፋ ማስጠበቂያ ማሽን እንዲኖር በመደረጉ፤ የመታወቂያ ህትመትን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ ተጨማሪ መሽን በመገዛቱ በአሁን ሰአት የተገልጋይ እንግልትና ቅሬታ ቀንሷል። በተጨማሪ ቅሬታ ያለው አካል ሲመጣ ጉዳዩን በመመርመር አፋጣኝ ምላሽ እየሰጠን እንገኛለን።

**ልደታ ፋና፡-** በተገልጋዩ መንገዶች በተቋሙ ላይ የሚነሱት የሌብነትና ብልሹ አሰራር ለማረም የተሰሩ ስራዎች ካሉ?

**የወ/ሮ መቅደስ፡-** በተቋሙ ሚነሱ የሌብነትና ብልሹ አሰራርን ለማረም በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የሌብነትና ብልሹ አሰራርን የሚያጋልጡ አሰራሮችን ለመዝጋት ለምሳሌ፡- የጥቆማ መስመሮችን በየቦታው ለጥፈናል፤ ችግር ሲገጥማቸው በተቀመጠው ቁጥር በመመደወል ጥቆማ እዲሰጡ ይደረጋል። አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ መስጠት(ዲጂታላይዝ) በማድረግ በማንዋል የሚሰጡ አገልግሎት ለሌብነትና ብልሹ አሰራር መንገድ ስለሚከፍት የማንዋል አሰራሮችን ሙሉ ለሙሉ ወደ ዲጂታል በመቀየራችን የሌብነት ሁኔታውን መቀነስ ችለናል። የሌብነትና ብልሹ አሰራር ዉስጥ ገብተዉ የተገኙ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ ስራ በስፋት በመስራታችን ባለሞያና አመራሩ አሁን ላይ በተጠያቂነት ስሜት እየሰራ ይገኛል። የተገልጋዩ በተለያየ መንገድ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ በስፋት በመስራት ብልሽቱን ማስተካከል ችለናል።

**ልደታ ፋና፡-** ፋይዳ ወይም የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ስራ ያለበት ደረጃ ቢገልፁልን?

**ወ/ሮ መቅደስ፡-** በቅድሚያ ብሄራዊ መታወቂያ ለኢትዮጵያ ነዋሪዎች በሙሉ የተለየ የነዋሪነት መታወቂያ መስጠት ነው። ይህ የነዋሪነት መታወቂያ "አንድ ሰው አንድ ነው" (one identity) የሚለውን መርህ ይዞ የግለሰቡን መረጃዎች በመውሰድ የራሱ የሆነ የነዋሪነት መታወቂያ እንዲኖረው ማድረግ ሲሆን ሁሉም ሰዎች አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ብሔራዊ መታወቂያ በማውጣት እንደሀገር በርካታ ጥቅሞችን እናገኛለን። ይህንን ምዝገባ እድናከናውን ተቋማችን ኃላፊነት ተሰጥቶት ወደ ስራ ገብተናል። ከጥቅምት 1/2/2017 ዓ.ም በ10ሩም ወረዳዎች ምዝገባ እያከናወንን እንገኛለን። ይህን ቃለ መጠይቅ እስከሚሰጥበት ድረስ 25,000 ዜጎችን መዝግበናል። እንደ ክፍለ ከተማችን 92,000 ህዝብ እንዲመዘገብ እቅድ የያዝን ሲሆን እቅዱን ለማሳካት በተነሳሽነት እየሰራን እንገኛለን። በዚህ አጋጣሚ ማህበረሰቡ የብሔራዊ መታወቂያ መያዝ ሊያስገኘው የሚችለውን ጥቅም በመረዳት በየወረዳው በመሄድ መመዝገብ ይኖርበታል።

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ መቅደስ ያደታ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## ለሀገር ዕድገት የወጣቶች ሚና

ወጣትነት በእርጅና ወራት መስራት የማይችላቸዉን ማንኛቸዉንም ተግባር በማከናወን በመጦሪያ ዘመኑ የአቅሙን ጥሪት ሀብት የሚያፈራበት እድሜ ነዉ። ለእዚህም ነዉ ወጣትን ከደፋሩና ከጀግናዉ የዱር እንስሳት መካከል ከሆነዉ ነብር ጋር በማገናኘት ወጣት የነበር ጣት ተብሎ የተተረተዉ። ኢትዮጵያ ደግሞ ትኩስ ሃይል ያለዉና ሰርቶ እራሱን በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ረገድ በማሳደግ ለሀገርም መትረፍ የሚችል ወጣት ያላት ባለጸጋ ሀገራችን ነች።

ይህን ያልኩት ያለምክንያት አይደለም እንደሚታወቀዉ መንግስት በየጊዜዉ ለወጣቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለያዩ ዘርፎች እንዲሳተፍና ዉጤታማ እንዲሆን ለማስቻል ሰፋፊ ስራዎች እየሰራ ይገኛል። ዛሬ ልናነሳዉ የወደዱነዉ የልደታ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ሲሆን መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ዓላማዉን እያሳካባቸዉ ካሉ ተቋማት መካከልም አንዱ የሆነዉን ይህን ማህበር በመጽሄት አምዳችን ልናነሳዉ ወደናል፤ ታዲያ ከማህበሩ ሰብሳቢ ወጣት ቢኒያም አሸናፊ ጋር ቆይታ አድርገናል በንባብ ተከተሉን መልካም



**ወጣት ቢኒያም አሸናፊ**
**የወጣት ማህበር ሰብሳቢ**

**ልደታ ፋና፦** ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሄደበት ርቀት ምን ይመስላል?

**ወጣት ቢኒያም፦** ማህበሩ የተቋቋመለትን አላማ ከማሳካት አንፃር በ26 አመታት ውስጥ ሰፋፊ ስራዎች የሰራ ሲሆን በዋነኝነት በሀገሪቱ የወጣቶች ፖሊሲ እንዲቀረፅ የጎላ አስተዋፆ በማድረግ የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እንዲገነቡ እና ወጣቱ በአስተሳሰብ የላቀ በእውቀት የመነጠቀ እና በስነ ልቦና የዳበረ አዕምሮ ባለቤት እንዲሆን በሀገራችን የመጀመሪያውን የወጣት ማዕከል በመገንባት ተምሳሌት መሆን ችሏል።

ወጣቱ በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታም የራሱን ድርሻ ከመወጣትና ሰፋፊ ስራዎችን ከመስራትም አንፃር በሀገራችን በተከናወኑ ሀገራዊ ምርጫዎች በታዛቢነት በማስተባበር ምርጫው ፍትሐዊ እና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን የራሱን አሻራ እያስቀመጠ የመጣ ማህበር ነው።

**ልደታ ፋና፦** የወጣቱን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሰራቸዉ ስራዎች ምንድን ናቸዉ?

**ወጣት ቢኒያም፦** የወጣቱን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንፃር ከመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር የተለያዩ በቋሚነት እና በጊዜያዊነት የስራ እድል እየፈጠረ ከመሆኑም ባሻገር ወጣቱ በተገኘው የስራ እድል በመጠቀም እና ስራ ሳይንቅ እራሱን እንዲቀየር ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በመተባበር የአመለካከት እና የክህሎት ስልጠናዎች እንዲወስድ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፦** ወጣቱ በሀገሩ ሰርቶ መለወጥ እንዲችል ለማስቻል ምን አይነት ስራዎች ተሰርቷል?

**ወጣት ቢኒያም፦** ወጣቱ በሀገሩ ሰርቶ መቀየር እንደሚችል ተምሳሌት የሆኑ ወጣቶች መድረክ እየተመቻቸላቸው ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ እየተደረገ ሲሆን በህገ-ወጥ ስደት እና የሰዎች ዝውውር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ስልጠናዎች እየተሰጡ ይገኛሉ። በእዚህም ስደት ምን አይነት ጉዳት ያስከትላል የሚለዉን እዉቀቱ እንዳላቸዉ ይታመናል ግን በተግባር ችግሩ የደረሰባቸዉን ወጣቶችን በተለያዩ መንገዶች ለግንዛቤ እያቀረብን በእርግጥም ችግሩ ምን ያክል ሰፊና የወጣቱን የመስሪያና የመለወጫ እድሜ በአጭሩ እየቀጨ መሆኑን እንዲረዱ እያደረግን ነዉ።ይህን ከተረዱ ደግሞ ሀገራቸዉ ላይ ባለ ፀጋና ሀብት ተጠቅመዉ እራሳቸዉን በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ ጉዳይ በማሳደግ በሀገር ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል ማሳያ እንዲሆኑ የማይቋረጥ ስራ እየሰራን እንገኛለን።

**ልደታ ፋና፦** ወጣቱ በማህበራዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የዜግነታቸዉን እየተወጡ እራሳቸዉን እንዲለዉጡ ለማስቻል ምን አይነት ስራዎች ተሰርቷል?

**ወጣት ቢኒያም፦** እንደ ማህበራችን ወጣቱ የነገ ሀገር ተረካቢ ነው በሚል ሳይሆን የዛሬ የሀገር ባለቤት እና ገንቢ ነው ብለን እናምናለን። ለዚህም ነው በተለያዩ ሀገራዊ አጀንዳዎች ፊት አውራሪ በመሆን እየተሳተፍን የምንገኘው።

ሌላው ማህበራችን የበጎ ፍቃድ ተግባራትን በከተማችን ከማስተዋወቅም በላይ ማህበራዊ እሴቶቻችንን ከማስጠበቅ አንፃር በተለያዩ ሰዋዊ ተግባራት ላይ እንደ ቁልፍ ተግባር በመያዝ በክረምት እና በበጋ የበጎ ፍቃድ ተግባራት ላይ ወጣቱን በማሳተፍ ሰፋፊ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

**ልደታ ፋና፦** አጠቃላይ ለወጣቱ የሚያስተላልፉት መልዕክት

**ወጣት ቢኒያም፦** ለከተማችን ብሎም ለክፍለ ከተማችን ወጣት የማስተላልፈው ነገር ወጣት ማለት የሰላም ባለቤት እንደመሆኑ መጠን ሰላማችንን ከመጠበቅ እና ከማስጠበቅ አንፃር ግንባር ቀደም በመሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትስስር እንዲሰሩ፣ መንግስት እየሰራቸው በሚገኙ የልማት ስራዎች በባለቤትነት በመጠበቅ እና በማስጠበቅ እንዲሁም መንግስትም ሆነ ወቅቱ በሚያመቻቸው የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ስራን ባለመናቅ ለተተኪዎቻችን ተምሳሌት በመሆን የምናስባትን የምንመኛትን ኢትዮጵያን መገንባት አለብን። ሌላዉ ምንጩ ከማይታወቅ የሀሰት መረጃዎች እራስን በመጠበቅ እና ሀሳብን በሀሳብ በመሞገት ወቅቱ የሚፈልገውን የስልጣኔ ደረጃ ላይ በመድረስ የራሳችንን ሀላፊነት እንድንወጣ ጥሪ አቀርባለሁ።

**ልደታ ፋና፦**ስለነበረን ጊዜ በጣም አመሰግናለሁ

**ወጣት ቢኒያም፦**እኔም አመሰግናለሁ

### የህዳሴ ግድባችን የአብሮነታችን ማሳያ

በአለም ላይ ያሉ ሀገራት አንዱ ሌላውን በስልጣኔ በልጦ ለመገኘት የተለያዩ አማራጮችን እየተጠቀሙ ይገኛሉ። ለስልጣኔያቸው ውጤታማነት ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች ደግሞ ዋነኛው የቴክኖሎጅ ስርዓቱን ማዘመን ነው። የቴክኖሎጅ ስርዓትን ለማዘመንና ስልጣኔዎችን ወደፊት ለማራመድ ሁሉም ሀገራት የእኔ ወደሚሉት ሃብታቸው ፊታቸውን በማዞር የኤሌክትሪክ ሀይላቸውን ለማጠናከር በትኩረት ይሰራሉ። ኢትዮጵያም የአሌክትሪክ ሀይሏን በማጠናከር የምታገኘውን የሀይል አቅርቦት ለመጠቀም ከወሰነች ዋል አደር ብላለች፡ ፡ይህን ዕቅዷን እውን ለማድረግ ከ13 ዓመት በፊት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በመገንባት ከሀገራችን አልፎ ለአፍሪካ ብርሃን እንዲሆን አድርጋ በመስራት ወደ ማጠናቀቁ ደረጃ አድርሳዋለች።

አገራችንን ወደ ቀደም ገናናነቷ ለመመለስ ደግሞ በግዙፍነቱ ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም ደግሞ ሰባተኛ ደረጃን የሚይዘውን ግድብ ሁሉም ዜጋ በመተባበር እንዲጠናቀቅና የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት የአገራችን ዋነኛ ችግር የሆነውን የመብራት መቆራረጥ አስወግዶ አዲስ የብርሃን ዘመን የሚያበስር ይሆናል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያለማቋረጥ በመገንባት ላይ ይገኛል፡ ፡የተሰራው በሁሉም የአገሪቷ ተወላጆች፣ ትውልደ ኢትዮጰያንና በባለሃብቶች ዙሪያ በተደረገው የገንዘብ ርብርብ ነው፡፡

በዛሬው ጽሁፋችን ርዕስ አድርገን የተነሳነው የክፍለ ከተማችንን የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የህዳሴ ግድብ አጠናቆ ሀገሪቷ ለምትፈልገው ጥቅም ለማዋል እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን ምን ይመስላሉ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የጽ/ቤቱን ኃላፊ አቶ ኤፍሬም መገርሳን ጠይቀን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



**አቶ ኤፍሬም መገርሳ**
**የልደታ ክ/ከተማ የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሀላፊ**

ከሁሉም አስቀድሜ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ከተጣለ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ልማት ወዳዱ የክ/ከተማችን ማህበረሰብ ከህጻን እስከ አዛውንት ባደረጋችሁት ርብርብ የግድቡ ግንባታ ብዙ ፈተናዎችና ውስብስብ ችግሮች አልፎ የፕሮጀክት አፈጻጸም 96% መደረሱ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ መግለጽ እወዳለሁ፡፡

የማስተባበሪያ ጽ/ቤታችን የታላቁ የኢት/ያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በመላ የክ/ከተማችን ነዋሪ ህዝቦች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ተጠናቆ የሰላም ፣የኢኮኖሚና የብልጽግናችን ምንጭ ሆኖ ማየት የሚል ራእይ ሰንቆ ለግድቡ ግንባታ ድጋፍ የሚውል ሀብት የማሰባሰብ፣ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን የማስተባበርና የግድቡ ግንባታ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በማስመልከት የተለያዩ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን የማሳለጥ ዋናዋና ተግባራትን ያከናውናል፡፡ በዚህ መሰረት እንደ ክ/ከተማችን በ2017 በጀት ዓመት ደግሞ የ10ሩም ወረዳዎችና የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የዘርፍ ኮሚቴዎች አቅም በመጠቀም ከዝግጅት ስራዎች ጎን ለጎን 1.8 ሚሊየን ብር ለታላቁ ህዳሴ ግድብ የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከ86% በላይ ሃገራችን ለናይል ውሃ እያቀረበች 1% ውሃ እንኳ ለወንዙ አስተዋጽኦ የማያበረክቱ ሃገራት ባለቤትነትን በመንፈግ ምንም በአባይ ውሃ መጠቀም እንደማንችል ከመግለጽ ባሻገር ስራውን ለማስተጓጎል በሃገር ውስጥ ጀሌዎቻቸውንና በአለም አቀፍ ደረጃ ደጋፊዎቻቸውን በማስተባበር አቅማቸው የቻለውን ሁሉ ቢያደርጉም የግድቡ ግንባታ ባለፉት አመታት ለአፍታም ሳይቆም እንሆ በጉጉትና በናፍቆት ሲጠበቅ የነበረው የኃይል ማመንጨት ተግባር በሁለት ዙር ዩኒት ዘጠኝና አስር የማመንጨት ስኬቱ በይፋ መበሰሩ የሚታወቅ ሲሆን በቅርቡ ሶስተኛው ዩኒት 8 ኃይል ማመንጨት መጀመሩንና አራት ተርባይኖችም በቅርቡ ኃይል ለማመንጨት አስፈላጊ ስራዎች በመጠናቀቅ ላይ እንደሆኑ የኢፌድሪ መንግስት መግለጹ ይታወሳል፡፡
ግድቡ የሃገራችን አለኝታና ከሃይል ማመንጨት ባሻገር ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ጠቀሜታዎች የሚሰጥ በመሆኑ ይቻላል ብለን እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን ብለንም ቃል በገባነው መሰረት በአሁኑ ሰዓት ከላይ እደተገለጸው ከ96 በመቶ በላይ የተከናወነ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ቀሪ የግንባታ ስራዎችም እጅግ ሰፊ መዋዕለ ነዋይ የሚጠይቁ ማለትም ከ49 ቢሊየን ብር በላይ ለቀሪ ስራዎች ማከናወኛ የሚያስፈልግ በመሆኑ በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ነዋሪዎችና ተቋማት ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ አቅም በፈቀደ መልኩ ሰለቸኝ ሳይሉ ሲያደርጉ ለነበረው ትልቅ ድጋፍና አስተዋጽኦ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡ አሁንም ወደ ኋላ ሳንል የተጀመረውን የግንባታ ስራ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ ይቻል ዘንድ በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ነዋሪዎችና ተቋማት ከእንደዚህ ቀደሙ ድጋፋችሁን በስጦታ ወይም ቦንድ በመግዛት ፕሮጀክቱን እንዲጠናቀቅ ይህን ሃገራዊ ጥሪ እንዲወጡና ታሪካዊ አሻራቸውን እንዲያኖሩ በዚህ አጋጣሚ በታላቅ ትህትና መልዕክቴን ማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም የህዳሴ ግድብ ግንባታ ተጠናቆ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎትና ለሀገራችን የሚያበረክተውን ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ እውን እስከሚሆን ድረስ ሁሉም ዜጋ እጅ ለእጅ ተያይዞ የዜግነት ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ አቶ ኤፍሬም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

“አባይ ግንድ ይዞ ይዞራል ከሚለው ተረት ወጥተን የኤሌክትሪክ ኃይል ይዞ ይዞራል” ወደ ሚለው ተጨባጭ እውነታ ተሸጋግረናል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም አመሰግናለሁ፡፡
**አቶ ኤፍሬም ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

## ጤናማ ትውልድ ለሀገር ዕድገት

ቀዳማይ የልጅነት ጊዜ (Early childhood development) ሕፃን ከተፀነሰበት ቀን ጀምሮ እስከ ስምንት አመት ድረስ ሲሆን በዚህን ጊዜ በህጻናት ላይ በጣም ፈጣን የሆነ ሁለንተናዊ ዕድገት የሚከናወንበት ወሳኝ ጊዜ በመሆኑ ሁሉም ሕፃናት ለሁለንተናዊ እድገታቸዉ ማለትም በአካል፣ በአእምሮ፣ በቋንቋ/በተግባቦት፣ በማህበራዊ ህይወት ግንኙነትና በስነልቦናዊና/በስሜት (emotional)ጤናማ የሆነ እድገት እንዲኖራቸዉ ሁልጊዜ ጥሩ/ተገቢ የጤና አጠባበቅ (good health) ፤

## የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
## Lideta Sub-City Communication office

በቂና ተመጣጣኝ ምግብ (adequate nutrition) ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እንክብካቤ መስጠት (responsive caregiving) ፤ቀዳሚ ማነቃቂያ/ ቅድመ-መደበኛ ትምህርት እና ደህንነትና ጥበቃ (safety and security/protection) ማግኘት አለባቸዉ።

በቀዳማይ ልጅነት /ECD/ ዙርያ መረጃዎችን ለእናንተ ለአንባብያን ለማድረስ ከልደታ ክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አህመድ እድሪስ ጋር ቆይታ አድርገናል ተከታተሉን።



**አቶ አህመድ እንድሪስ**
**የጤና ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና ፡-** የቅድመ-ልጅነት ዘመን ዕድገት እንክብካቤ ለምን ይረዳል
**አቶ አህመድ ፡-**የቅድመ-ልጅነት ዘመን ዕድገት እንክብካቤ (Nurturing Care for Early Child Development) የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገት እንክብካቤ በተጠቀሰው የልጅነት ዕድሜ ወቅት አራቱም የዕድገት ምሰሶዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ በማስቻል ልጆች ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲኖራቸው ለማገዝ የሚተገበር የተሟላ እንክብካቤ ነው።የልጅ ዕድገት አራት ምሰሶዎች አሉት። እነሱም አዕምሮአዊ፤አካላዊ፤ የቋንቋ፤ የማህበራዊና ስሜታዊ/ስነልቦናዊ የዕድገት ምሰሶዎች ናቸው።

**አእምሯዊ እድገት (Cognitive Development):**
ሲባል ሕፃናት የመረዳት፣ የመማር/የማወቅ፤ የመተንተን፣ የመተርጎም፣ የማስታወስ የተሻለ ዘዴ የመፍጠር እና በእራሳቸው እና በአካባቢያቸው ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ የሚችል ሁኔታን የመቋቋም ብልሃት ወይም ችሎታቸውን የሚያመለክት የዕድገት ዓይነት ነው።

**አካላዊ እድገት (Physical Development):**
ማለት ሕጻናት በቁመታቸውና በክብደታቸው፤ በአካላቸዉ ወይም በሰዉነታቸዉ እንደ ዕድሜያቸው የሚያሳዩት የእድገት ለዉጥ፤ የአካል ጥንካሬና ቅልጥፍና ሲሆን የትላልቅ ጡንቻዎች እድገት (Gross motor) ማለትም እግር፡ አንገት፡ ወገብ ወዘተ... በመጠቀም መንቀሳቀስ እና የትናንሽ ጡንቻዎችን (Fine motor) ማለትም የእጅ ጣቶችን) በመጠቀም መመገብን፣ እቃ መያዝን፣ ስዕል መሳልን፣ መፃፍን፣ ትናንሽ ነገሮችን ከመሬት መልቀም መቻልን ወዘተ የመስራት ችሎታቸውን ያጠቃልላል።

**ማኅበራዊ እድገት (Social Development):**
ማለት ሕፃናት ከሌሎች ሰዎች ጋር በነፃነት የመግባባት፣ አብሮ የመጫወት፣ የመተጋገዝና ከአካባቢያቸው ጋር ጤናማ፣ ወዳጃዊና የማያሰጋ ግንኙነት የመፍጠር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ ተግባራትና ችሎታ ማለት ነው።

**ስነ-ልቦናዊ/ስሜታዊ እድገት (Emotional Development):**
ማለት ደስተኝነትን፣ በራስ የመተማመንን፣ መሳቅን፡ ርህራሄን፣ መረጋጋትን፣ በተገቢ ሁኔታና ጊዜ ዉስጥ የመግለፅ ችሎታ እና ፍርሃትን፣ ስጋትን፣ ጭንቀትን፣ ቁጣን፣ ማልቀስን፣ የስሜት መረበሽን የመከላከልና የመቆጣጠር ችሎታን ማዳበርን ያመለክታል።

**መግባባት/የመግባበት ችሎታ (Communication):**
ማለት ሕፃናት በድምፅ፣ በሰዉነት እንቅስቃሴ ወይም በምልክት የተነገራቸዉን ወይም ያዩትን የመረዳት /የማወቅ (Receptive ability) እና እነሱም ለሌሎች የመናገርና የማስረዳት/መልስ የመስጠት (Expressive ability) ችሎታን ማሳደግ/ማዳበር ማለት ነዉ።

**ልደታ ፋና፡-** የቅደመ ልጅነት ዘመን ዕድገት እንክብካቤ ስንት ዘርፎች አሉት
**አቶ አህመድ፡-**የአለም ጤና ድርጅት ያወጣው የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገት እንክብካቤ አምስት ዘርፎች አሉት እነሱም ጥሩ ጤና፤በቂና የተመጣጠነ ምግብ፤ደህንነትና ጥበቃ ፤ፍቅር የተሞላበት ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ፤ቀደም ብሎ የመማር ዕድልና የአዕምሮ መነቃቃት ናቸው፡

ለልጆች የተሟላ ሁለንተናዊ ዕድገት በቂና የተመጣጠነ ምግብ መመገብ፤ጤናቸውን እና ደህንነታቸውን መጠበቅ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ፍቅር የተሞላበት ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ማድረግ ፤ ዘወትር በማጫወትና በማዋራት ቀደም ብለው የመማር ዕድል እንዲያገኙና የአዕምሮአዊ ዕድገታቸው እንዲነቃቃ ማስቻል እጅግ በጣም ያስፈልጋል፡፡

የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገት እንክብካቤን በተሟላ መልኩ መተግበር ልጆች ሁለንተናዊ ዕድገት ይዘው በማደግ ብሩህ አዕምሮ ፤ አካላዊ ብቃት ፤ ጥሩ ተግባቦት መልካም ማህበራዊ ግንኙነት ፤ ጠንካራ ስነልቦና እና ቀና አስተሳሰብ ያላቸው እንዲሆኑ ይረዳል፡ ፡ ይህም በህይወት ዘመናቸው ሊደርሱ ከሚችሉበት ከፍተኛ የብቃት ደረጃ እንዲደርሱና ስኬታማ ህይወትን በመምራት ከራሳቸው አልፈው ለማህበረሰብና ሀገራዊ ብልጽግና አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡

ቀጥተኛ ሀገራዊ ጥቅምን በተመለከተ የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገት ላይ መዋለ ነዋይ ማፍሰስ ለሀገራዊ ጠቅላላ ምርታማነት (GDP) እና ማህበራዊ እድገት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ለምሳሌ አንድ ዶላር በልጅ ላይ ማዋል በሚያስገኘው የተሻለ ትምህርት ፤ ኢኮኖሚ ፤ ጤናና ማህበራዊ ውጤት ምክንያት 13 ዶላር አመታዊ ትርፍ እንደሚያስገኝ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡



Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office
Lideta sub-city communication office

**ልደታ ፋና፡-** ለልጅ ሁለንተናዊ ዕድገት ምን ማድረግ ይገባል?

**አቶ አህመድ፡-** ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ማድረግያ ስፈልጋል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው የልጆችን ፍላጎትና ስሜት በማስተዋል ለሚያሳዩት ምልክትና ፍላጎት ፍቅር በተሞላበት መንገድ እንዲጫወቱና እያወሩ ተገቢ ምላሽ መስጠት ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ይባላል፡፡ ምላሽ ሸጪ እንክብካቤ በልጅ ፍላጎት እየተመሩ ማጫወትን ፤ዓይን ዓናቸውን እያዩ ማውራትን፤በፍቅር ማቀፍና መደባበስን ትኩረትና ጊዜ ሰጥተው አብሮ መሆንን ያካትታል፡፡ ከልጆች ጋር በሚሆኑበት ጊዜ ስሜታቸውን ማዳመጥ፤ ዓይን ዓይናቸውን ማየት ፤ስማቸውን እየጠሩ ማዋራት ፤ለሚጠይቁት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠትና ለሚያደርጓቸው መልካም ነገሮች በአካላዊ ምልክትና በንግግር ማበረታታት ለአእምሮአዊ ለቋንቋ ፤ለአካላዊ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ዕድገት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** ልጆችን እንዴት ማነቃቃትና የአእምሮ እድገታቸው እንዲፋጠን ለማስቻል ምን ምን መደረግ አለበት

**አቶ አህመድ፡-** ልጆችን በማጫወት በማውራት ወይም በማነቃቃት ቀደም ብሎ የመማር እድል እንዲያገኙ እና የአእምሮ እድገታቸው እንዲፋጠን ማስቻል ማለትም የሰው አእምሮ ከጽንሰት እስከ መጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት በህይወት ዘመን ተማላልሶ በማይመጣ ፍጥነት ወደ 80%ገደማ ያድጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ልጆችን ዘወትር በማጫወት በማውራት መዝሙር በመዘመርና መሰል ተግባራትን በማድረግ ልጆች ቀደም ብሎ የመማር እድል እንዲያገኝ በማድረግና የአእምሮ እድገቱን በማነቃቃት ለተሟላ ሁለንተናዊ እድገቱ ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ልጆች ሁሉንም የስሜት ህዋሶቹን (ማየት ፣መስማት ፣መዳሰስ፣መቅመስ እና ማሽተትን ) መጠቀም በሚያስችል ሁኔታ እንዲጫወት ያደርጋል፡፡

እርሶ የሚያደረጉትን ልጅ አስመስሎ እንዲያደርግ እንዲሁም ልጅ የሚያደርገዉን እርሶም በተራዎ አስመስለው እያደረጉ ተራ በተራ ከልጆች ጋር እየደጋገሙ ይጫወቱ/ያውሩ መጽሃፍት እንዲያዩ እንዲይዙ እያገላበጡ እንዲያነቡ አብረው እያነበቡ ያበረታቱ፡፡ በዚህ መልኩ ልጆችን ዘወትር ሲያጫውቱ፡ሲያውሩ ፡ሲዘምሩለት፡ተረት ሲተርኩለትና መጽሐፍ ሲያነቡለት ልጆችን ቀደም ብሎ የመማር እድልን በማግኘት አዳዲስ ቃላትን፤ዕዉቀትን ክህሎትን አንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፡ ፡ በተጨማሪም የተግባቦት አቅሙ እንዲያድግ እና ነገሮችን ለማወቅ ለመማር እና ለንባብ ያለው ፍላጎት እንዲቸምር ያግዙታል ፡፡ ይህም የአእምሮ እድገቱን በማነቃቃት ለተሟላ ሁለንተናዊ እድግቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ከቤት ውጪ ልጆችን ማጫወት ፡-ጨዋታ ለልጆች አእምሮአዊ፣አካላዊ፣የስሜትና ስነ-ልቦናዊ ዕድገትን ያግዛል፡፡ ከቤት ውስጥ በተጨማሪ ልጆችን ዘወትር ወደ ውጭ በማውጣት ደህንነቱን በጠበቀ ሁኔታ ማጫወት ያስፈልጋል፡፡ልጆች ገና በለጋ እድሜው በዙሪያው ባለው ዓለም የሚሳተፉበት እና መስተጋብር የሚፈጥሩበት በጨዋታ ነው፡፡ጨዋታ ልጆች ከወላጅ/አዋቂ ወይም ከሌሎች ልጆች ጋር መሆን የታዳጊነት ሚናቸውን እየተለማመዱ ፍርሃታቸውን በማሸነፍ ዓለምን እንዲያቁ ያስችላል፡፡

ጨዋታ የልጆች የመማር፤የመተግበርና የፈጠራ ችሎታን ያዳብራል፡፡ በተቻለ መጠን ልጆች ከስክሪን ( ቲቪ፣ ሞባይል...) ጋር የሚሳተፍበትን ጊዜ እንዲቀንሱ እና እንዲርቁ በማድረግ በምትኩ ከወላጅ/አሳደጊ ወይም ሌሎች ልጆች ጋር አብረው የሚጫወቱበትን ጊዜ ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡ይህም ልጆች ተንቀሳቅሰው እንዲጫወቱ ፤እንዲያወሩ ነገሮችን እንዲያሰላስሉ፤እንዲመራመሩ በአእምሮአቸው ነገሮችን ስለው እንዲያዩ ማስቻል የተሟላ እድገት እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

የልጆች የእድገት አቅጣጫ የሚወሰነው ከወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጋር ባላቸው ፍቅር እና ጨዋታ የተሞላ ቋሚ ግንኙነት ነዉ፡፡ከልጆች ጋር መጫወት በወላጅ እና በልጅ መሀል ያለውን ግንኙነትን ያጠናክራል፡፡ በጨዋታ የተሞላ ወላጅነት ወላጆች የልጆቻቸዉን የእድገት ችግሮች በቶሎ እንዲፈቱና ሁለንተናዊ እድገታቸውን እንዲያዳብሩ በማስቻል ደስተኛ ቤተሰብ እንዲኖር ያግዛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ልጆችን ለማጫወት ምቹ ጊዜ የቱ ነው?

**አቶ አህመድ፡-** ልጆችን ዘወትር ስናጫዉትና ስናዋራ የተሟላ ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲኖራቸው እናስችላለን፡፡ስለዚህ እያንዳንዱ ደቂቃ ለልጆች ሁለንተናዊ ዕድገት ሊኖረው የሚችለውን አስተዋጽኦ በማሰብ በተቻለ መጠን ልጆችን የምናጫዉትበትና የምናዋራበትን ጊዜ ማብዛት ያስፈልጋል፡፡

ልጆችን ለማጫወትና ለማዋራት የተለየ ጊዜ ለማግኘት ከማሰብ ይልቅ ከእለታዊ ክንዉኖቻችን ጋር በማጣመር ልጆችን ማጫወትና ማዋራት ይቻላል፡፡ለምሳሌ፡- ጡት ሲያጠቡ፤የልጆችን ገላ ሲያጥቡ፤ምግብ ሲያበስሉ፤ልብስ ሲያጥቡ፤ልጆችን ሲያስተኙ፤ቤት ሲያጸዱ፤እረፍት ሲያደርጉና ሌሎች መሰል እለታዊ ክንውኖችን በሚተገብሩበት ጊዜ ሥራዎን እየሰሩ ጎን ለጎን ልጅዎን ማጫወትና ማዋራት ይችላሉ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለልጆች ምን አይነት የመጫወቻ እቃን መጠቀም ያስፈልጋል?

**አቶ አህመድ፡-** ልጆችን ለማጫወት ከሱቅ የሚገዙ ዉድ የመጫወቻ እቃዎችን የግድ መጠቀም አያስፈልግም፡፡ በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ቀላል መጫወቻዎችን በማዘጋጀትና የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ልጆችን በሚገባ ማጫወት ይቻላል፡፡የማጫወቻ እቃዎቹ ለልጆች አደጋ የማያደርሱ፤ንጹህ፤ሳቢ፤ምቹና ልጆችን ንቁ የሚያደርጉ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል፡፡

ወንድና ሴት ልጆች እኩል የመጫወት እድል እንዲኖራቸዉ ማድረግና በጾታ ያልተለየ የመጫወቻ እቃዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ በወንዶችና ሴቶች መሃል ያለዉን እኩልነትና መረዳዳትን ያሰርፃል፡፡ ስለዚህ ሴቶች ልጆች የሚያዘወትሩዋቸውን መጫወቻዎች ወንዶች ልጆችም በመጠቀም እንዲጫወቱ ያበረታቱ፡፡ ለምሳሌ በአሻንጉሊት እንዲጫወቱ፤ዕቃ ዕቃ ሲጫወቱ ምግብ የመስራት፤ቤት የማጽዳት፤ልጅ የማዘልና የመንከባከብ ሚና ወስደዉ ከሴቶቹ እኩል እንዲጫወቱ ያበረታቱ፡፡

በተመሳሳይ ወንዶች ልጆች የሚያዘወትሩዋቸዉን መጫወቻዎች ሴቶች ልጆችም በመጠቀም እንዲጫወቱ ያበረታቱ፡፡ለምሳሌ መኪና መንዳት፤አውሮፕላን ማብረር፤ኳስ መጫወትና ከቤት ውጭ ወጥቶ መጫወት እንዲችሉ ያበረታቱ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ጨዎታ የልጆችን እድገት እንዴት ያግዛል

**አቶ አህመድ፡-** ልጆችን በምናጫውትበት ጊዜ የምናጫውታቸው ጫወታዎች የልጆችን እድሜ የሚመጥኑ መሆን ይኖርባቸዋል። ልጆችን የምናጫውታቸው ጨዋታዎች የአራቱንም የእድገት ዘርፎች ዕድገት ማገዝ የሚችሉበትን መንገድ እያሰብን ማጫወትና ጨዋታዎችን እንደ አስፈላጊነቱ እየቀያየርን በማጫወት የአራቱንም የዕድገት ዘርፎች ዕድገት በተሟላ መልኩ ማገዝ ተገቢ ነው።

ለምሳሌ፡- የተለያዩ መጠንና ቀለም ያላቸውን የሚሰካኩ መጫወቻዎችን አይነትና መጠን እየለዩ መሰካካትን እንዲጫወቱ ስናደርግ፡

- በአይነትና መጠን እየለዩ መሰካካቱ ማሰብን ስለሚጠይቅ የአእምሮ ዕድገታቸው ያነቃቃሉ።
- በጣቶቻቸውና እጆቻቸው ሲያነሱ ሲያስቀምጡና እየተንቀሳቀሱ ሲጫወቱ የአካላዊ እድገታቸው ይዳብራል።
- ዝም/ጸጥ ብለን ከሚጫወቱ ይልቅ ጨዋታውን በማሻሻል እያዋራንና እየዘመርን ብናጫዉታቸው የቋንቋ እድገታቸው ይዳብራል።
- አብረናቸው ተራ በተራ እያገዝናቸው ብንጫወት፤ሲጫወቱ በአካላዊ ምልክትና በድምጽ ብናበረታታቸው፤ጥሩ ተጫዉተው ደስ ሲላቸው አብረናቸው ብንደሰት፤እንዲሁም ጨዋታው ሲበላሽባቸውና ሲበሳጩ፤ሲያለቅሱ አቅፈን ደግፈን ስናባብላቸውና ስናግዛቸው የማህበራዊና ስሜታዊ/ስነልቦናዊ እድገታቸውን እናዳብራለን።

**ልደታ ፋና ፡-** ጨዋታና ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ለታመሙና አካል ጉዳተኛ ልጆች ያለው ጠቀሜታ ይግለጹልን?

**አቶ አህመድ ፡-**የታመሙና አካል ጉዳተኛ ልጆችን ዘወትር ማጫወት፤ማዋራትና ፍቅር የተሞላበት ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ማድረግ የምግብ ፍላጎት፤የእንቅልፍና የደም ዝዉዉር ስርአቶቻቸዉ የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋል።

እንዲሁም ከጭንቀት በማላቀቅ፤የተረጋጉ፤ደስተኛ እና ንቁ እንዲሆኑ በማድረግ ከበሽታቸዉ ቶሎ እንዲያገግሙና በሁለንተናዊ እድገታቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ወይም ለማስቀረት ያግዛል።በተመሳሳይ የምግብ እጥረትና አካል ጉዳተኛ የሆኑ ልጆች የአእምሮ እድገታቸውን በማነቃቃት ከጤናማ ልጆች እኩል የአእምሮ እድገታቸዉን እንዲዳብርና ሁለንተናዊ እድገታቸዉ እንዲሻሻል ያግዛል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** መልካም ስነ-ምግባር እያስተማሩ ልጆችን ለማሳደግ ምን መደረግ አለበት?

**አቶ አህመድ ፡-** ቅጣት እና ሀይለቃል የተሞላበት ቁጣን በማስቀረት መልካም ስነ ምግባርን እያስተምሩ ልጆችን ማረቅ ያስፈልጋል።ልጆች ለሚያሳዩት መልካም ስነ-ምግባርና አወንታዊ ባህሪያት ያበረታታቸዉ፡፡ የቤት ውስጥ ደንቦችን/ህጎችን በማዉጣት ልጆች እንዲተገብሯቸዉ ያድርጉ። ልጆች የቤት ዉስጥ ህጎችን ሳይከተሉ ሲቀሩ ወይም ጥፋት ሲያጠፉ ከአካላዊ ቅጣት እና ሀይለ ቃል ከተሞላበት ቁጣ ዉጭ በሆነ መንገድ ይገስጽዋቸው።

ቅጣት እና ቁጣን በማስቀረት መልካም ስነ ምግባርን እያስተማሩ ልጆችን ማረቅ ልጆች ከአደጋ እንዲጠበቁ፤እራስን መቆጣጠር እንዲችሉ፤በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ እንዲችሉ እና በወላጅ/አሳዳጊ እና ልጆች መሀል አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖር ያግዛል።

**ልደታ ፋና ፡-** ልጆችን ሀይል በመጠቀም መቅጣት ጉዳት አለው ወይ?

**አቶ አህመድ፡-** በተቃራኒው ቅጣትና ቁጣ ልጆች ሀይልን የችግር መፍቻ መንገድ አድርገው እንዲማሩ፤ወላጅ የፈለገዉን ልጅ ከፍላጎቱም ውጪም እንኳን ቢሆን ሁል ጊዜ ተገደዉ መፈጸም እንዳለባቸው፤በወላጅ/አሳዳጊና ልጆች መሃል ያለው አዎንታዊ ግንኙነት እንዲቋረጥ፤ልጆች ወላጅን ከማክበር ይልቅ እንዲፈሩ እና በራስ መተማመን እንዲጎላቸው ያደርጋል።ቅጣትና ቁጣን በማስቀረት መልካም ስነ ምግባርን እያስተማሩ ልጆችን የሚያርቁ ቤተሰቦች በራሱ የሚተማመኑ፤ቅን የሆኑና ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ የሚችሉ ልጆችን የማፍራት እድል ይኖራቸዋል።

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራርያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን

**አቶ አህመድ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## ለመሰረታዊ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጥ ተቋም



**አቶ ስንታየሁ ተረፈ**
**የስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ኃላፊ**

### 1.ኤሌክትሪክ ፣ እሳትና አደጋ ስጋት እና ደረቅ ቆሻሻ ፎረም የተሰሩ ስራዎች ኤሌክትሪክ አገልግሎት በተመለከተ

- ወረዳ 10 አፍሪካ ህብረት አካባቢ የመብራት መቆራረጥ ችግር ተፈቷል
- ወረዳ 03 ኦሜድላ ፣ወረዳው ጀርባ፣38 ኮንደሚኒየም 37 ቀበሌ አካባቢ እንዲሁም አብዲሳ ት/ቤት አካባቢ መብራት መቆራረጥ ችግር ተፈቷል
- ወረዳ 06 ግራር ወፍጮ ቤት አካባቢ የመብራት መቆራረጥ ችግር ችግር ተፈቷል
- ወረዳ 10 ዋንዛ ፍርኒቸር አካባቢ እንዲሁም አፍርካ ህብረት ት/ቤት የመብራት መቆራረጥ ችግር ችግር ተፈቷል

- ወረዳ 10 መብራት ሀይል ጨምሮ በመምጣት እቃዎችን እያቃጠለ መሆኑን በማሳወቅ ሊስተካከል ችሏል
- ወረዳ 07 ቀጠና 4 ተክለሀይማኖት ንግድ ባንክ አካባቢ ፣ ጎላ ሚካኤል በላይኛው መግቢያ አካባቢ ፣ቀጠና 6 ጎላ ሚካኤል በታችኛው በር መብራት በተደጋጋሚ መጥፋት አጋጥሞ የነበረ ሲሆን የተፈታ።
- ወረዳ 01 አባይ ምንጭ አካባቢ የመብራት ፓወር መጨመር የነበረ ችግሩ ተፈቷል።
- ወረዳ 06 በቀለ ትምህርት ቤት አካባቢ መብራት ኬብል ተበጥሶ መስተካከል ችሏል
- ወረዳ ወረዳ 10 አፍሪካ ህብረት አካባቢ የመብራት መቆራረጥ ችግር ችግር ተፈቷል
- ወረዳ 07 ወጣቶች አደባባያ የኮሊደር ልማትእንቅፋት የሆነ ከኤሌክትሪክ ጋር ተገናኝ ዛፍ ተቀርጦ ተስተካክሏል።
- ወረዳ 07 ጎማ ቁጠባ አካባቢ የወደቀ መብራት ፖል ተነሰቷል።
- ወረዳ 01 ቀበሌ 01 ልዩ ስሙ 49 አባወራ እና ቆርቆሮ ሰፈር ተብሎ የሚጠራ አካባቢ መብራት መብራት መቆራረጥ ችግር ተፈቷል
- ወረዳ 06 ቶታል ዲማ አካባቢ ትራንስፎርመር ተበላሽቶ ችግር ተፈቷል።
- ወረዳ 10 ደሴ ሆቴል አካባቢ የመብራት መቆራረጥ ችግር ችግር ተፈቷል
- ወረዳ 10 ልደታ ቤተክርስቲያን ጀርባ የመብራት መቆራረጥ ችግር ችግር ተፈቷል
- ወረዳ 01 አባይ ምንጭ ፣ልማት ምንጭ ፣ከካ አካባቢ የመብራት በተደጋጋሚ መጥፋት የነበረ ችግሩ ትራንስፎርመር በማስተካከል ተፈቷል።
- ወረዳ 03 37፣38 ቀበሌ አዲሱ መንገድ፣ ሻወር ቤት የመብራት መጥፋት የነበረ ችግሩ ተፈቷል።
- ወረዳ 10 ላቦራ ፣ አፍሪካ ህብረት አካባቢ ፣ ብርሃን ሆቴል ፣ ማሩታ ካፌ የመብራት በተደጋጋሚ መጥፋት የነበረ ችግሩ ተፈቷል።
- ወረዳ 05 ቀበሌ30፣41፣42፣43፣47 የመብራት በተደጋጋሚ መጥፋት የነበረ ችግሩ ተፈቷል።
- ወረዳ 10 አማረች ሆቴል ገባ ብሎ የኤሌክትሪክ ገመድ ተቆርጦ ለባለሙያዎች በማሳወቅ የተስተካከለ ።
- ወረዳ 10 የመብራት ፖል ወድቆ የማስተካከል ስራ ተሰርቷል።
- ወረዳ 03 አስተዳደር መግቢያ በር ፊት ለፊት የኤሌክትሪክ ሽቦ ተበጥሶ መሬት ላይ ወድቆ ነበር ተስተካክሏል።
- ወረዳ 07 ጎላ ሚካኤል በላይኛው መግቢያ አካባቢ ፣ቀጠና 6 ጎላ ሚካኤል በታችኛው በር መብራት በተደጋጋሚ መጥፋት አጋጥሞ የነበረ ሲሆን የተፈታ።
- ወረዳ 07 ደቀ መሀሪ ፣ራህዋ ሆቴል አካባቢ መብራት መጥፋት አጋጥሞ የነበረ ሲሆን የተፈታ።
- ወረዳ 07 60 ፖሎች የመቀየር ስራ ተስርቷል።
- ወረዳ 05 630kva ትራንስፎርመር ቀበሌ 41፣30 ላለው ትራንስፎርመር ማስቀመጥ ተችሏል።
- ወረዳ 08 ላፍቶ ሞል አካባቢ የኤሌክትሪክ ፖል ወድቆ ተስተካክሏል።
- ወረዳ 06 ከካርል አደባባይ እስከ ደሳለኝ አካባቢ መብራት መጥፋት አጋጥሞ የነበረ ሲሆን የተፈታ።
- ደመራ የሚደመርባቸው በታዎችን ከኤሌክትሪክ አደጋ ስጋት ነጻ መሆናቸው፣ መብራት ያለባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል።

እሳት አደጋ ስጋትና ስራ አመራር

- ወረዳ 01 መኮነኖች ክበብ በር በኤሌክትሪክ ፖል የተነሳው እሳት ምንም አደጋ ሳይፈጥር በመብራት ሀይል እሳት አደጋ ስራ አመራር አደጋውን ተቆጣጥረውታል
- ወረዳ 07 ቀጠና 4 ተክለ ሀይማኖት አካባቢ የተነሳ እሳት ምንም ጉዳት ሳደርስ መቆጣጠር ተችሏል
- ወረዳ 05 ክላስተር 5 ቀጠና 6 ብሎክ 1 ቤት ቁጥር 046 ምክንያቱ ባልታወቀ በተነሳ እሳት አደጋ ወደ ለሌላ ሳይዛመት መቆጣጠር ተችሏ የእሳት አደጋ ስራ አመራር የበዓላት ቅድመ አደጋ የጥንቃቄ የግንዛቤ ማጨበጫ የጎዳና ቅስቀሳ ስራ ተሰርቷል ።
- 2100 በራሪ ወረቀት፣2 ባነሮች ከቅርንጫፍ ሰራተኞች ጋር ከበጎ ፍቃደኞችእና ብሎክ ካውንስል አባላት ጋር የበዓላት የቅድመ አደጋ ጥንቃቄ የጎዳና ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርቷል።
- በልደታ ክፍለ ከተማ ደመራ ሚደመርባቸው ቦታዎች የተለዩ 142 ቦታዎች ሲሆኑ የእሳት ተጋላጭ 42 ቦታዎች ናቸው እንዚህ ቦታዎች ተለዋጭ ቦታ ተስተካክሏል።

የጎርፍ አደጋ ችግር:-

- ወረዳ 01 የጣለው ከባድ ዝናብ ጤና ጣቢያ ጀርባ የወንዝ ዳርቻ ቤቶች ኩሽና አጥር የመሬት መንሸራተት ገጥሞ በሰው ህይወት የደረሰ አደጋ የለም።
- ወረዳ 06 የጣለው ከባድ ዝናብ ሰላም አካባቢ 8 አባወራዎች ቤት በተወሰነ መልኩ በመግባት የወደመ ንብረት የለም
- ወረዳ 02 የጣለው ከባድ ዝናብ አማካኝነት 1ግለሰብ ቤት ጎርፍ በመግባት የቤት ቁሳቁስ ሙሉ በሙሉ ጉዳት የደረሰ ሲሆን በሰው ላይ የደረሰ ጉዳት የለም
- ወረዳ 02 በ1ቤት የሬድዮ ጣቢያ የድጋፍ ግንብ ወድቆ ግርፍ የገባ ሲሆን በሰውና በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት የለም።
- ወረዳ 01 ልማት ምንጭ አካባቢ ብሎክ 10 ልዩ ስሙ 18 አባወራ ብሎክ 11 ልዩ ስሙ 49 አባወራ ብሎክ 23 እነዚህ ብሎኮች 18 ቤቶች ላይ የቤት ቁሳቁስ ላይ ጉዳት አድርሷል።
- ወረዳ 04 ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያ መሻገሪያ ድልድይ ስር የተደፈነ የወንዝ ማወረዳ ትቦ መክፈት ስራ ተሰርቷል

### የህዝብ ንብረት ከብክነት የማዳን ተልዕኮ

መንግስት ለስራ እንዲዉል በጀት መድቦ ግዢ በመፈጸምና ግብአት በማሟላት ስራዉን የተቀላጠፈ እንዲሆን እያደረገ ይገኛል። ግብአቶቹም ለሚመለከተዉ አካል በሚያስፈልገዉ ልክ ስርኣቱንና ፍትሃዊነቱን በጠበቀ መልኩ የማሰራጨቱን ተግባር ደግሞ በሚመለከተዉ አካል እንዲከናወንም በኃላፊነት ተቋማት ስራቸዉን ይሰራሉ። ከእዛ ባለፈ ግን ንብረቶቹ ምን ላይ ዋሉ እና ተቋማቱ የተሰጣቸዉን ንብረትና የሚሰሩበትን ቦታ በአግባቡ እየተጠቀሙ መሆናቸዉን በተጨማሪም ሌሎች ጉዳዮችን የሚከታተለዉ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ይሆናል።

ይህ እንደ መንግስት ተቋም ሲሆን በሌሎች መስሪያ ቤቶችም አሰራሩን ተከትሎ ተግባሩን የሚያከናዉኑ ይሆናል። የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ልደታ ፋና የመጽሄት አምዳችንም እንደ ልደታ ክፍለ ከተማ ያሉ ንብረቶችን እና የመስሪያ ቦታ በአግባቡ የመከታተሉ ተግባር ላይ ምን እየሰራ ነዉ የሚለዉን ለመመልከት ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ከአቶ ቢኒያም ታደሰ ጋር ቆይታ አድርጓል በንባብ እንድትከታተሉን ጋበዝናችሁ።



**ቢኒያም ታደሰ**
**የመንግስት ንብረት አስተዳደር ጽ/ቤት**

**ልደታ ፋና፡-** የጽ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት ምንድን ነው?

**አቶ ቢኒያም፡-** ጽ/ቤቱ ከከተማ አስተዳደሩ በአዋጅ 84/2016 በተሰጠዉ ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ዘርፈ ብዙ ተግባራቶች የሚያከናዉን ተቋም ነዉ።
ከእነዚም መካከል ሊጠቀሱ የሚችሉት

**1.** በመንግስት ህንጻ ንብረት አስተዳደር ላይ ለከተማው አስተዳደር የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል ያማክራል።

**2.** የከተማው አስተዳደር ህንጻዎችና ቋሚ ንብረቶችን ይመዘግባል በበላይነት ያስተዳድራል ያድሳል ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ህንጻዎች በመለየት እንዲጠገኑ ያደርጋል።

**3.** የህንጻና ንብረት አስተዳደር እና አጠቃቀም ዘመናዊ ስርዓቶችን ይዘረጋል ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል ምድረ ግቢን ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ያደርጋል

**4.** የመንግስት ህንጻዎች አጠቃቀም ለተጠቃሚው ያላቸው ተደራሽነት እና ከወጪ አንፃር ውጤታማ መሆቸውን ያረጋግጣል።

**5.** የተቋማትን ፍላጎት የስራ ባህሪይ እና የተገልጋይ ሁኔታን በማጥራት የተቋማትንና የስራ ክፍሎች የስራ ቦታ ይደለድላል።

**6.** የከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ለአገልግሎት አሰጣጥ የሚያስፈልጋቸው ህንጻዎች የኪራይ ደረጃ አጥንቶ ይወስናል ለመንግስት አገልግሎት የሚውሉ ህንጻዎች እንዲገነቡ ያደርጋል።

**7.** በከተማው ውስጥ ባለቤት የሌላቸው ህንጻና ንብረቶችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተረክቦ ያስተዳድራል።

**8.** የመንግስት ህንፃዎች ወጥ የሆነ ስታንዳርድ እና ዲዛይን እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል ያስገነባል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

**9.** የህንጻ አስተዳደር ሥራዎች የተቀላጠፉና ውጤታማ እንዲሆኑ የውስጥ አደረጃጀት እና የቢሮ ቁሳቁስ ስታንዳርድ ያዘጋጃል እንዲተገበር ያደርጋል።

**10.** በመንግስት የንብረት አያያዝ ስርዓት መሰረት የመንግስት ንብረቶች በአግባቡ ስለመያዛቸው እና ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የንብረት ኦዲት ያደርጋል።

**11.** የህንጻና የንብረት ኦዲት ውጤት መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ ያልወሰዱ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለይቶ ተጠሪ ለሆነላት ቢሮና ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።

**12.** አግባብ ባለው ህግ ቋሚ ንብረቶች ዋጋ እንዲወጣላቸው እና በየዓመቱ የዕልቀት ዋጋ እንዲሰላላቸው በማድረግ መንግስት የቋሚ ንብረቶች የያዙትን ዋጋ እንዲያውቅ ያደርጋል።

**13.** መንግስት በሚያስተዳድራቸው ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ህገወጥ ድርጊቶችን ይከላከላል፤ ተፈጽሞም ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

**14.** የመንግስት ህንፃዎች የሚገነቡበት ቦታ ያስፈቅዳል፤ ይመዘግባል፤ ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይጠብቃል።

**15.** የመንግስት ህንፃዎች የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣ የጽዳትና ውበት፣ የጥበቃ፣ የመጀመሪያ ህክምና፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ፣ የመኪና እጥበት እና የህፃናት ማቆያ አገልግሎቶች ተግባራትን ያከናውናል።

**ልደታ ፋና፡-** ተቋሙ የመንግስት ንብረትን ለታለመለት አላማ እንዲውል ከመቆጣጠር አኳያ በበጀት ዓመቱ ምን ተሰርቷል?

**አቶ ቢኒያም፡-** በ2016 በጀት ዓመት የ6 ህንጻዎች ኪራይ ዋጋ በወቅቱ ጥናት በማድረግ ክፍያ እንዲፈጸም አድርጓል፣በ49 ተቋማት የመንግስት ሃብት እንዳይባክን የቋሚና አላቂ ንብረቶች ቆጠራ ማከናወን ችሏል፣ ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ቋሚና አላቂ ንብረቶች አገልግሎት ወደ ሚሰጡበት ተቋም እንዲተላለፉ ማድረግ ተችሏል፣አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በ16 ተቋማት ማስወገድ፣በ26 ተቋም የንብረት ኦዲት ማደረግ፣በ16 ተቋማት ኦዲት ኢንስፔክሽን ማከናወን፣

ግቢውን ለባለሙያና ለባለድርሻ አካላት ውብና ጽዱ የማድረግ፣ የህጻናት ማቆያ የመኪና ማቆሚያ እንዲሁም በተለያዩ ክፍለ ከተማው ውስጥ የሚገኙ ህንጻዎች የመብራት የኤሌክትሪክ መስመርና የሳኒተሪ ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን የመጠገን ስራዎች ማከናወን ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** አገልግሎት ለማዘመን ምን ተሰርቷል?

**አቶ ቢኒያም፡-** በአጠቃላይ 443 ህንጻዎች ሙሉ በሙሉ ምዝገበ የተከናወነ ሲሆን የቋሚ ንብረት ምዝገባ እና የተጠቃሚዉን ስም ከተረከበዉ ንብረት ጋር አባሪ አድርጎ በበለጸገው ሶፍት ዌር ዉስጥ ያስገባን ሲሆን የሚቀሩን ስራዎች ለመፈጸም ባለሙያዎቻችን በተገቢዉ መንገድ እየሰሩ ይገኛሉ።

ሌላዉ መረጃ በማጥራትና በ5 ጽሎች በ10 ወረዳዎች በ8 ጤና ጣቢያዎች የበለጸገው የቋሚ ንብረት ሶፍት ዌር ተግባራዊ ተደርጎ ስራዉን በተገቢዉ መንገድ እየተሰራበት ሲሆን በ26 ትምህርት ቤቶች መረጃ አጥርቶ ሲስተሙ ላይ ለማስገባት በሂደት ላይ እንገኛለን። በአጠቃላይ ግን አገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመንና የተገልጋዩን ፍላጎት ለመጨመር ሰፊ ስራዎች እየሰራን ነዉ ስራ ላይ ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-** በሚቆጣጠራቸውና በሚደግፋቸው ተቋማት ላይ የሚፈጸሙ ህገወጥ ተግባሮችን በምን አግባብ ይከታተላል?

**አቶ ቢኒያም፡-** በጽ/ቤቱ ራሱን የቻለ ክትትልና ድጋፍ ባለሙያ አለ፡፡ በሚሰሩ ስራዎች ላይም ከክፍለ ከተማዉ እስከ ወረዳዉ ድረስ በመዉረድ የመደገፍ፣ የማስተካከልና ችግር በሚስተዋልባቸዉ ተቋማት ላይም ቁጥጥር አድርጎ እርምጃ ይወስዳል። የእርምጃ አወሳሰዱንም እንደየሁኔታዉ ይለያያል።

1. በ49 ተቋም የመንግስት መመሪያና ደንቡን እንዲያውቁ በአዋጅ በመመሪያ ዙሪያ ለሁሉም ባለሙያ የግንዘቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል

2. በአመራርም ሆነ በፈጻሚ የሚከናወኑ ህግ ወጥ ድርጊቶችን ለመቀነስ የኦዲት ዳሰሳ ጥናት በየአመቱ በማድረግ እንዲለይ ይደረጋል

3. በተለዩት ላይ የንብረት ኦዲት እንደ ቅድመ ተከተላቸው ያከናውናል

4. በተደረገው ኦዲት ኢንስፔክሽን በማድረግ ህገ ወጥ የሆነ አሰረር የፈጠረ ባለሙያም ሆነ አመራር ተጠያቂ በማድረግ የማስመለስ ስራ ይሰራል

5. እያንዳንዱ ተቋም ህግ ወጥ ለሚፈጸሙ ስራዎች በመረጃ በጥቆማ ወደ ጽ/ቤቱ ሲመጣ ሙሉ በሙሉ የማጥራት ስራ ይሰራል

## 2.የመንግስት ንብረት እንዳይባክንና ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ስርዓትን ለመዘርጋት ምን እየተሰራ ነው እንዲሁም የመንግስት ንብረትን ከብክነት ለመጠበቅ የባለድርሻ አካላት ሚና ምን መሆን አለበት?

- ከአመራር አንጻር እያንዳንዱ የተቋም አመራር ስራዎች ሲከናወኑ በመመሪያና ደንቡ መሰረት ማከናወን እንዳለባቸው አውቀው በተለይ የበለጸገው ሶፍት ዌር ወደ ኋላ እንዳይመለሱ እያንዳንዱ ቋሚ ንብረት ወቅቱን ጠብቆ ምዝገባ እንዲከናወንበት በማድረግ የተገዛው ዕቃ ባለቤት እንዲኖረው ማድረግ እንዲሁም እያንዳንዱ የተቋም አመራርም ሆነ ባለሙያ ሲለቅ፤ ሲዘዋወር፤ በጡረታ ሲወጣ ወ.ዘ.ተ ምክንያት የተረከበውን ንብረቶች በአግባቡ እንዲያስረክብ በማድረግ ክሊራንስ መስጠት እንዲሁም ከሌላ ተቋም የሚመጣ ካለበት መስሪያ ቤት ክሊራንስ እንዲያመጣ በማድረግ የአሰራር ስርዓቱን መጠበቅ።

- የመንግስት ንብረት ወስደው የማይመልሱ በተቋሙ ካሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 10/2003 መሰረት እያንዳንዱ የተቋም አመራር የሚባክነውን የመንግስት ንብረት ማስመለስ መቻል።

- ከባለሙያ አንጻር የተረከበውን ቋሚና አላቂ ንብረቶች ለመንግስት ስራ ብቻ እንዲውሉ ማድረግ

- የተረከበውን ቋሚ ንብረት በአግባቡ መያዝ እና ከቦታው ሲነሳ ለአስረከበው አካል በአግባቡ መመለስ የመለሰበትን መረጃ መያዝ።

- ንብረት ተረክቦ የማይገለገለበት ሆኖ ሲገኝ ወዲያውኑ ተመላሽ ማድረግ።

- በማንኛውም ሰዓት ከተቋሙ ሲለቅ ክሊራንስ እንዲሰጠው ጠይቆ መያዝ።

## 3.የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ

•በ49 ተቋም ያሉ አመራርና ፈጻሚዎች የሚረከቡትን ንብረቶች በአግባቡ በመጠቀምና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገድ ለማድረግ ተቋሙን ውብና ጽዱ ለስራ ምቹና ማራኪ በማደረግ የክፍለ ከተማው እንዲሁም የተቋሙን ራዕይ በጋራ ማሳካት

## 4.መልዕክት

•ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋትና የመንግስት ንብረት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል እንዲሁም ውብ ጽዱና አስተማማኝ ጥበቃ ያለው ተቋማትን ለመፍጠር ከምንም ጊዜ በላይ ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ስራዎችን ለማከናወን እቅድ አቅዶ ወደ ስራ የገባ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለዕቅዱ ተግባራዊነት የላቀ ሚናቸውን እንዲወጡና እንዲሁም ውስን በሆነው በህዝብና በመንግስት ሀብት በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ተገዝተው ለስራ የሚቀርቡ ንብረቶችን በአግባቡ በመያዝና በመጠቀም ለታለመለት ዓላማ እንዲውሉና አስፈላጊ ከሆኑ ለግል ጥቅም ከሚውልና በምን አገባኝ ስሜት ከመጠቀም በመቆጠብ ሁላችንም የዜግነት ሚናችን እንወጣ!!!

## ደንብና ስርአት ማክበር ስልጡንነት ነው

የልደታ ክፍለ ከተማ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት በከተማችን ያሉ ደንብ መተላለፎችን መስመር ለማስያዝና በህገ ወጥ አሰራሮች ምክንያት በህጋዊ መንገድ ስራቸውን የሚሰሩ አካላት ተጎጅ እንዳይሆኑ ለማድረግ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።ይህን ስራ ተግባራዊ ለማድረግ በአዋጅ ቁጥር 84/2016 መሰረት ወደስራ ገብቷል።የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት በአዋጅ ተቋቁሞ ወደስራ ከገባ በኋላ የደንብ መተላለፎችን መስመር ለማስያዝ እየሰራ ሲሆን እያከናወነ ያለውን ተግባር የጽ/ቤቱን ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ካሴ በመጠየቅ ለመጽሄት ግብዓት በመውሰድ እንዲህ አቅርበነዋል።

# የልደታ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Lideta Sub-City Communication office



**አቶ ደሳለኝ ካሴ**
**የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ሃላፊ**

ደንብ ማስከበር  እንደተቋም ከተመሰረተ በኋላ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት  መሰረት በዋናነት ዘጠኙ የደንብ መተላለፎች እንዳይፈጽሙ የመከላከል  መቆጣጠር  ሲሆን ተግባራቱ ተፈፅመው ሲገኙ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የሚስተዋለው የደንብ መተላለፎች ሥርዓት ለማስያዝ  የከተማ  አስተዳደሩ  ልዩ  ትኩረት  ሰጥቶ  እየሰራ  ይገኛል፡፡በተለይ  ቅንጅታዊ  ስራዎች  በማጠናከር  ህብረተሰቡን  በማሳተፍ በከተማችን የሚሰተዋለውን መጠነ ሠፊ እና ዘርፈ ብዙ እንዲሁም ውስብስብ የሆነውን የደንብ መተላለፎች ሥርዓት የማስያዝ አላማውን ከግብ ማስያዝ ችሏል፡፡ነገር ግን አሁንም ችግሩን መቀነስ ተችሏል እንጂ ሙሉ  ለሙሉ  መቅረፍ  አልተቻለም፡፡በከተማችን  የሚታዩ  የደንብ መተላለፎችን ስርዓት ለማስያዝ እየተደረገ ባለው ጥረት ህብረተሰቡ ከመንግስት ጎን በመሆን የሚታዩትን የደንብ መተላለፎች ለመቀነስ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የግንዛቤ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡

ሀገራችንም  ሆነ  ከተማችን  ከነበረችበት  ኢኮኖሚያዊ  ማህበራዊ ተግዳሮት  አንፃር  ሙሉ  በሙሉ  የደንብ  መተላለፍን  ማጥፋት ባይቻልም  ቅድመ  መከላከል  እና  ግንዛቤ  ማስጨበጥ  ስራዎች በማጠናከር  50,456  ማህበረሰቦች  በ9ኙም  የደንብ  መተላለፎች የግንዛቤ ማስጨበት ስራዎች የተሰራበት በጀት አመት ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የደንብ መተላለፎችን ተፈፅመው በተገኙ ጊዜ ህጋዊ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የደንብ መተላለፍ ምጣኔን አሁን ካለበት በእጅጉ መቀነስ ይታላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በልደታ ክፍለ ከተማ የሚስተዋሉ ህገ ወጥ እንቅስቃሴዎችን ለመግታት የተለያዩ አማራጮችን በመወሰድ በህገ ወጥ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ አካላት  ከድርጊታቸው  እንዲታቀቡ  የሚያደርጉ  ስራዎች  እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡በክፍለ  ከተማችን  በስፋት  የሚስተዋለው  ህገ  ወጥ  የጎዳና ንግድ፣ህገ ወጥ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ፣አዋኪ ድርጊት፣ ህገ ወጥ ማስታወቂያ፣ህገ ወጥ የመንገድ አጠቃቀም ፣ህገ ወጥ ግንባታ እና የእንስሳት ዝውውርና እርድ ማከናወን እናም ሌሎች  የእርምት እርምጃዎች የተወሰዱበት ሲሆን ይህን ህገ ወጥ ተግባራት በፈፀሙ 316 ግለሰቦች  እና ተቋሟት በ33 ግለሰቦችና ተቋማት በተወሰደው ርምጃም 2,292,040 ብር ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የተደረገበት በጀት አመት  ነው፡፡እንዲሁም  በኮሪደር  ልማቱ  ላይ  መንግስት  የሰጠውን ተልዕኮ መሰረት በማድረግ ደንቡን እያስከበርን ነው፡፡

በተለይም  ህገ  ወጥ  የጎዳና  ላይ  ንግድ  እና  በህገ  ወጥ  የመንገድ አጠቃቀም አንፃር በሚወሰዱ እርምጃዎች  ላይ ለምን ይሄ ይሆናል? ምናለ ሰርተው ቢኖሩ? ቤተሰቦቻቸውን ሰርተው ቢያስተዳድሩ? የሚሉ አሉ፡፡

በእርግጥ እሳቤው ትክክል ቢመስልም ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት ግን ብዙ ችግሮች ይስተዋሉበታል፡፡ ምክንያቱም ህጋዊ ንግድ ፍቃድ አውጥተው ሱቅ ተከራይተው አሰራሩን ተከትለው እና ለመንግስት ግብር እየከፈሉ የሚሰሩትን ህጋዊ ነጋዴዎች የሚጎዳ እና በሀገር እድገት ላይ ጉዳት የሚያድረስ ከመሆኑ ባለፈ በትራፊክ ፍሰቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ መጨናነቅ የሚፈጥር ከመንገድ መዘጋት ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ አደጋ በሠው፣በንብረት ላይ ጉዳት እንዲከሰት መንስኤ የሚሆንበት ችግር ሲሆን ይስተዋላል፡፡የከተማችንን ገፅታም ያበላሻል ሀገር እንደሀገር ሁለንተናዊ እድገቷ የሚረጋገጠው የህግ የበላይነት ሲከበር ሁሉም ሰው በህግና ሥርዓት ሲመራ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ሲረጋገጥ በመሆኑ የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ፅ/ቤት በከተማችን ብሎም  በክፍለ  ከተማችን  የሚስተዋሉ  የደንብ  መተላለፎችን ጉልበት በመስጠት ከተቋቋሙ ተቋማት አንዱ መሆኑን በማስታወስ በያዝነው 2017 በጀት አመት በውጤታማነት የሰራናቸው እና ችግሩን ያቀለልንበትን ለአንባቢያን ለማካፈል በማለት ነው፡፡



**አቶ ቢንያም ሰይፉ**
**የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ሃላፊ**

የልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት በ2017 በጀት  አመት  በጽ/ቤቱ  አከናውናለሁ  ያለቻውን  ስራዎች  በእቅድ በመያዝ  በቀን  ለቀን  አገልግሎት  አሰጣጥ  ተግባር  ለህብረተሰባችን የተሻለ እርካታን ለመፍጠር የሚያግዙ የአሰራር ስርአቶችን በመከተል በበጀት አመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተለያዩ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

በአጠቃላይ በ2017 በጀት አመት የመጀመሪያው 6 ወራት አራት ዋና ዋና ግቦችን ማለትም ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ፤ደረጃቸውን የጠበቁ የዲዛይን ፕላኖች፣ የግንባታ ፈቃድ እና በቴክኖሎጂ የተደራጀ መረጃ አሰራርን ማሻሻል፤ጠንካራና ውጤታማ የግንባታ ክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት ማጎልበት እና የከተማዋን ፕላንና የግንባታ ሕግ የተከተለ የሕንፃ መጠቀሚያ፤ የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻልን መሰረት ያደረገ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በተሻለ መልኩ ለማከናውን ተችሏል ። በተጨማሪም በየአገልግሎቶቹ የሚከፈለውን የአገልግሎት ገቢ በመመሪያው መሰረት የተሰበሰበ መሆኑም በስድስት ወሩ ከሰራናቸው ስራዎች ውስጥ ይገኛሉ ።

በክ/ከተማችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የግንባታ እንቅስቃሴ በስፋት ለማስቀጠል ህግና ስርዓት የተከተለ እንዲሆን እንዲሁም የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል የከተማ አስተዳደሩ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን እንደገና ተቋቋሞ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶችን ለመወጣት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል።